مؤسسة دار الفكر
Dar Al-Fiker Foudation
فنفني – إثيوبيا

# The Qur'an and the Sunnah: The Time-Space Factor

*Dr. Taha Jabir al Alwani*
*Dr. Imad al Din Khalil*

# ቁርኣን እና ሱንና
# የጊዜ-ቦታ ተፅዕኖ

አዘጋጅ፡
ዶ/ር ጣሀ ጃቢር አል ዓልዋኒ
ዶ/ር ዒማድ አልዲን ኸሊል

ተርጓሚ፡
ዳር አል ፊክር ፋውንዴሽን

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2017

# The Qur’an and the Sunnah: The Time-Space Factor

Taha Jabir al Alwani
Imad al Din Khalil

# ቁርኣን እና ሱንና የጊዜ-ቦታ ተፅዕኖ

አዘጋጅ:
ዶ/ር ጣሀ ጃቢር አል ዓልዋኒ
ዶ/ር ዒማድ አል ዲን ኸሊል

ተርጓሚ፡-
ዳር አልፍክር ፋውንዴሽን

የቅጂ መብት በህጋዊ መንገድ ለዳር አልፍክር ፋውንዴሽን የተጠበቀ ነው።

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2017 G. C

DF-E-TrBs-17/29

መውጫ


የአርታኢዎች ማስታወሻ ---------------------------------------------3

ቁርአን፡የዕውቀት ቀዳሚ ምንጭ -----------------------------------------5

-የተወሰኑ ቁርኣናዊ ገፅታዎች ----------------------------------------- 14

ሱንናን በአግባቡ መረዳት ------------------------------------------- 33

- የዑማ ችግሮች ለመቅረፍ የሱንና ሚና --------------------------- 41
- ሱንናን ቃል በቃል የመተርጎም አደጋ ----------------------------42
- ለዑማው ተሃድሶ የሱንና ሚና -----------------------------------43
- መደምደሚያ ----------------------------------------------- 44

ቁርኣንና ዘመናዊ ሳይንስ፡የስነ ዘዴ ዕይታዎች -----------------------------45

1. የሳይንሳዊ ፍልስፍና፣ዓላማዎቹ እና የኢስላም መሠረታዊ መመርያዎች --47
2. ስነ-ዘዴው ------------------------------------------------- 50
3. ዕውነታዎች ------------------------------------------------- 53
4. ትግበራ -----------------------------------------------------55

## የአርታዒዎች ማስታወሻ

ለረጅም ዘመን እስካሁን ድረስ የዑማ ጥንካሬ፣ ጥራት፣ ዕውቀትና ንቃት ትላልቅ ምንጮች የሆኑት ቁርአንና ሱናን [1] በበቂ ሁኔታ ጥቅም ላይ አልዋሉም፡፡ በዚህም የተነሳ ዑማውም [2]ሆነ መላው ዓለም ከቁርአንና ሱናን ቁጥር ስፍር የሌላቸው ጠቀሚታዎችን ከማግኘት ተነፍገዋል፡፡

አሁን ዑምማው የራሱን ችግሮች ይበልጥ እያወቃ ስለመጣ፣ የተደበቁ ሐይሎችንም ስለተረዳ እና ታሪክንና ስልጣኔ ለማንሰራራት የመሪነት ሚናውን ለማደስ ባለው ፍላጎት በዚህ ምንጭ ላይ የመመርኮዝ ጉዳይ ከመቸውም ጊዜ በላይ ወቅታዊና አስቸኳይ ሆኗል፡፡ ሁለቱን ኢስላማዊ ምንጮች ዳግም መጎብኘትም ምሁራዊ ፣ አካዴሚያዊ ፣ ትዝታዊ ወይንም የማምለጫና የጊዜ ማሳለፍያ ጉዳይ ሳይሆን ያለተነገሩ ሽልማቶችን የማያስገኝ ታላቅ የግኝት ጉዞ ነው፡፡

እንደ ማናቸውም ትላልቅ የግኝት ጉዞች ሁሉ ይህኛውም ብዙ ተግዳሮትንና እንቅፋቶች የሚንረው ሊሆን ችላል፡፡ ይሁንጂ ወደፊት በሚኖረው ተልዕኮ ላይ ጠንካራ ፍላጎት ከታከለ እና የሁሉም ተጓዦች ታላቅ መሪና ከርሃን ምርቃቶችና ግርማ ሞገስ ከሰፈና ባዶ እጅም ሆነ ባዶ ነፍስ ወደ ኋላ መመለስ አይኖርም፡፡

1. ሱንና፡- በቀጥታ ትርጉም ሱንና ግልፅ መንገድ ወይንም የወጣ ገባ መንገድ ነው፡፡ ነብዩየተናገሩት፣ ያከናወኑት ፣ የተስማሙበት ፣ ወይንም ያወገዙት ማለት ነው፡፡ ሱንና ከቁርኣን ቀጥሎ የሸሪአ ምንጭና ሕጋዊ ማረገጫ ነው፡፡ እንደ ሸሪአ ምንጭነቱ ሱንና ምንጭነቱ ከቁርአን የሆነ መመሪያን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሁለተኘነት ሱንና የቁርአን ማብራሪያ ወይነም መገለጫን ሊይዝ ይችላል። ሶስተኛ፣ ሱናን በቁርአን ያልተጠቀሱ መመሪያዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ የብዙ ቁጥር ሱናን ጠቀሜታው ሕይወትን ፣ ስነ-ፍጥረትን የሚገዙ ሕግጋትንና መመሪያዎችን ያመለክታል፡፡
2. ዑማ (ብዙ ቁጥር ዑመም) ማሕበረሰብ ፣ ሕዝብ ማለት ነው፡፡ በተለይ የምዕመናን ወይንም መላው ሙስሊም ማሕበረሰቡ ነው፡፡ ሽልማቶች በእርግጥ ስፍር ቁጥር የሌሎቸው ናቸው፤ የሰውን እምቅ ችሎታንና የአላህ ዕቅድ የበለጠ የሚጣወቅበት ፣ ሚዛናዊ ፣ ተንቀሳቃሽ እና ዓላማ ያለው ሕይወት እንደገና

የሚገኝበት ፣ ክብር፣ ሰላምና አንድነት ለሁማውም ሆነ- ለረጅም ዘመን በተሳቱ ርዕዮቶችና ሀሳቦች ስትሰቃይ ለቆየችው ዓለም የሚጎናፀፍበት ይሆናል፡፡

በአይአዎንታነት በውብና ጥንቅ የቁርአንና ሱንና ገፆች ውስጥ ወደ ከለፈው ጊዜና ቦታ የሚዳረገው ጉዞ የማህበራዊና ታሪካዊ ለውጥ አንቀሳቃሾችኝና በምድር ላይ የሰውን ሚና በተመለከተ የበግ ብስል ንቃት ሊይዝ ይገባል፡፡ ይህ ሙስሊሞች የሚያስችሉ ነገሮችና እንዲኖራቸውና ችሎታውንም የሚያሻሽልና የሚስል ነው፡፡

የፍለገው ሰብዓዊና ንፅፅራዊ ጎኖች ወደ ሙስሊሞችና የሰው ልጆች የሚያቀርቡን ብቻ ሳይሆን የበለጠ በከፍተኛ ደረጃ-በእርግጥ እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ወደ የሁሉም ሕይወትና የሁሉም ጥረት ፈጣሪ ሊያቀርቡን ይገባል፡፡

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው ጥናታዊ ወረቀት ዶ/ር ጣሀ አል ዓልዋኒ በአላህ (ሱ.ወ) የወረደው እና ከግድፈት የሚጠበቀው ቁርአን የዕውቀት ምንጭ ፣ በአግባበብ ከተነበበ ብዙ ጠቀሜታዎችን የሚገልፅ ምንጭ መሆኑን ያብራሩበት ነው፡፡ ዶክተር አል ዓልዋኒ ቁርአን የሚነበብበት ሁለት ደረጃዎች መኖራቸውን ይከራከራሉ፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ መንፈሳዊ ምጥቀት የሚገኝበት ሲሆን ሁለተኛው ደረጃ ሰው በኺሊፋነቱ በምድር ላይ ለሚኖረው አዎንታዊ ድርጊት ትእይንተ ዓለምን እንዲያጠናና እንዲመረምር የሚያነሳሳ ነው፡፡ በአንድነት ሁለቱን ንባቦች ማከናወን በሁለቱ መሃከል ሚዛን መጠበቅ በዚህኛው ዓለምም ሆነ ከሞት በኋላ ላለው ዓለም ደህንነት ለማስገኘት መመዘኛዎችና ቅደም ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ቀደምት ትውልዶች በዋናነት በቁርአ እና የአኼራ መደበኛ ገፅታዎች (ጉዳዮች) እና ወሕይ እንደ ፊቅሕና የሕግ ምንጭ ብቻ እንደሆኑ ይቆጠሩ ነበር፡፡ ይህ ውስጥ ያለውን ዋጋ ለመመርመርና ለማጥት የነበረውን ታላቅ ጉጉት አግዷል፡፡ ዶ/ር ዓልዋኒ ቁርአንን በምሉዕ መንገድ ለመረዳት የሚያስችል አዲስ አቀራረብ ማስፈለጉን የሚደግፉት ለዚህ ነው፡፡

በዚህም የዶ/ር አል ዓዋኒ ሁለተኛው ጥናታዊ ፅሑፍ ርዕስ ጉዳይ - ቁርአንን ባግባብ ማንበብና መገንዘብ የነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) የነቢይነት ዓላማዎች የተሻለ ለመርዳትና የሱንናቸውን መንፈስ በምክንያታዊ መንገድ ለመተግበር እንደሆነ

ያስረዳል፡፡ ይህም ከምንኖር በትን ጊዜና ቦታ አስተዋይ መመዘኛዎች ጋር የቀረበ ነው፡፡

ዳ/ር ዒማድ አል ዲን ኺላል በበኩላቸው በቁርአንና በሳይንስ መሀከል ላለው ግንኙነት ቁርአን የሳይንስ መመሪያ መጽሕፍ አለመሆኑንና በውስጡ የተካተተው ሳይንስ ተኮር መረጃዎች በግልፅ ሳይንሳዊ ዕውነታዎች ወፃንም አመለካቶች ቅርፅ የሚገኙመሆናአውን ያብራራሉ፡፡ በእሳቸው ዕይታ ቁርአን እነዚህ ሳይንስ-ተኮር መረጆዎች ለመተንተን ተቀያያሪና ዋሉዕ ስነ-ዘዴን ያስረዳል፡፡ ይህ ስነ-ዘዴ በጊዜና በየትኛውም ዘመንና አካባቢ ዋጋ የላቸው ናቸው፡፡

ቁርአንና ሱንናን በአዲስ መንገድ ለማንበብ የዚሁ ሃሳቦች በቅርብ ዓመታት ከተከልቱ ኢስላማዊ ና ሌሎች ማዕዘኖች አኳያ የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ዶ/ር ዓልዋኒ እና ዶ/ር ኸሊል ሁለቱ ታዋቂ ሙስሊም አሳቢዎች በኢስላማዊ ድንበር ውስጥ ለትክክለኛ የእበኚህ ምንጮች አቀራረብ ሃሳቦቻቸውን አቅርበዋል፡፡

**ቁርአን ፡ የዕውቀት ቀዳሚ ምንጭ**

ኢስላም የመጨረሻው መልዕክት ለሁሉ ፍጥረት የምህረት፣ብርሃን፣የመመርያና የፈውስ መገለጫ ነው ኣለህ እንዲህ ይላል

وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧ ألانبياء : 107

‹‹ ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አላክንህም ›› (ቁርኣን 21፡107)
ይህመልእክትና መፅሓፍ ቁርኣን ሁልጊዜ ሰዎችን የሚመራና ከጥመትና ከአፈንግጦ የተጠበቀ የተከበረ ነው፡፡ አላህ ይህን እንዲህ በማለት አረጋግጦል፡-

لَّا يَأۡتِيهِ ٱلۡبَٰطِلُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَلَا مِنۡ خَلۡفِهِۦۖ تَنزِيلٞ مِّنۡ حَكِيمٍ حَمِيدٖ ٤٢ فصلت:42

‹‹ ከኋላም ከፊትም ውሸተ አይመጣበትም፤ጥበበኛ ምስጉን ከኾነው ጌታ የተወረደ ነው፡፡ ›› (ቁርኣን 41፡42)
ቁርኣን መጀመርያና መጨረሻ የሌለው የአላህ መፅሓፍ ለፍጥረታት ሁሉ መስጠንቀቂያ ይህን ዘንድ የነብያት መደምደምያ በሆኑት ነብዩ ሙሓመድ ሰ.ዐ.ወ በኩል የተለከ ነው፡፡ በእርግጥ ነገ ሙሓመድ በኃላ ነብዩ የለም ከቁርኣን በሓለም ራእይ የለም፡ከነብዩ ሙሓመድ በፊት ነብያዊ ተልዕኮዎች በተከታታይ ነበሩ፡፡

እያንዳንዱ ሕዝብ በራሳቸው ቋንቋ ከሁኔታቸው ጋር ተመጣጣኝ በሆኑ መንገድ ልዩ መልዕክተኞች ተልኮላቸዋል፡ ነብያቱም በማይቀየር መንገድ ለሰዎች የበለጠ አግባብ ባለው ሁኔታ ለሰዎች ምላሽ ስጥተዋል፡፡

وَإِن مِّنۡ أُمَّةٍ إِلَّا خَلَا فِيهَا نَذِيرٞ ٢٤ فاطر: 24

‹‹ ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም። ›› (ቁርኣን 35፡24)

وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوۡمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمۡۖ ٤ إبراهيم: 4

‹‹ከመልክተኛ ማንኛውንም፤ ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም፤ ›› (ቁርኣን 14፡4)

ቀደም ያሉት ነብያዊ መልዕክቶች ለሰዎች በመልዕክቱ እንዲያምኑ መነሳሳትን ዓለማ በደራጉ ትዕይንት ዓለማዊ ምልክቶችና አካላዊ ተኣምራት የተጀቡ ነበሩ፡፡

አንደኛው ነብይ ለምሳሌ ለሕዝቡ ጥላ .. ፍጡር ተራራን በአናታቸው ላይ አንዣቧል፤ ህዝብ በሁለቱ የተከፈሉ ክፍሎች መሃከል በደረቅ መተላለፍ ላይ ተራምደው እንዲሻገሩ ባሕረን ሰንጥቀዋል ፤ ባትራቸውን በመሬት ላይ በመጣል ወደ እባብ እንዲቀየር አድርገዋል ወይንም በኪሳቸው እጃቸውን አስገብተው ሲወጣ ወደ ነጭነት ቀይረዋል፡፡ ልለኛው ነብይ እንደ ምልክት አስደናቂ ሴት ግመል ተልካላቸዋለች፡፡

ሶስተኛው ነብይ  ሙታንን አስነስተዋል፤ዓይን ስውራንንና የስጋ ደዌ ሕሙማንን አድነዋል፡፡ ምልክቶችንና  ተአምራትን ከተመለከቱ በኋላ ነብዮቻቸውን ያልተቀበሉ ለሕዝብ ቅጣትና ውድመት ደርሶባችዋል፡፡ ይሁንጂ አላህ ሙስሊሙን ዑምማ በማክበር ከእለቂትና ከጥፋ አትርፏል፡፡

የመካ ጠኦት አምላኪዎች ነብዩ ምንጭ እንዲያፈልቁላቸው ወይንም በመሰላል ወደ ሰማይ እንዲወጡ ወይንም በወርቅ ያጌጠ ቤት እንዲኖራቸው እየጠየቁ በሰዋዊነታቸው ሲያወግዟቸው አላህ ለጥያቂያቸው ምላሽ አልሰጣቸውም፡-

وَقَالُواْ مَالِ هَٰذَا ٱلرَّسُولِ يَأۡكُلُ ٱلطَّعَامَ وَيَمۡشِي فِي ٱلۡأَسۡوَاقِ لَوۡلَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مَلَكٞ فَيَكُونَ مَعَهُۥ
نَذِيرًا ﴿٧﴾ أَوۡ يُلۡقَىٰٓ إِلَيۡهِ كَنزٌ أَوۡ تَكُونُ لَهُۥ جَنَّةٞ يَأۡكُلُ مِنۡهَاۚ وَقَالَ ٱلظَّٰلِمُونَ إِن
تَتَّبِعُونَ إِلَّا رَجُلٗا مَّسۡحُورًا ﴿٨﴾ الفرقان:7-8

‹‹ ለዚህም መልክተኛ፣ ምግብን የሚበላ በገበያዎችም የሚኼድ ሲኾን፣ ምን (መልክተኛነት) አለው? ከርሱ ጋር አስፈራሪ ይሆን ዘንድ፣ ወደርሱ መልአክ (ገሃድ)፣ አይወረድም ኖሯልን? አሉ። ወይም ወደርሱ ድልብ አይጣልለትምን? ወይም ከርሷ የሚበላላት አትክልት ለርሱ አትኖረውምን? (አሉ)፤ በዳዮቹም (ላመኑት) የተደገመበትን ሰው እንጂ ሌላን አልተከተሉም፣ አሉ። ›› (ቁርኣን 25፡7-8)

በሌላ አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

وَلَقَدۡ صَرَّفۡنَا لِلنَّاسِ فِي هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ مِن كُلِّ مَثَلٖ فَأَبَىٰٓ أَكۡثَرُ ٱلنَّاسِ إِلَّا كُفُورٗا ﴿٨٩﴾ الإسراء:89

‹‹ በዚህም ቁርአን ውስጥ ከምሳሌው ሁሉ ለሰዎች በእርግጥ መላለስን፤ አብዛኛዎቹም ሰዎች ክሕደትን እንጂ ሌላን እምቢ አሉ። ›› (ቁርኣን 17፡89)

አሁንም በሌላ አንቀፅ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

وَقَالُواْ لَن نُّؤۡمِنَ لَكَ حَتَّىٰ تَفۡجُرَ لَنَا مِنَ ٱلۡأَرۡضِ يَنۢبُوعًا ﴿٩٠﴾ أَوۡ تَكُونَ لَكَ جَنَّةٞ مِّن نَّخِيلٖ وَعِنَبٖ
فَتُفَجِّرَ ٱلۡأَنۡهَٰرَ خِلَٰلَهَا تَفۡجِيرًا ﴿٩١﴾ أَوۡ تُسۡقِطَ ٱلسَّمَآءَ كَمَا زَعَمۡتَ عَلَيۡنَا كِسَفًا أَوۡ تَأۡتِيَ بِٱللَّهِ
وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ قَبِيلًا ﴿٩٢﴾ أَوۡ يَكُونَ لَكَ بَيۡتٞ مِّن زُخۡرُفٍ أَوۡ تَرۡقَىٰ فِي ٱلسَّمَآءِ وَلَن نُّؤۡمِنَ لِرُقِيِّكَ حَتَّىٰ
تُنَزِّلَ عَلَيۡنَا كِتَٰبٗا نَّقۡرَؤُهُۥۗ قُلۡ سُبۡحَانَ رَبِّي هَلۡ كُنتُ إِلَّا بَشَرٗا رَّسُولٗا ﴿٩٣﴾ وَمَا مَنَعَ ٱلنَّاسَ أَن يُؤۡمِنُوٓاْ إِذۡ
جَآءَهُمُ ٱلۡهُدَىٰٓ إِلَّآ أَن قَالُوٓاْ أَبَعَثَ ٱللَّهُ بَشَرٗا رَّسُولٗا ﴿٩٤﴾ الإسراء:90-94

‹‹አሉም፡-ለኛ ከምድር ምንጭን እስከምታፈነዳልን ለአንተ አናምንም፤ወይም ከዘንባባዎችና ከወይን የሆነች አትክልት ለአንተ እስከምትኖርህና በመካከልዋም ጅረቶችን በብዛት እስከምታንቧቧ፤ ወይም እንደምትለው ከሰማይ ቁራጮችን በኛ

ላይ እስከምታወድቅ፤ ወይም አላህንና መላ እክትን በግልጽ እስከምታመጣ፤ ወይም ከወርቅ የሆነ ቤት ላንተ እስከሚኖርህ፤ ወይም በሰማይ እስከምትወጣ፤ ለመውጣትህም በኛ ላይ የምናነበው የኮነን መጽሐፍ እስከምታወርድልን ድረስ ፈጽሞ አናምንልህም፤ (አሉ)። ጌታዬ ጥራት ይገባው፤ እኔ ሰው መልከተኛ እንጂ ሌላ አይደለሁም፤ በላቸው። ሰዎችንም መሪ (ቁርአን) በመጣላቸው ጊዜ ከማመን አላህ ሰውን መልከተኛ አድርጎ ላከን? ማለታቸው እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም። ››
(ቁርኣን 17፡90-94)

በዚህ ሱራ (አል-ኢስራዕ) ውስጥ ለመጠበቅ ጥያቄዎቻቸው አለህ በጥበብ የተሞላ ምላሽ ለጠኦት አምላኪዎች ሰጥቷል፡፡

وَمَا مَنَعَنَآ أَن نُّرۡسِلَ بِٱلۡأٓيَٰتِ إِلَّآ أَن كَذَّبَ بِهَا ٱلۡأَوَّلُونَۚ وَءَاتَيۡنَا ثَمُودَ ٱلنَّاقَةَ مُبۡصِرَةٗ فَظَلَمُواْ بِهَاۚ وَمَا نُرۡسِلُ بِٱلۡأٓيَٰتِ إِلَّا تَخۡوِيفٗا ﴿٥٩﴾ الإسراء:59

‹‹ ታምራቶችንም ከመላክ የቀድሞዎቹ ሰዎች በርሷ ማስተባበልና (መጥፋት) እንጂ ሌላ አልከለከለንም፤ ለሠሙድም ግመልን ግልጽ ታምር ሆና ሰጠናቸው፤ በርሷም በደሉ፤ታምራቶችንንም ለማስፈራራት እንጂ አንልክም። ›› (ቁርኣን 17፡59)
አለህ ጣኦት አምላኪዎች መልዕክቱን ያልተቀበሉበት ግልፅ ምልክቶችንና ተኣምራትን በማጣተቸው ምክንያት ሳይሆን በሌሎች ምክንያት ተፅዕኖ መሆኑን ለነብዩ ሙሓመድ (ሰ.ዐ.ወ) ግልፅ አድርገዋል፡፡ የግብፅ ፍርአውን እና ህዝቡ በነብዩ ሙሳ (ሰ.ዐ.ወ) በኩል ያለምንም ጥርጥር የሚያሳምኑ ምልክቶችና ተአምራት ቢያዩም ምላሻቸው ከመካ ጠኦት አምላኪዎች ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَىٰ تِسۡعَ ءَايَٰتِۭ بَيِّنَٰتٖۖ فَسۡـَٔلۡ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ إِذۡ جَآءَهُمۡ فَقَالَ لَهُۥ فِرۡعَوۡنُ إِنِّي لَأَظُنُّكَ يَٰمُوسَىٰ مَسۡحُورٗا ﴿١٠١﴾ الإسراء:101

‹‹ ለሙሳም ግልጽ የሆኑን ዘጠኝ ታምራቶች በእርግጥ ሰጠነው፤ በመጣቸውም ጊዜ የእስራኤልን ልጆች (ከፈርዖን እንዲለቀቁ) ጠይቅ (አልነው)፤ ፈርዖንም፡- ሙሳ ሆይ! እኔ የተደገመብህ መሆንህን በእርግጥ እጠረጥርሃለሁ አለው። ›› (ቁርኣን 17፡ 101)

አላህም መልዕክቱ ከእሳቸው ሌላ ሌላ  ነብይ የሚያስፈልጋው፤ ከቁርኣንም ሌላ ሌላ ምልክትና መፅሃፍ እንደሚያስፈልገው አረጋግጦላቸዋል፡፡

وَلَقَدْ صَرَّفْنَٰهُ بَيْنَهُمْ لِيَذَّكَّرُوا۟ فَأَبَىٰٓ أَكْثَرُ ٱلنَّاسِ إِلَّا كُفُورًا ﴿٥٠﴾ وَلَوْ شِئْنَا لَبَعَثْنَا فِى كُلِّ قَرْيَةٍ

نَّذِيرًا ﴿٥١﴾ فَلَا تُطِعِ ٱلْكَٰفِرِينَ وَجَٰهِدْهُم بِهِۦ جِهَادًا كَبِيرًا ﴿٥٢﴾ الفرقان:52-50

‹‹ (ጸጋችንን) ይገነዘቡም ዘንድ በመካከላቸው ከፋፈልነው፤ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች ክሕደትን እንጂ እንቢ አሉ። በሻንም ኖሮ የከተማይቱ አስፈራሪን በላክን ነበር። ከሐዲዎችንም፣ አትታዘዛቸው፤ በርሱም (በቁርአን) ታላቅን ትግል ታገላቸው። ›› (ቁርኣን 25፡50-52)

የመደምደሚያ መልዕክት ሰዎች መልዕክቱ በቁርኣን ያመኑ ዘንድ እንዲያነቡት፣ እንዲያደምጡትና እንዲገነዘቡት ጠይቆቸዋል፡፡ ይህ በፅናት የአላህን መልዕክት ለማዳምና ዕውነታ ለመመስከር ፍቀዳኛ በሆኑ ሰዎች ልቦችና አዕምሮዎች ውስጥ ተፈላጊውን ለውጥ ለማስገኘት በቂ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጠማማዎች ምላሽ በእብርተኝነት የተሞላና ጥልቀት የሌለው ነበር፡፡

﴿٤٩﴾ وَقَالُوا۟ لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْهِ ءَايَٰتٌ مِّن رَّبِّهِۦ ۖ قُلْ إِنَّمَا ٱلْءَايَٰتُ عِندَ ٱللَّهِ وَإِنَّمَآ أَنَا۠ نَذِيرٌ مُّبِينٌ

﴿٥٠﴾ أَوَلَمْ يَكْفِهِمْ أَنَّآ أَنزَلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ يُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَرَحْمَةً وَذِكْرَىٰ

لِقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿٥١﴾ العنكبوت:51-50

‹‹ በርሱ ላይም ከጌታው ዘንድ ታምራቶች፣ ለምን አልተወረዱም አሉ፤ ታምራቶች አላህ ዘንድ ብቻ ናቸው፤ እኔም ግልጽ አስፈራሪ ብቻ ነኝ በላቸው።እኛ መጽሐፉን በነሱ ላይ የሚነበብ ሆኖ ባንተ ላይ ማውረዳችን አይበቃቸውምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ሕዝቦች ችሮታና ግሣጼ አለበት። ›› (ቁርኣን 29፡50-51)

አላህ በጥበቡ ንባብን የዑማው ሕይወት የማሽከርከርያ ነጥብ አድርጓል፡፡ በሊቀመልኣክ ጂብሪል ለነብዩ ሙሓመድ በወሕይ የወረደው ቀዳሚው ቃል

ኢቅራዕ (አንብብ) የሚል ነበር፡፡ ለዚህ መልዕክት ያልተማሩት ነብዩ ምላሽ ‹‹ እኔ ማንበብ አልችልም›› የሚል ነበር ከዚያም መላኢካዊ ትዕዛዝ አስተላለፈባቸው፡፡

ٱقۡرَأۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلَّذِي خَلَقَ ۝١ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِنۡ عَلَقٍ ۝٢ ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ۝٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ۝٤ عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ۝٥ العلق:1-5

‹‹ (አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)። አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብዕር ያስተማረ፤ ሰውን ያልወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን። ›› (ቁርኣን 96፡1-5)

እነዚህ አያት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራእይ መቀበል የጀመሩበትና መለኮታዊ ሰብዓዊ ገፅታ ያለቸው ሁለት ትዕዛዛትን የያዙ ናቸው፡፡

ቀዳሚው ትእዛዝ ማንባብ ነው፡፡ ይህም በወሕይ የወረደውን መልዕክት መቀበል፤ መገንዘብና ማወጅ ነው፡፡ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ መለኮታዊ ገጽታ ቁርኣን የአላህ ቃልና ራዕይ መሆኑን የሚያሰይ፣ ይህንንም ለነብዩ (ሰዐወ) በወሕይ የመግለፅ ስልጣን የአላህ መሆኑ፤ይህም በምሉዕ እና ሊደረስበት በሚችል ሁኔታ ለሰው ልጆች እንዲደርስ ታስቦ የተከናወነ፤ሰዎችም እንዲተነትኑት፤እንዲያስታውሱት፤ እንዲገነዘቡት በተከታታይ ሁኔታ እንዲማሩት የተገለፀ ነው፡፡

وَلَا تَعۡجَلۡ بِٱلۡقُرۡءَانِ مِن قَبۡلِ أَن يُقۡضَىٰٓ إِلَيۡكَ وَحۡيُهُۥۖ وَقُل رَّبِّ زِدۡنِي عِلۡمٗا ۝١١٤ طه:114

‹‹ ወደ አንተ መወረዱም ከመፈጸሙ በፊት በማንበብ አትቸኩል፤ ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ በል። ›› (ቁርኣን 20፡114)
ቁርኣን እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡-

وَلَقَدۡ يَسَّرۡنَا ٱلۡقُرۡءَانَ لِلذِّكۡرِ فَهَلۡ مِن مُّدَّكِرٖ ۝١٧ القمر:17

ቁርአንንም ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው ተገንዛቢም አልለን? ››(ቁርኣን 54፡17)

لَا تُحَرِّكۡ بِهِۦ لِسَانَكَ لِتَعۡجَلَ بِهِۦٓ ۝١٦ إِنَّ عَلَيۡنَا جَمۡعَهُۥ وَقُرۡءَانَهُۥ ۝١٧ القيامة:16-17

‹‹ በርሱ (በቁርአን ንባብ) ልትቸኩል ምላስህን በርሱ አታላውስ። (በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡና ማንበቡ በኛ ላይ፣ ነውና።›› (ቁርኣን 75፡16-17)

ስለዚህ ወሕይ (ራእይ) የማሳየት፤የማውረድ፤የመሰብሰብና የመጠበቅ ሓላፊናትና ስልጣኔ የኣለህ ሲሆን የሰዎች ሚና የማንበብ የመማርና የማስተማር ነው ፡፡ በዚህም ሰዎች ነፍሶቻቸውን ያነፁበታል፡፡ ያፀዱበታል፡፡ ይህን ሲያደርጉ ብቻ ነው፡፡ እንደ አላህ ወኪልነታቸው የተሰጣቸውን ሚና የሚያሟሉትና ስልጣኔ ለመገንባት የተሰጣቸው መሰሪያዎች በተግባር ላይ በማዋል ለሰው ዘር ምርጥ ሕዝቦችን የሚያስገኙት፡-

هُوَ ٱلَّذِى بَعَثَ فِى ٱلْأُمِّيِّـۧنَ رَسُولًا مِّنْهُمْ يَتْلُوا۟ عَلَيْهِمْ ءَايَـٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلْكِتَـٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا۟ مِن قَبْلُ لَفِى ضَلَـٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٢﴾ الجمعة:2

‹‹እርሱ ያ በመሐይሞቹ ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርአንን) በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው (ከማጋራት) የሚያጠራቸውም መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የሆነን መልክተኛ (ሙሐመድን) እነስው ውስጥ የላከ ነው፤ እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበሩ። ›› (ቁርኣን 62፡2)

ሁለተኛው ጥብቅ ምክር ሰዎች ለንባብ ትኩረት እንዲሰጡ የሚገፋፈው ትእይንት ዓለሚን እንዲያጠኑና ሁሉም በኣለህ የሚተዳደር የእሱን አንደነት የሚመሰክሩግንኙነቶችና ቅርበቶችን ከእነ ተለያዩ አካለት ጋር እንዲያጠኑ እንዲመረምሩና እንዲያነቡ የተላለፈው ነው፡፡ በእርግጥ መለኮታዊው ገጽታ የሰው አፈጣጠርን ጨምሮ ከሁሉም ፍጥረት ውስጥ በግልፅ የታየና የተመሰከረ ነው፡፡

خَلَقَ ٱلْإِنسَـٰنَ مِنْ عَلَقٍ ﴿٢﴾ العلق:2

‹‹ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)። ››(ቁርኣን 96፡2)

በረጋ ደምና በሰው እና በሕይወትና በሞት መካከል ያሉት ግንኙነቶች ስርዓት በላው ትዕይንት ዓላም ውስጥ ሥራ ላይ ካሉ ሌሎች የመለኮታዊ ሓይል ምልክቶች ውስጥ ተመጣጣኞች አሏቸው፡፡ ከሁሉም በስተጀርባ ያለው ዓላማ ሰዎች ዕውቀት ቀስመው ስልጣኔ እንዲያበረታቱ ማዘጋጀት ነው፡፡ ይህ ክብር በሁሉም ልሳኖችና ቋንቋዎ የተወጀ የአላህ ምህረት ግልጽ ማስረጃ ነው፡፡

وَإِن مِّن شَىْءٍ إِلَّا يُسَبِّحُ بِحَمْدِهِۦ وَلَـٰكِن لَّا تَفْقَهُونَ تَسْبِيحَهُمْ ۗ إِنَّهُۥ كَانَ حَلِيمًا غَفُورًا ﴿٤٤﴾ الإسراء:44

‹‹ ከነገርም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚያጠራው እንጂ አንድም የለም፤ ›› (ቁርኣን 17፡44)

ሌላኛው ዓላማ የህልውና ዓላማና የመፍጠር ዓላማን ማረጋገጥ ነው፡፡

هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلْأَرْضِ وَٱسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا فَٱسْتَغْفِرُوهُ ثُمَّ تُوبُوٓا۟ إِلَيْهِ ۚ إِنَّ رَبِّى قَرِيبٌ مُّجِيبٌ ﴿٦١﴾ هود:61

‹‹እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፤ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፤›› (ቁርኣን 11፡61)

وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾ الذاريات:56

‹‹ጋኔንንና ሰውን ሊገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም። ›› (ቁርኣን 51፡56)
ሁለቱ ንባቦች እርስ በእርሳቸው የተያያዙ፤በቅደም ተከተል የተከሰቱና በአላህ ስም የሆኑ ናቸው፡፡ ተያያዥነታቸው በአላህና በሰዎች መካከል መመሳሰልና ግንኙነትን የመፍጠርና አላህ በወኪሊነታቸው በሚያደርጉት ጥረትና በአኬራም እንደሚያድባቸው ያረጋገጠበት ነው፡-

وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿٤﴾ الحديد: 4

‹‹ እርሱም የትም ብትሆኑ ከናንተ ጋር ነው፤ ›› (ቁርኣን 57፡4)
ሁኔታዎች ሰዎችን ለብቻቸው የሚተዋቸው አይደለም፡፡ አላህ ለጋስና ቸር ነው፡፡ ይልቁንስ ሰዎችን በቁርኣናዊ ንባባቸው ውስጥ የሚመራቸው ነው፡-

ٱقْرَأْ وَرَبُّكَ ٱلْأَكْرَمُ ﴿٣﴾ ٱلَّذِى عَلَّمَ بِٱلْقَلَمِ ﴿٤﴾ عَلَّمَ ٱلْإِنسَٰنَ مَا لَمْ يَعْلَمْ ﴿٥﴾ العلق:3-5

‹‹ አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብዕር ያስተማረ፤ ሰውን ያልወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን። ›› (ቁርኣን 96፡3-5)
እሱ የሰዎችን ድክመት፣የእምቅ ኃይላቸውን ዳርቻዎች፣የዕውቀታቸውን ትንሸናትና የሃሳባቸውን ንፅፅራዊናት አዋቂ ነው፡፡

أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٤﴾ الملك:14

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ እውቀተ ረቂቁ ውስጥ ዐዋቂው ሲሆን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን? ›› (ቁርኣን 67፡14)

يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُخَفِّفَ عَنكُمْ ۚ وَخُلِقَ ٱلْإِنسَٰنُ ضَعِيفًا ﴿٢٨﴾ النساء: 28

‹‹አላህ ከናንተ ሊያቃልልላችሁ ይሻል። ሰውም ደካማ ሆኖ ተፈጠረ። ›› (ቁርኣን 4፡28)

رَّبُّكُمۡ أَعۡلَمُ بِمَا فِي نُفُوسِكُمۡۚ إِن تَكُونُواْ صَٰلِحِينَ فَإِنَّهُۥ كَانَ لِلۡأَوَّٰبِينَ غَفُورٗا ﴿٢٥﴾ الإسراء:25

‹‹ ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም፤ በላቸው። ›› (ቁርኣን 17፡25)

በመሆኑም አላህ አደምን ሁሉንም ስሞች አስተማራቸው፡፡ በእስከሪፕቶም ሰዎችን የማያውቁትን አሳወቃቸው፣አስተማራቸው፡፡ ይህም ሰዎች ቀዳሚውን ንባብ እንዲተገብሩ ብቁ እንደሆኑ ላመስቻል ነበር፡፡ ሁሉም ነገር ለሰዎች ተገዢ እንዲሆኑ አደረገ፡፡ በምድር ላይ እንዲጓዙ አዘዛቸው የማስተዋል፣የማስተንተን የመገንዘብ ክህሎቶችን ሰጣቸው፡፡ ሁለተኛውን ንባብ እንዲያከናውኑ ምልክቶችን ገለፀላቸው፡፡

ሁለቱን ንባቦች በአንድ ላይ ማከነውን በዚህ ዓለምም ሆነ በአኬራ ደህንነትና ሰላም ለማግኘት ቅደመ ሁኔታ ነው፡፡ ሁለቱን ንባቦች መተው ወይንም አንዳቸውን መዘንጋት ወይንም በመሃከላቸው ያለውን ሚዛናዊነት ማዘባት በአላህ መልዕክት ላይ ፊት ማዞር ነው፡፡ የዚህ አስተሳሰብ አስከፊ ውጤቶች ይህችን ሕይወት ከባድ እንድትሆንና ለመኖር አስቸጋሪ እንድትሆን የአኬራ ሕይወትንም የሚያበላሽ ነው፡፡

وَمَنۡ أَعۡرَضَ عَن ذِكۡرِي فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةٗ ضَنكٗا وَنَحۡشُرُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ أَعۡمَىٰ ﴿١٢٤﴾ طه:125

‹‹ ከግሳፄየም የዞረ ሰው፣ ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤ በትንሳኤም ቀን ዕውር ሆኖ እንቀሰቅሰዋለን። ›› (ቁርኣን 20፡124)

በዚህ ሁኔታ ሰው ከወኪልነትና የመስካሪነት ዞፋን የሚሸርና ተገዢ እንዲሆንና እንዲዋረድ ያደርጋል፡-

وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يَتَمَتَّعُونَ وَيَأۡكُلُونَ كَمَا تَأۡكُلُ ٱلۡأَنۡعَٰمُ وَٱلنَّارُ مَثۡوٗى لَّهُمۡ ﴿١٢﴾ محمد:12

‹‹እነዚያም የካዱት (በቅርቢቱ ዓለም) ይጣቀማሉ፤ እንሰሳዎችም እንደሚበሉ ይበላሉ፤ እሳትም ለነርሱ መኖሪያቸው ናት ። ›› (ቁርኣን 47፡12)

أُوْلَٰٓئِكَ كَٱلۡأَنۡعَٰمِ بَلۡ هُمۡ أَضَلُّۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡغَٰفِلُونَ ﴿١٧٩﴾ ألعراف:179

‹‹እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው፤ ይልቁንም እነርሱ በጣም የተሳሳቱ ናቸው፤ እነዚያ ዘንጊዎቹ እነርሱ ናቸው፤ ›› (ቁርኣን 7፡179)
ለሁለተኛው ንባብ ትኩረት ሳይሰጥ በመጀመርያው ንባብ መወጠር እንባቢዎች በምክልትና የመገንዘብ ችሎታዎቻቸውን ስሜቶቻቸውን በከፍተኛ ደረጃ ሊጠቅሙ

የሚችሉ ብዙ ትርጓሜዎችንና ነፀብራቅ ሊያስገኙላቸው ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ግን ወደ መንፈሳዊ እራስን መሳትና ሰው በኸሊፋነቱ እና እንደ ስልጣኔ ገንቢ ካለው ሓላፊነት ጋር በማይገናኙ ጉዳዮች ጊዜውን እንዲያባክን ሊያደርገው ይችላል ፡፡ ይህ በተወሰነ ግላዊ አገባብ ሊታገሱትና ሊገነዘቡት የሚችል ቢሆንም ሰፊ በላ የዑማ ደረጃ ከተከሰቱ እጅግ በጣም ሊወገዝ የሚገባ ነው፡፡ ወይንም እንደ የዑማው የሕይወት ዘይቤ ተቀባይነት ካገኘ ይህ የሰው ጥረት የዋጋ ሃሳብ እንዲዘነጋና ተቀባይነት እንዲያጣ ከማድረግ አንፃር አደገኛ ነው፡፡

የዚህ ዓይነት ፀባይ ከተከሰተ ሰዎች የተወላገደ የሕይወት ዕታና ትርጓሜ እንዲኖራቸውና፣በዓለማዊ ሕልውናቸው ሚናቸው የተዛባ ያደርጋል፡፡ ይህም ሰዎች እዚህ የምድር ላይ ኑሯቸውን  እንደ ሸክም እንዲመለከቱት፣ለመለየት የሚመኙትና እስከታቻለ ድረስ ወደ አኬራ ለመምራት ወደ ሚያመሩበት ያመራቸዋል፡፡

## የተወሰኑ ቁርአናዊ ገፅታዎች

ቁርአን የወረደው እራሰቸውን በቻሉ ክፍሎች ነው፡፡ ከእነዚህ የሕዝብን ልቦች ፣ አዕምሮዎችና ነፍሶች ቁርአናን በወረደበት ወቅት ከተወሰኑ ሁኔታዎችና ክስተቶች ጋር በማዛመድ ለመዘጋጀት የወረዱ አንቀፆች ነበሩ፡፡ ይህ ሕዝብ በቀላሉ እንድገነዘብ፣ የቁርንን ቃላት እንዲየስታውስ፣ ትርጓሜዎችንና መመሪያዎችን በዘላቂነት በሕሊናቸው እነዲቀርጹ የታሰበ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ልቦቻቸው ቁርአንን መለዕክት ለመቀበል ክፍት ይሆናል፡፡ አዕምረቸው ይገነዘባል፡፡ ነፍሳቸው በዚህ ይነቃቃል፡፡ ይነሳሳል፡፡ ሕይወት በሙሉ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህ ኑራቸው እርካታ የለውና ተቀባይነት ወደ አለው ይቀየራል፡፡

በዚህም ሁኔታ ቁርአን ለቀዳሚው ትውልድም ሆነ ከኋላ ለመጡ ትውልዶች መመሪያ፣ ማረጋገጫ እና ሊታመን የሚችል ምንጭ ይሆናል፡-

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَوۡلَا نُزِّلَ عَلَيۡهِ ٱلۡقُرۡءَانُ جُمۡلَةٗ وَٰحِدَةٗۚ كَذَٰلِكَ لِنُثَبِّتَ بِهِۦ فُؤَادَكَۖ وَرَتَّلۡنَٰهُ تَرۡتِيلٗا ﴿٣٢﴾

الفرقان: 32

‹‹ እነዚያ የካዱትም፡- ቁርአን በርሱ ላይ ለምን በጠቅላላ አንድ ጊዜ አልተወረደም? አሉ፤ እንደዚሁ በርሱ ልብህን ልናረጋ፣ (ከፋፍለን አወረድነው) ፤ ቀስ በቀስ መለያየትም ለየነው። ›› (ቁርኣን 25፡32)

وَقُرۡءَانٗا فَرَقۡنَٰهُ لِتَقۡرَأَهُۥ عَلَى ٱلنَّاسِ عَلَىٰ مُكۡثٖ وَنَزَّلۡنَٰهُ تَنزِيلٗا ﴿١٠٦﴾ الإسراء:106

‹‹ ቁርአንንም በሰዎች ላይ በዝግታ ላይ ኾነህ ታነበው ዘንድ ከፋፈልነው፤ ቀስ በቀስ ማውረድንም አወረድነው። ›› (ቁርኣን 17፡106)

ቁርአን የወረደው የሕዝብን ልቦች ሙሉበሙሉ በሚያሸንፍ፣ ነፍሶቻቸውን በሚየስደንቅና በመያስደምምሁኔታ እንደ ተግዳሮትና ተአምር ነው፡፡ ይህ መልዕክቱን እንዲቀበሉ ለማመቻመችና በምሉዕ ህያውነታቸው ምላሽ አንዲሰጡት ነበር፡፡

ቁርአን መሰረታዊ ተፈጥራዊ ሃሳቦችንና አጠቃላይ ደንቦችን የሰው ልጆጅ በሙሉ በሁሉም ቦታና ጊዜ በእያንዳንዱ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ መመሪያዎችንና ዋጋ ያለው ምክር የያዘነው፡፡ ቁርኣን በወረደበት ዘመን በነበሩ ጥቃቅንና ዝርዝሮችና ጉዳዮች የተወሰነ ቢሆን ኖሮ ይህልዩ የጊዜና ቦታ ሁለንተናዊነት አይኖረውም ነበር፡፡ ኋላ የመጡ ትውልዶችም በውስጡ የሚጋጩና የሚለዋወጡ ነገሮችን ያገኙ ነበር፡፡

በዝርዝር የተተነተኑ ልዩ ጉዳዮች በዋናነት በሁሉም ጊዜና ቦታ ሥራ ላይ የሚውሉ የእምነትና ዒባዳ ስነሥራዓቶችን የሚመለከቱ ውርስና የአለፍ ሕዝቦችና አገሮች ቀደምት ታሪኮች ናቸው፡፡ ፈጠራ እንዲህ ሲል ቁርኣንን እንደሚጠብቅ ቃል ገብቷል፡፡

إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ﴿٩﴾ الحجر:9

‹‹ እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡ (ቁርኣን 15፡9)
ቁርኣንን በቀዳሚ ቋንቋው (በአረብኛ ቋንቋ በትርጓሜ ወይንም በማሳተር ማስተላለፍ መከልከሉ) መጽሕፍ አላ ህ ለሰው ዘር የሚሻውን የህይወት ዘይቤ ለመቋቋምና ለመመሥረት ያለውን ችሎታ ለማረጋገጥ ነው፡፡ በሚሌዮኖች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ቀዳም ብሎ በወረደባቸው ምላትና ቅርጽ የመቅራታቸውና የማንበባቸው ጥበብ ይህ ሙስሊሞች ሁሉ ሁሌጊዜና በሁሉም ቦታዎች የሚስማሙበት መሠረት ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው፡፡

በመሆኑም ነብዩና እሳቸውን የተከተሉ አንጋፋ ፍቀሃዎች የቁርኣን እያንዳንዱ ፊደል በመጀመሪያ በሰዎች አዕምሮና ልብ እንዲቀርፅ ከዚያ በኋላ ብቻ ተገልብጦ እንዲፃፍ የወሰኑት ለዚህ ነው፡፡

ይህ ጥበብ በሰሃባና በብዙ ታቢዑን (ሰሃባን የተከተለ ትውልድ) በተናገሩ ሀዲሶች ከቁርኣን ሌላ (ወይንም ጋር) የሌላ የማንኛውም ነገር መገልበጥ የተከለከለው ለዚህ ይመስላል፡፡ ሌሎች ሁሉም ነገሮች በተጨባጭ ትግበራ ከዚህ ጋር የተያያዙ ናቸው፡ ፡ ይህ ከሌላ ከየትኛውም ሐይማኖታዊም ሆነ የሌላ መጽሐፍ ባሕርይ አይደለም፡፡

የቁርኣን ትርጓሜዎች በተመለከተ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እያንዳንዱ አያ በተመለከተ ተፍሲር (ትርጓሜና ማብራሪያ) የመስጠት ዕውቀት አላቸው፡፡ ይሁንጂ እሳቸው ይህንን አላደረጉም፡፡ ዓዒሻ(ረዐ) ‹‹ የአላህ ነብይ ትርጓሜ የሰጡት ጂብሪል ላስተማራቸው ጥቂት አያት ብቻ ነው›› ብለዋል፡፡ እነዚህ አያት ከአካል ገይብ (ከማይታየው) ና በወሕይ ብቻ ሊገነዘቡ ከሚችሉ ጥቂት ሌሎች ጥያቄዎች ጋር የተገነኙ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ልዩ ልዩ የተፍሲር አስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች መብዛት ችለዋል፡፡ በክፍለ ዘመናት ውስጥም ሙስሊም ዑለማዎች ቁርኣንን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመመልከት ችለዋል፡፡ የተወሰኑት ተሳክቶላቸዋለ፡፡ ሌሎቹ አልተሳካላቸውም ፡፡

ቁርኣን ሲወርድ የነበሩ (የተተኩ)አያቶቹ የወረዱበትን የተሰረዙበትንና የተሰረዘ (አል ነስኽ) አያቶችን እንዲሁም አያቶቹን ከእውነተኛ ክስተቶች ጋር የሚያገናኙ ምክንያቶችን የሚያውቁ የነብዩ ሶሃባዎችን በተመለከተ ብዙ ተነግረዋል፡፡ ኢማም አል ጋዛሊ እና ኢማም አል ቁርጡቢ የሚከተለውን ሃሳብ ሰጥተዋል፡- ስለ ተፍሲር በሶሃባዎች የተነገረ ነገር ሁሉ ትክክል ነው ብሎ ማሰብ በሁለት ምክንያቶች ስህተት ነው አንደኛው ነብዩ ተፍሲር የሰጡት በጥቂት አያት ላይ ብቻ ነው….. ይህ የ ዓይሻም አመለካከት ነው፡፡ ሌላኛው በተለያዩ ነጥቦች ላይ በሚሰጧቸው ተፍሲር እርስ በእርሳቸው ልዩነት አለ፡፡ እነኚህ ልዩነቶች ሊታረቁ የማይችሉ እና ሁሉም ከአላህ ነብይ የመጡ ናቸው ማለት አይቻልም-የተወሰኑት ሊሆኑ ቢችሉም፡፡ [1]

---

1.ሸይኽ ሙሓመድ አል ጣሂር ኢብን ዓሹር፤ተፍሲር አል ተሕሪር ወ አል ተንዊር (ቱኒስ፡-አል ዳረ አል ቱኒሲያ፤1984) ገፅ 28-9 ፡፡

እዚህ የቀረበው ሃሳብ የአዕምሮ የማሰብ ችሎታ ስለ ቁርኣን የሚኖር ግንዛቤን ፣ ትርጓሜዎችን በተወሰነ ጊዜ ወይንም ከተወሰነ ትውልድ ጋር ብቻ ‹‹ ማሰር›› እንደማይገባ የሚጠቁም ነው፡

በእርግጥ ሙስሊሞች ወደ ፈጣሪያቸው ላመቅረብ ከሚቻልባቸው እጅግ በጣም ውጤታማ መንገዶች አንዱ ቁርኣን ማንበብና በአያቶቹና ትርጓሜዎቹ ላይ በጥልቀት መመርመር እና ማሰላሰል ነው፡፡ ግንዛቤ የሌለበት ንባ ወይንም ማሰላሰል የሚፈቅድ ነው ለማለትም አይቻልም፡፡ ፍቀሃ ማገናዘብ እና ማሰላሰል ያለው ጥቂት ንባብ ማሰብ ወይንም ማሰላሰል ከሌለበት ብዙ ንባብ የተሸለ መሆኑ ላይ ስምምነት አላቸው እዚህ ማሰላሰል ስንል አያን መቅራት፣መከለስ የያዘውን ትርጓሜዎች በተቻለ መጠን ለማወቅ ትኩረት ማኖር እና አላህ ለተወሰኑ ልዩ የአዕምሮ ችሎታና ግንዛቤ ለሰጣቸው ሰዎች ለሚገለጥ ድብቅ ትርጓሜዎችና ፍችዎች ላይ ለመድረስ ሃሳብን በነፃነትና ያለ መደነቀፍ ማኝሸራሸር ማለታችን ነው፡፡

ቁርኣን እንደ መለኮታዊ ወሕይ (ራእይ) ለሁሉም ዓይነት ዕውቀት ከሁሉም በላይ አስተማማኝ ምንጭና የሰብዓዊናት የዕውቀት ዘርፎችና ማሕበራዊ ሳይንሶችን ለሚያጠኑ ምሁራን እውነተኛው መመርያ ነው፡፡ የአንድን ሰው ሳይንሳዊ ደመነፍሶች የሚያነቃቁና የሚመሩ አጠቃላይ ሳይንሳዊ መጠቆሚያዎችና ማሳያዎችን የያዘ ነው፡፡ እንደ አለመታደል ግን ብዙ ሙስሊሞች ለረጅም ዘመን ቁርኣን በቀናነት የአለፍ ሕዝቦች ታሪኮች፣ታሪኮቻቸው ለተግሳፅና ለማስጠንቀቂያ የሚነገረ በተጨማሪም የአኬራና የድብቅ ገፅታዎቹነ የፍቂህ ህግጋት መናሻ የመረጃ መፅሓፍ ነው፡፡ የሚል አመለካከት ይዘው ቆይተዋል፡፡

አምሳያ በሌለው ተኣምራዊ ስነ ግጥማዊ የቋንቋ፣የዘይቤ እና ስና ፅሑፋዊ ልዕልናና ግርማ-ሞገስ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው ነበር፡፡ ይህ የቁርኣን ልዩ ባህርይ በእርግጥ የአረብኛ ቋንቋ ሊጎነፀፍ የሚችለው ከፍተኛውን ጫፍ የሚወክል፣ከዚያ በፊት በአረብኛ ዘይቤ ውስጥ በማይታወቅ ሁኔታ ቋንቋው አገልግሎት ላይ የዋለበት ነው።

በእርግጥ የእነ አል ሩማኒ፣አል በቂላኒ፣አል ጁርጃኒ፣አል ቃዲ አያድ እና የሌሎችም ዑለማዎች ስራዎች እንደሚያመለክት በቀደምት ትውልዶች የተከነወኑ የቁርኣን ተኣምራዊ ልዩ መግለጫዎችን በተመለከተ የተከሄዱ ጥናቶችና ምርምሮች ከሞላ ጎደል እነዚህ ሶስት ገጽታዎች ጋር የተወሰኑ ነበሩ፡፡ ቁርኣን እንደ ፍቅህና ሕግ

ማረቀቂያ ምንጭ ብቻ የሚታይበት ጊዜ ነበር ይህ ቁርአንን በ200 እነ 500 አያት ብቻ የሚገደበው ነው፡፡ የተቀረው የቁርኣን ይዘት ለመገሰጫ እና ለማስጠንቀቂያ፣ ለፀባይ ማሻሻያና ለምክርየተካተተ ብቻ ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡ እነኚህ መገደቢያዎች የቁርአንን ተአምራዊነት በውብ የንግግር ደረጃ ብቻ ከመወሰናቸውም በላይ ሁሉም ጊዜና ቦታ የሚታደሱና የሚተገበሩ ገፅታዎችን ለመፈለግ የሚደረገውን ታላቅ ጉጉት የሚያግድ ነው፡፡ እነኚህ ገፅታዎች ቁርአንን ተአምራዊ ተፈጥሮ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡

የተከበረ፣ ከጊዜወ ጋር የሚሄድ ኢስላማዊ የሕይወት መስመር በመከተል ኢስላማዊ ተሃድሶን ማስገኘት ስለምንፈልግ የፊቅህ ሕግጋት ከቁርአን ይዘት በጣም ትንሽ ክፍል ብቻ እንደሚሸፍን ማወቅ አለብን፡፡ ሙስሊሞች ሁሉንም የቁርአንአያት ለመገንዘብ እና ለማስተንተን አዕምራዊ ዕውቀትታቸው መጠቀም እንደሚገባቸው መገንዘብ አለብን፡፡ በሰብዓዊ ወጥራ (አብሮ የተፈጠረ ተፈጥሮ) እና በማህበራዊና የትግበራ ሳይንሶች የመጀመሪያ ምንቾቻቸውና የሁሉም ዕውቀት መሠረት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በየትኛውም የዕውቀት ዘርፍ ያሉ ልዩ ክህሎት ያላቸው ሙስሊሞች ለፈጠራ የላቸውን ፍላጎት ለማነሳሳትና ለመመሪያነት ወደ ቁርኣን መመለስ ግዴታ ነው፡፡

የአላህን መፅሓፍ በንቃትና በተፈኩር ማንበብ የዕውቀት መጋዘናቸውን ለማሻሻል ለማበልፀግና ቅርፅ ለማስያዝ የሚያስችላቸው ነው፡፡ ይህ ሙስሊሞች እውነተኛውን የቁርኣን ዑማ መልሰው እንዲገነባ ኃይል ይሰጣቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ደረጃ ላይ ከመድረሳችን በፊት ልናከናውናቸው የሚገቡን ብዙ ነገሮች አሉ፡፡

እንደ መናሻ የቁርኣን ተኣምራዊ ተፈጥሮ ላይ የተሰሩ ጥናቶችና ምርምሮች እንደገና መገምገም ይኖርባችዋል ይህ ዘመናዊ ሙስሊሞች በተለምዶ እንደ ተአምር ከሚቆጠር የቁርኣን ገፅታዎች ላይ ተጨማሪ ባሕሪያትን የሚያስገኝ ነው፡፡ ልዩ ፍላጎት ሊሰጣቸው ከሚችሉ ቦታዎች መካከል ቁርኣን በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ያለው ተፅዕኖ፣የተራቀቀ የሰው ዘር እና በየትኛውም ጊዜና ቦታ ምርጥ ቤተሰብ ለማስገኘት ያለው ችሎታው እና በማህበረሰብና በሀገሮች መፈጠር ላይ ያለው ተፅዕኖ ይጠቀሳሉ ሙስሊም የስነ ልቦና ምሁራንና የስነሰብ፡፡ሙስሊም የስነ ልቦና ምሁራንና የስነ ሰብ ምሁራን ይህ ሊመራመር የሚገባ ኢትራፍ ዘርፍ እንደሆነ ደርሰውበታል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ሙስሊም የትግበራ ሳይንቲስቶችና ሌሎች

ምሁራንም በቁርኣን ውስጥ ዋጋ ያለው ዕውቀት ማግኘት ይችላሉ፡፡ ሙስሊም አስሊዎችና ዑለማዎች ለተከበረ ሰብዓዊ ሕይወት እንዲሁም ፍትሓዊ ለመገንዘብ ቀላ የሆኑና ለመተግበር የሚመቹ ትክክለኛ መሠረት ለመፍጠር የሚችሉ የአህካም (ሕግጋትን ) ህግ የማውጣት የእውቀት ዘርፎች የቁርኣንን ታአምራዊ ተፈጥሮ መመርመር ይችላሉ፡፡

በሁለተኛ ምዕራፍ ቁርኣንን ከማንበብና ከመተርጎም በስተጀርባ ያሉ ዓለማዎች ደግም መጤን ይገባቸዋል ይህ ዕውቀትን ከማግኘት ሶስቱ ዓላማዎች  ቀደምት ሕዝቦችና ሀገሮችን አኬራንና የፍቅህ ህግጋትን ከማወቅ ታልፎ ሊከናወን ይገባል ሌሎች አስፈላጊ ዓላማዎችም አሉ ፡፡ ይበልት አስፈላጊዎቹ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1.በሰብዓዊ ጉዳዮች ግለሰባዊና ማሕበራዊ ባሕሪን እንዲሁም ፈጣሪን በሚያጠኑ ሳይንሶች ላይ አጠቃለይ መመርያ ለማግኘት፡፡

2.ሕብረተሰቡን ለማደስና ፖለቲካዊ ስርዓትን ለማደስ የሚያስችሉ መሠረታዊ ደንቦችና መመርያዎችን በተመለከተ ዕውቀት ለመግኘት፡፡

ይህ ሰብዓዊ ማሕበራዊ ተፈጥሮ እና ተህድሶ በሚገኝበት መንገድ ስምምነት በለው ሁኔታ የሚከናውን ነው፡፡

ሁሉንም ማሕበራዊ ሳይንሶች በእዚህ ሁለት ዓለማዎች ስር መመደብ እንችላለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ቁርኣን ለሁሉም ሳይንቲስቶች ምሁራን አስተማመኝ ማጠቀሻ እና የኖራል ጠራት መለኪያ ይሆናል፡፡ ይህ ማጠቀሻ ይዘቱ በፍፁም ጊዜ ሊያልፍበት የማይችል ነው፡፡ በማህበራዊና የትግበራ ሳይንሶች በስነ-ፅሁፍ ወዘተ ያሉ እስፔሻሊስቶች ዕለት ተዕለት ክንውኖቻቸው የሚያመክሩት ጠቃሚ ምንጭ ይሆናል ይህ ማለት ሙስሊሞች ቁርኣንን ከአሁኑ ጊዜ አያያዛቸው በተለየ ሁኔታ ሊንከባከቡት ይገባቸዋል፡፡ የአላህን ፀጋ ለመግኘት ወይንም የተወሰኑ ህግጋትን ለማወቅ በማሰብ ከሚያነቡት ሁኔታ በተለየ ትኩረት ሊያነቡት ይገባቸዋል፡፡

እዚህ ላይ ሁለቱን ትርጓሜዎች ማለትም አል ተፍሲር ቢ አል መዕሱር (ከነብዩና ከሶሃቦች በተገኙ ሀዲሶች ላይ በመመርኮዝ ከሚከነውን ተፍሲር) እና ከ አል ተፍሲር ቢ አል ራዒ(አዕምሮን በነፀፃነት በማሰራት ሚከነውን ተፍሲርን) በተመለከት ከሚነሳ አስፈላጊ ጥያቄ ምላሽ መስጠት አለብን ፡፡ ይህ ጉዳይ ትኩረት የሚስበው የዛሬ ዑለማዎችና ምሁራን መደምደሚያዎቻቸውና ተርጓሜዎቻቸውን

ለመደገፍ ብዙን ጊዜ ከነብዩና ከሶሃቦች የተገኙ ከንውኖች ልምዶችን ስለሚያገኙ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ንግግሮቻቸው ከግል አስተያት ባለፈ በተሸለ ማረጋገጫ ላይ የተመሰረተ አይሆንም፡፡ እነዚህ እውነተኛ ሃዲሶች የሚገለፁት ይህንኑ ነው፡-

ቁርኣንን በእርሱ አስተያየት ላይ በመመስረት የሚተረጉም በጀሃነም እሣት ውስጥ ስፍራውን ያገኛል፡፡ [1]

ያለ ዕውቀት ቁርኣንን የሚተረጉም በጀሃነም እሣት ውስጥ ስፍራወን ያገኛል፡፡ [2]

በእርሱ አስተያየት ላይ በመመርኮዝ ቁርኣንን የሚተረጉም ትርጓሜው ትክክል እንኳን ቢሆን የተሳሳተ ነው ፡፡ [3]

---

1.በትርሚዚ የተዘገበ፡፡

2. በትርሚዝ የተዘገበ፡፡

3.በትርሚዝ እና በአቡ ዳውድ የተዘገበ ፡፡

አሁን ጥያቄው፤ቁርኣንን በግል አስተያየት ላይ በመመስረት መተርጎም የሚከለክሉ ሀዲሶች በሉበት ሁኔታ አል ተፍሲር ቢ አል ራዒን መደገፍ እንዴት ይቻላል የሚለውን ነው፡፡ በእርግጥ ከሰሃበዎችና ታቢዑን ብዙዎቹ በሱንና ከልተደገፈ የትርጓሜ ንግግሮች ከመስጠት የተቆጠቡ ናቸው ይህ ከሆነ በየትኛውም የዕውቀት ቅርንጫፍ ያለ ቀራጥ ሙስሊም ተመራማሪ የቁርኣን አያትን ለመተርጎም የራሱን /የራሶን ምክንያታዊናት እንዲተገብር ወይንም እንዲተገበር እንዴት መጠበቅ እንችላለን ይህ ትልቅና ጥንቃቄ የሚሻ ጥያቄ ቢሆንም የሚከተለውን ለስተዋለ ምላሹ ግልፅ የሚሆን ነው፡፡

ከአል ተፍሲር ቢ አል መዓሱር ከነብዩ የተለለፈልን ቅፅ ውስን መሆኑን ቀደም ብለን ገልፀናል፡ጥበብ ሊያመለክተን የሚመስለው የሙስሊም በመሆኑም የአዕምሮ ችሎታ የቁርኣን አያት ለመገንዘብ በሚደርግ የማስተንተን፣የተፈኩር (በጥልቀት የማሰብ) ና ምክንያት ከሏቸው መደምደሚያዎች በኩል የሚከናወኑ ጥረቶች እንዲቀጥሉ መፍቀድ አለበት፡፡

በየዘመኑ በርካታ የተፍሲር መፅሓፍት መፃፋቸውና ህግጋትንም ሆነ ሌሎች ያየዙ አያትን በተመለከተ የቁርኣን ትርጓሜዎችንና ፊችዎችን ለመገንዘብ የተፍሲር ሁለማዎች የተለያዩ ሰፊ አቀራረቦችን መከተላቸው ይታወቃል፡፡

ፈኺር አል ዲን አል ራዚ (በ606 ዓመተ ሒጅራ የሞቱ) ቢፈልጉ ፈሱር አል ፋቲሃን የአንድ ግመል ጭነት ተፍሲር ማዘጋጀት እንደ ሚችሉ ይናገሩ ነበር፡፡ በዕውነትም ለእኛ የደረሰን የእሳቸው የዚህ ሱራህ ተፍሲር አንድ ትልቅ ቅፅ የሚሆን ነው፡፡ እንደ ኢብን ዐቲያ ፣አልቁርጡቢ፣ኢብን አል ሰበግ እና ሌሎችም ያሉ ብዙ ዑለማእ ከአንድ አያ ትርጓሜ መምዘዝ ወይንም በአንድ አያ ላይ በአስር በመቶዎች የሚቆጠሩ የምርምር ጥያቄዎችን ማሰናደት ሚችሉ ነበሩ፡፡

በእነዚህ ሁኔታዎች የሚነሱ አደዲስ ጥያቄዎችና ከትእይንት ዓለም ሕግጋት ስልጣኔ ንድፎች ወዘተ ጋር የተገናኙ ሚመጥኑ ጉዳዮች ቁርኣንን ከሌሎች መለኮታዊ መፅሓፍት መካከል የተለየ የሚያደርጋው ነው፡፡ ይህ ቀደም ተብሎ ያልተጠቀሰው ውይንም በእርሳቸው በነብዩም ያልተብራራ ነው፡፡ ይሁንጂ ሌሎች ዑነላመዎች እና የተፍሲር ምሁራን ለአብራራዎች ትክክለኛ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ቁርኣንን በዚህ መንገድ መቅረብ አልከለከሉም፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በአል ጠይብ አገለለፅ ተፍሲር (ከኪታቡ) እውነታኛ ቃለት ጋር መስማማት ያለበትና ከጥራዝ ነጥቅነት፣ የውሸት ባህሪይ ተገቢ የቃለት መጠን ከመጠቀምና ከአሰልቺነት ነፃ መሆን አለበት ፡፡

---

1.ሸይኽ ሙሓመድ አል ጣሂር ኢብን ዓሽር ተፍሲር አል ተህሪር ወ አል ተንዊር፣ ገፅ12

---

ስለዚህ በግላዊ አስተያየት ላይ ተመርኩዞ የሚሰጠን ተፍሲር በሚከለክሉ ሀዲሶች ሁኔታ እንደ ቢድዓ የሚቆጠር  ትርጓሜ ከሚከተሉት ምድቦች በአንድ የሚመደብ ይሆናል

1.ለዐረብኛ ቋንቋ የለቀ ልዕልና፣ለዘይቤዎቹና ለሸሪዓ ዓለማዎች ለለስርዝ ጥያቄና ለተሰረዙ አያት እና ከአንድ የተወሰነ አያ ወይንም አያት በስተጀርባ ለአሉ ምክንያቶች ሁነኛ ትኩረት ሳይሰጥ በግላዊ አመለካከት ላይ የተመሰረተ ተፍሲር የዚህ ዓይነት ያልታሰበበት ተፍሲር ግምታዊና እውነት እንድትበለፅግ የሚፈይደው ነገር የለውም፡፡

2.ሃሳብና በጥልቀት የተመረመረ ማሰላሰል ያየዘ ግን ከአያው ጋር የተያያዙ ምክንያቶች በተፍሲር በለሙያዉ ድክመት ስላልተካተተ ጉደለት ያለበት ተፍሲር፡፡ በዚህ ዓይነት ተፍሲር ተንታኙ/ኟ መደምደሚያውን ወይንም መደምደሚያዋን

የሚመረኮዘው ካቃላት ግልፅ ትርጓሜዎች ላይ ነው ወይንም ከትርጓሜና በከፊል ገፅታ ሲሆን ይህ የታሰበ ብቸኛው ትርጓሜ እንደሆነ ይወሰዳል፡፡

3.የመጨረሻው ምድብ ተርጓሚዎች የአንድ የተወሰነ የአስተሳሰብ ምድብ ወይንም ቡድን ክፍፍል ወይንም አዝማሚያ ተከተዮች ሆነው የተወሰኑ የቁርኣን አያትን ስነ ልሳናዊ ትርጓሜዎች እና /ወይንም አያቶች የወረዱበትን የወቅቱን ሁኔታዎች ያላገነዘበ ከቡድኑ አባላትና ተከታዮች አዝማሚያ ጋር በሚስማማ ሁኔታ የተዘጋጀ፡፡ ለምሳሌ የበያንያ ጀምዓ፡-

هَٰذَا بَيَانٌ لِّلنَّاسِ وَهُدًى وَمَوْعِظَةٌ لِّلْمُتَّقِينَ ﴿١٣٨﴾ آل عمران:138

‹‹ይህ ለሰዎች ገላጭ፤ለጥንቁቆች መሪና ገላጭ ነው፡፡ ›› (3፡138) የሚለውን አያ በ119 ዓመተ ሂጅራ የተገደለው መሪያቸውን በያን ቢን ሰምዓን አል ቲሚሚን እንደሚያመለክት ይተረጉማሉ፡፡ ቀዲያኒያ፡-

وَمُبَشِّرًا بِرَسُولٍ يَأْتِي مِنْ بَعْدِي اسْمُهُ أَحْمَدُ ﴿٦﴾ الصف:6

‹‹ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ››(61፡6)

የሚለውን አያ ጉላም አሕመድ ቀዲያኒን እንደሚገልፅ ይተረጉማሉ፡፡ ባጢንያ ቁርኣን ውጫዊና ድብቅ ፍቺ እንዳለው ውጫዊው ፍቺ ሙስሊሞች የሚገነዘቡት ድብቅ ፍቺው እራሳቸው ለስበሰቧቸው ከአለፍ ፍልስፍናዎች ጥንታዊ ሓይማኖታዊ እምነቶች ወይንም ከልዩ ልዩ መሪዎቻቸው የተገኙ አሳሳች እምነቶችና ጣኦታዊ አምልኮዎችን ለመደገፍ የሚጠቁሙት ነው፡፡ ትክክል አለመሆናቸውን ለሚከራከሩ ሰዎች ትርኪሚርኪ ሃሳቦቻቸው በቁርኣን ውስጥ ያሉ ‹‹ ድብቅ ፍቺዎችን›› ይሰጣሉ የዑማው አንጋፋ ምሁራን ግን ዚህን አዝማሚያ ስህተትነት ለማረጋገጥና ክፉ ዓላማዎቹን ለማጋለጥ ችለዋል፡፡

ሌለው ‹‹ ምልክቶች ›› ወይንም ዛሬ ‹‹ ተምሳሌትነት›› የሚባለው አስተሳሰብ መኖር ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ለምሳሌ አንድ አያ ተምሳሌታዊ ፍቺ እንዳለው ሊታሰብ ይችላል ይህም ወዲያው ወደ አዕምሮ የማይመጣና በቋንቋው በቀጥታ ያልተጠቀሰ ሃሰብ የሚወክል ሊሆን ይችላል፡፡ የሚከተለውን እነስተውል፡-

وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن مَّنَعَ مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ أَن يُذْكَرَ فِيهَا ٱسْمُهُۥ وَسَعَىٰ فِى خَرَابِهَآ ۚ ﴿١١٤﴾ البقرة:114

‹‹ የአለህንም መስጊዶች በውስጣቸው ስሙ እንዳያወሳ ከከለከለና እርሳንም በማበላሸት ከሮጠ ሰው ይበልጥ በዳይ ማነው ? ›› (ቁርአን 2፡114)

እዚህ ላይ መስጂድ ‹‹ልቦችን›› ይወከላል የሚል ትርጓሜ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ይህም ልቦች ለአላህ የመታዘዝ ቦታዎች ስለሆኑ ነው፡፡ ህ ፍቺው ስነ ልሳናዊ ድጋፍ በአጠቃላይ የሌለው ትርጓሜ ነው፡፡ ይሁንጂ ትክክል እንደሆኑ የሚታሰቡ ሶስት የትርጓሜ ዘዴዎች አሉ ፡-

1.ቃለት ግልፅ ፍቺዎች ግንዛቤ መወሰን፡፡

2. በቃለት ግልፅ ፊቺዎችን የቀረቡ ሃሰቦች ላይ በማገናዘብ ዕውነተው ላይ መድረስ የሚቻለው በችሎታ ባላቸው የተፍሲር ባለሙያዎች ጥንቃቄ ማሰብ በኋላ የሚከነውን ነው፡፡ በስነ ልሳናዊ አስተውሎቶች ከአጠቃቀም ጋር በላቸው መስተዳምር ላይ በመመስረትና ከቁርአን ዓላማዎችና ግብ ሳያፈናግጡ የሚደረስበት ነው፡፡

3.የተፍሲር ባለሙያው ዕወቀታዊ፣ሳይንሳዊና ባሕላዊ የራሱ ዘመን ምንጮችን በመጠቀም አያቶችን ለመተንተን ከቁርአን ማመለከቻዎች ጋር ያለቸውን አብሮነት ለማየት ሲፍለግ ፡፡ በዚህም እነዚህ የእውቀት ዘርፎች በአያው ውስጥ በጠጠቀሰው ፍቺዎች ብርሃን ለማስተካከል ሊወስን ይችላል፡፡

يُؤْتِى ٱلْحِكْمَةَ مَن يَشَآءُ ۚ وَمَن يُؤْتَ ٱلْحِكْمَةَ فَقَدْ أُوتِىَ خَيْرًا كَثِيرًا ۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّآ أُو۟لُوا۟ ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿٢٦٩﴾ البقرة:269

‹‹ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፤ ጥበብንም የሚስሰጥ ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጠ፡፡ የአእምሮዎች ባለቤቶች እንጂ (ሌላው) አይገሰጽም፡፡ ›› (ቁርአን 2፡269)

አንድ ዘመናዊ የኢኮኖሚ ሊቅ

كَىْ لَا يَكُونَ دُولَةًۢ بَيْنَ ٱلْأَغْنِيَآءِ مِنكُمْ ۚ ﴿٧﴾ الحشر:8

‹‹ከናንተ ውስጥ በሀብታሞቹ መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን ›› (ቁርአን 59፡7)

የሚሉ የአላህን ቃለትን ሲገነዘብና ከዚህ በፊት የሀብት አፈጣጠርና አስረጫጨትን በተመለከተ በሙስሊሙምሁራን ያልተጠቀሰ ሃሰብ ቢያቀርብና ይህም ለህዝብ መልካም ነገር የሚሰራበትን መንገድ ቢያሰይ ይህ ሃሳብ ከዚህ በፊት ስለልተናሳ ወይንም በ ሀዲስ ያልተደገፈ ነው በሚሉ ምክንያቶች ተቃዎሞ ሊገጥማው አይገባም ። ይሁንጂ ዑሱሊዩን[1] ዐረብኛ ቁርኣን በወረደበት ወቅት ከያዙት የመጀመርያ (አስሊ) በስተቀር ሌላ ፍቺ ላይ ማፈላለግ እንደማይፈቀድ አቋም አላቸው፡

---

1.ዑሱሊዩን ፡ ‹‹ መሠረታዊያን ›› ወይንም ‹‹ ግብረገብነትን አጥባቂዎች ›› የሚለው መጥፍያ አይገልፃቸውም፡፡ ትክክለኛው ቃል ‹‹ ሁሉም ነገር ትክክልና ንፅሁ መሆን አለበት›› የሚለው ሲሆን የቁርኣንና የሱንናን ባህላዊ ትርጓሜዎች የሚከተሉና ከኢጅቲሃድ የሚቆጠቡ ናቸው፡፡

የእነርሱ አቋምም በብዙ ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ለውይይት ግን ክፍት ነው። አል ሻቲብ እንዲህ ይላሉ ፡-

አንድ ‹‹ የመሃያማን ሽርዓ ›› (ዑምሚያት አል ሽርዓ )የተገኛ ነገር በሕዝብ - ዐረቦችን ለማለት ነው፡፡ እንዲተገበር ተቀባይነት ከገኙ መመሪያዎች ይገኙበታል፡፡ የዚህ አንደኛው ብዙ ሰዎች ለሁሉ ነገር ከቁርኣን መፍትሔ ለማግኝት ርቀው በመሄድ ወሰኑ ከስነ ልሳን፣ስነ ኣመክንዩ፣ስነ-ፍቺ ወዘተ በተጨማሪ ከኖረበት ዘመንና በቀደምት ትውልዶች ዘንድ የሚታወቁ ሁሉንም ተፈጥሮአዊ ሳይንሶች እንዲያጠቃልል ያደርጋሉ፡፡ ይህ ግን ቀደም ብለው ከነበሩ ልምዶች ጋር አይገጥምም፡፡ የተከበሩ ቅደመ አያቶቻችን በቁርኣን ዕውቀት፣በሳይንሶችና በይዘቶቹ በጣም ከፍተኛ ክህሎት የነበራቸው ቢሆንም ማረጋገጫ ከገኙ ትእዛዛትና ከአኬራ ጋር ከተያያዙ ሕግጋትና መርሆች በስተቀር ስለ ሌላ ነገር ሃሰብ ሲያቀርቡ አይሰማም፡፡ አዎ ቁርኣን ዐረቦች ያወቋቸው የነበሩና የለመዷቸው ሳይንሶችን የበለጠ ኃይለኛ የማሰብ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ሳይሆን አስተዋዮችን በሚያስደንቅ ሁኔታ ያከተተ ነው፡፡[1]

---

ሽይኽ ሙሓመድ አል ጣሀር ኢብን ዐሹር፣ተፍሲር አል ተሕሪር ወ አል ተንዊር፣ ገፅ 44 ፡፡

---

የአል ሻቲብ አስተያየቶች ቁርኣን የህግጋት ማውጫ ምንጭ እና ላልሰለጠና ሕዝብ ለዐረቦች የተለከ መልዕክት ብቻ ነው፡፡ በሚል ሃሰብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

በመሆኑም ቁርአነዊ ሃሳቦችና ንድፍ በዐረቦች የራስቸው የማስተዋል ችሎታ የሚወስን ነው፡፡ ቁርአን የወረደው ለሁሉም ጊዜና ቦታ ለመላው ዓለም የምክርና የመመርያ መፅሓፍ ስለሆነ ይህ ከ ዑሱሊ ከፍተኛ ስህተቶች አንዱ እንደሆነ የብዙ ሰዎች እምነት ነው፡፡ የዐረብኛ ቋንቋ ካለው ስፋትና ብልፅግና አኳያ የቁርኣንን ፍቺ ለመሸከም ምቹ ቀዋንቋ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የዐረብ አዕምሮ በስነ-ልሳነዊም ሆነ በሌሎች እነዚህ ፍቺዎች ላይ ሁሉ ብቸኛ ስልጣንና ኃይል አለው ማለት አይደለም ፡ ፡ በተጨማሪም በዚህ አጭር ጥናት ለመዘርዘር የማይቻል ዐረቦች በፊት የሚያውቋቸው ወይንም ያላስተዋሏቸው ብዙ ነገሮችን የያዘ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

تِلْكَ مِنْ أَنبَاءِ الْغَيْبِ نُوحِيهَا إِلَيْكَ ۖ مَا كُنتَ تَعْلَمُهَا أَنتَ وَلَا قَوْمُكَ مِن قَبْلِ هَٰذَا ۖ فَاصْبِرْ ۖ إِنَّ الْعَاقِبَةَ لِلْمُتَّقِينَ ﴿٤٩﴾ هود:49

‹‹ይህቺ ከሩቅ ወሬዎች ናት፤ ወደ አንተ እናወርዳታለን፤ አንተም ሕዝቦችህም ከዚህ በፊት የምታውቋት አልነበራችሁም፤ ታገሥም፤ ምስጉን የሆነችው ፍጻሜ ለሚጠነቀቁት ናትና፡፡›› (ቁርኣን 11፡49)
በወሕይ ዘመን የነበሩ ዐረቦች የተነገራቸው በሚገባቸውና በሚረዱት መንገድ ነበር በኋላ ግንዛቤ ሊስፋፋ አዳዲስ ክስተቶችና ተፅዕኖዎች በቁርኣን ውስጥ ተገለፁ፡፡ ብዙ የማይወስኑ ፊችዎችም ተጨመሩ፡፡ ይህ በእውነት ከቁርኣን ተኣምራዊ ተፈጥሮ እንደ አስፈላጊ ገጽታ ነው። በተላይ በዘመናት ውስጥ አንድ ብቸኛ መጽሓፍ በአግባቡ ተስተውሎና አንድ አይነት ቃላትና ፊደላት ይዞ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ምላሽ መስጠት መቻሉ የቁርኣንን ተኣምራዊ ተፈጥሮ መግለጫ ነው፡፡ በቲርሚዝ የጠዘገበ ዐሊ ኢብን አቡ ጣሊብ ያስተላለፉት ሀዲስ፡- ‹‹የቁርኣን ድንቆች ፍጹም አይቋረጡም›› ይላል፡፡ በቁርኣን የተገለፁ ስነ-ልሳነዊ ፍቺዎችን አልፎ መሄድ አይፈቀድም ማለት የቁርኣን ድንቆች አላቂና በጊዜና በቦታ የሚወሰኑ ናቸው እንደማለት ነው፡፡ አያቶቻችን አንድን አያ ወይንም አያት በተመለከተ አንድ የጠወሰነ ነገር አለመጥቀሳቸው ማብራራት የተከለከለ ነው ማት አይደለም ፡፡ ይህ የሚያመለክተው የእነርሱ ትርጓሜ ትኩረት በለሙያ በሆኑባቸው ቦታዎችና ትርጓሜ ባስፈለገባቸው ቦታዎች ነበር ፡፡ እነርሱ ያልደረሱባቸው ቦታዎችን አለማጥናትን በግልፅ የሚያመለክት አይደለም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ያሉ መግለጫዎችና ማረጋገጫዎች በቁርኣንና በልዩ ልዩ ሳይንሶች መካከል ያለው ግንኙነት በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

1.ከቁርኣን የተወሰዱ ሳይንሶች አሉ እነርሱም ተውሂድ ተሽሪዕ (ሕግ) እና ዑሱል(የሐግ ፍልስፍና ሳይንስ ምንጮች ) ናቸው፡፡

2.እንደ ቋንቋ ሳይንሶችና በላጋህ (የንግግር ጥበብ በተለይ በውብ ቃለት አስተሳሰብን የሚቀይር ንግግር) ያለ በዚህ ላይ የተመሠረቱ ሌሎች ሳይንሶችም አሉ፡፡

3.በቁርኣን ውስጥ የተጠቀሙ ቁረኣንን ለመረዳትና በቁርኣን ላይ የሚኖር እምነትን ለማጠነከር የሚረዱ ሳይንሶች አሉ፡፡

4.በመደምደሚያ ከቁርኣን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ሳይንሶች አሉ፡፡ በመሆኑም ወቅቱን የሚመጥኑ ኢስላማዊ ማህበራዊ ሳይንሶች ሰብኣዊ ሳይንሶች በመቋቋም የኢስላማዊ አስተሳሰብ ስነ-ዘዴዎች ለማሻሻል እና ኢስላማዊ የባህል ሥርዓትን መልሶ ለመገንባት ኃይሎች ማነሳሰት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ሂደትም ሳይቆጠር ዋነው ዓላማ እነዚህ የዕውቀት ዘርፎች ከቁርኣንና ከነብዩ ሱነን ጋር በአራት መመርያዎች ላይ ተመሥርተው በተወሰነ ዕቅድ የሚገነኙበትን የበለጠ ምርጥ ዘዴ ማግኘት ይሆናል፡፡

ከእነኚህ መርሆች ቀዳሚውና እጅግ በጣም ጠቀሚው ቁርኣንን ከኢስላማዊ ባህላዊ ሳይንስ ጋር ወደ ቀድሞ ሁኔታው በመመለስ በቁርኣንና በሙስሊሞች አዕምሮ (አስተሳሰብ)መካከል ያለውን ክፍፍል መቋጨት ነው፡፡ በዚህም ቁርኣንን የጊዜው የሙስሊሞች ዋነ የእውቀት ምንጮች በመስደረግ የሚከነውን ነው፡፡ ይህ ቀደምት አያቶቻቸን ትክክለኛ ፣የሕይወት የሰው ዘርና ለማግኘት በቁርኣን ላይ የመረኮዙ እንደነበር ሁሉ አሁንም ቁርኣንን ለዚህ ዓለማ ማዋል ይገባል፡፡

---

1.ተውሂድ፡-የአላህ አንደነት አለህ በዕውን ያለ ነገር ሁሉ አንድ ብቸኛ እንከን  የላቀ ፈጣሪ ጌታና አምላክ መሆኑን የማረጋገጥ ድርጊት፡፡ በተለመደው ቀላል አገላለፅ ተውሂድ ‹‹ ከአምለክ ሌላ አምለክ የለም›› በሚል እምነትና ምስክርነት ነው፡፡ ተውሂድ የኢስላም ዋና የእምነት ምስክርነት ነው፡፡ ተውሂድ የኢስላም ዋና የእምነት መሠርት ነው፡፡ ለኢስላማዊ ስልጣኔ ማንነትን የሚሠጥ ››፣ልዩ ሌዩ ክፍሎችና አንድ

ላይ የሚያያዝ እና ስልጣኔ የምንለው የተሟለ ሕይወት ያለው አካል የሚዳርጋቸው ነው፡፡

ሁለተኛው መርህ ዘመናዊ ኢስላማዊ ባህልና ስልጣኔ ለመገንባት የነብዩን ሱንና ለመገንዘብ የሚያስችል ስነ ዘዴ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ሶስተኛው የእራሳችንን ዘመናዊ ባህልና ለመገንባትና ከእነኚህ ተመኩሮችን ለመጠቀም በኢስላማዊ ውርስ ላይ መመርኮዝ ለመገንዘብም ትክክለኛ ስነ ዘዴዎችን መተግበር የሚያቅፍ ነው፡፡

ዐራተኛው መርህ የግንዛቤ መንገዶችን በመመርመርና በመጠቀም ለወቅታዊው የዐረቡ ዓለም ሃሳብ መፍተሔ መፈለግ ይሆናል፡፡

መከተል ያለብን ስትራቴጂ ቁርኣንን ለመገንዘብና ለመተግበር ለሚያስችሉ ስነ ዘዴዎች ተገቢውን ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት ፡፡ በዚህ ተልዕኮ ሂደትም በእነኚህ ምርምሮች ጥናቶችና ላይ ትኩረት ለማድረግ የቁርኣን ፋይል ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

1.ቁርኣንን የመገንዘቢያና የዘመናዊ ሙስሊሞች ቀዳሚ የባህል፣የዕውቀት የሳይንስና የመመርያ ምንጭ የማድረጊያ መንገዶች፡፡

2.ከተፍሲር፣ተዕዊል(የታሰቡ ፍቺዎች ትርጓሜ)፣ከቁርኣን ምደባና አመለካች፣ ከቀድሞና ዘመናዊ የሙስሊሞች ሳይንሶች ጋር ቁርኣን ያለው ግኙኙነቶችንና የሚመለከቱ ጉዳዮች፡፡

3.ሌሎች ሀ)ሙስሊም ምሁራን ቁርኣንን በትክክለኛ መንገድ ለመተግበር የሚያስችላቸው ችሎታ መልስ ለመፍጠር

ለ) በዘመናዊው የሙስሊም ባህል፣ዕውቀትና ስልጣኔ መካከለኛ ቦታ ቁርኣንን በተገቢው ደራጃ ለማኖር ዓለማ ያደረጉ ሌሎች ጉዳች ይህ ከሆነ የሙስሊሞች አዕምሯዊ ችሎታ የሚታደስ ፣ቁርኣን የማንቃት ሚናውን እንደገና ማግኘት ይችላል። ወደፊት የሚታሰበው የቁርኣን ፈይል በሸይኽ ሙሓመድ አል ጋዛሊ ከይፋ ነተ ዓመል ማዓ አል ቁርኣን የተጀመረና ይህን ዐቢይ ርዕስ በሚሸፍቱ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያላቸው ጥናቶችን ማስከተል ይቻላል፡፡ ይህ መፅሓፍ ቁርኣንን በለውጥ ላይ ካላቸው ዓላማ ውስጥ ወደ አሳማኝ አገባብ ለማምጣት በኣዲስ ንቃት ጥረት የሚያደርግ ነው ፡፡

በእርግጥ ይህ መፅሐፍ ለሁሉም ችግሮች መፍትሔ የሚሰጥና ለሁሉም ጥያቄዎች ምላሽ ያለው ነው ለማለት አይቻልም ፡፡ ይሁንጂ ዘመናዊ ኢስላማዊ ስነ-ዘዴያዊ ንቃት ለመፍጠር የመጀመሪያ እርምጃ ነው፡፡ ጥረቱ ኢስላማዊ ውርስና ቅርሳችንን ከሰብዓዊ ገጽታ ወደ መከለስ እና ወደ መመዘን የሚያደርሰን መሆን አለበት፡፡ ይህ ጥናትም ሆነ በዚህ ርዕስ ላይ የሚካሄዱ የወደፊት ስራዎች ከተለመዱት የተወረሰ የኢስላማዊ አስተሳሰብ ጉዳዮች ጋር መጠረስ የላባቸውም፡፡ በተቃራኒው ዕውነተኛናታቸው ሊረጋገጥ ከሚችሉ ውርሶች የሚቀበልና ለሁሉም ኢስላማዊ አዝማሚያዎችና የአስተሳሰብ ምድቦች ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡ በተለይ ከውድቀት፣ ኋላቀርናትና ከዕውቀት መገታት ዘመን በፊት ለተከሰቱ ወርሶች፡፡

በዚህም ቁርአንን ለበለጠ እውቀተኛ ምክንያታዊ አዕምሮ ላላቸው ሕዝቦች ለማድረስ መሥራት ኢስላማዊ ግዴታ ነው መጽሓፍ ብዙና ልዩ ልዩ የሚተነትኑት ወሳኝ መግብያዎች ያለው ነው፡፡ ጥያቄዎቹና መልሶቻቸውም የሚዘወተር ማናቸውንም እምነቶችና ሃሳቦች ያለ ሂስና ትንተና የማይቀበሉ የስነ ዘዴ መርሆች ጋር በሚስማማ መንገድ ቁርአነዊ ንቃት ለመፍጠር የሚጥር ናቸው፡፡
ቁርአን ምሁራን ወደ እራሳቸው የዕውቀት ዘርፎች ዕውቀት የሚቀዱበት ምንጭ ከሆነ ቆይቷል፡፡ ዓለምን የሚረዱበት መሠረትም ሆኖላቸዋል፡፡ ቁርአንን የሚተገብሩባቸው መንገዶች እንደየ ሰብአዊ ሃሰብ ታሪካዊ እድገት ቢለያይም ፡፡
ቁርአንን በጠቅላላነት የሚያነብ ሰው በመምረጥ ከሚያነበው አንባቢ፣አያቶችን እንደየ አገባባቸው ከሚያነበው ይለያል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ቁርአንን እንደ ታሪኮች፣ህግጋት፣ማበረታቻዎችና ማስፈራሪያዎች ስብስብ የሚቆጥረው ሰው ቁርአንን ትእይንት ዓለምን ለመረዳት ዕንቅስቃሴዎችንና በቋሚ ሁልጊዜ ተለዋዋጭ የጊዜና ቦታ እስፔክትረም ያሉ ግንኙነቶችን በተመለከተ እራሱን የቻለ ግንዛቤ ለመግኘት የሚያስችል የተሟላ ባሕሪ ሀሳብ እንደሆነ ከሚመለከተው ሰው ይለያል።
ቁርአን የራሱ የሆኑ ልዩ ባህርያትን በመግለፅ ለሁሉም ዘመን ለአለፍ፣ለአሁንና ለወደ ፊት ጊዜ ሁኔታዎ ምላሽ የሚሰጥ የተሟላ ወሕይ (ራእይ) እንዳለው ያብራራል፡-

وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ هُوَ ٱلۡحَقُّ مُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيۡهِۗ إِنَّ ٱللَّهَ بِعِبَادِهِۦ لَخَبِيرُۢ بَصِيرٞ ٣١ ثُمَّ
أَوۡرَثۡنَا ٱلۡكِتَٰبَ ٱلَّذِينَ ٱصۡطَفَيۡنَا مِنۡ عِبَادِنَاۖ فَمِنۡهُمۡ ظَالِمٞ لِّنَفۡسِهِۦ وَمِنۡهُم مُّقۡتَصِدٞ وَمِنۡهُمۡ سَابِقُۢ
بِٱلۡخَيۡرَٰتِ بِإِذۡنِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡفَضۡلُ ٱلۡكَبِيرُ ٣٢ فاطر: 31 -32

‹‹ያም ከመጽሐፉ ወዳንተ ያወረድንልህ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲሆን እርሱ እውነት ነው፤ አላህ በርግጥ በባሮቹ ውስጥ ዐዋቂ ተመልካች ነው፡፡ከዚያም እነዚያን ከባሮቻችን የመረጥናቸውን መጽሐፉን አወረስናቸው፤ ከነርሱም ነፍሱን በዳይ አለ፤ ከነርሱም መካከለኛ አለ፤ ከነሱም በአላህ ፈቃድ በበጎ ሥራዎች ቀዳሚ አለ፤ ያ (ማውረስ) እርሱ ታላቅ ችሮታ ነው›› (ቁርኣን 35፡31-32)

እነኚህ አያት ቁርኣን በየዘመነት ለሚከሰቱ ሁኔታዎችና ፍላጎቶች እራሱን በሚያድስ ሂደት በቋሚነት ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡

۞ فَلَآ أُقۡسِمُ بِمَوَٰقِعِ ٱلنُّجُومِ ٧٥ وَإِنَّهُۥ لَقَسَمٞ لَّوۡ تَعۡلَمُونَ عَظِيمٌ ٧٦ إِنَّهُۥ لَقُرۡءَانٞ كَرِيمٞ ٧٧ فِي كِتَٰبٖ مَّكۡنُونٖ ٧٨ لَّا يَمَسُّهُۥٓ إِلَّا ٱلۡمُطَهَّرُونَ ٧٩ الواقعة:75-79

‹‹በከዋክብትም መጥለቂያዎች እምላለሁ፡፡እርሱም ብታውቁ ታላቅ መሐላ ነው በተጠበቀ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡የተጥራሩት እንጂ ሌላ አይነካውም፡፡ ›› (ቁርኣን 56፡75-79)

አላህ የቅድመ አያቶቻችን ታሪኮች የሚተርክበት ቁርኣን ልዩ ልዩ ባሕርይም አለው፡፡ የማይሳሳትና ሊለወጥ የማይችል መለኮታዊ መፅሐፍ ነው፡፡

إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٩ الحجر:9

‹‹ እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡›› (ቁርኣን 15፡ 9)

ስለዚህ ቁርኣን ለወደፊት ትውልዶች ለጉዳዮቻቸው አብሮነት ያለው ስልጣንና ኃይል ያለው ሊታመን የሚችል ሰነድ ነው፡፡

وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ إِلَّا رِجَالٗا نُّوحِيٓ إِلَيۡهِمۡۖ فَسۡـَٔلُوٓاْ أَهۡلَ ٱلذِّكۡرِ إِن كُنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ٤٣ بِٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلزُّبُرِۗ وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلذِّكۡرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيۡهِمۡ وَلَعَلَّهُمۡ يَتَفَكَّرُونَ ٤٤

النحل:42-44

‹‹ከአንተም በፊት ወደነሱ ወሕይን (ራእይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ፣ ሌላን አልላክንም፤ የማታውቁም ብትሆኑ የዕውቀትን በለቤቶች ጠይቁ፡፡በግልጽ ማስረጃዎችና በመጻሕፍት (ላክናቸው)፤ ወደ አንተም፣ ለሰዎች ወደነሱ

የተወረደውን (ፍች) ልትገልጽላቸውና ያስተነትኑም ዘንድ ቁርአንን አወረድን። ››
(ቁርኣን 16፡43-44)

ከቀደሚዎቹ መፅሓፍ መጥመምና ፈንገጫዎች ሃሳብ የሚያስለውጥ መፅሓፍ ነው፡፡

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ فَٱخْتُلِفَ فِيهِ ۗ وَلَوْلَا كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ لَقُضِىَ بَيْنَهُمْ ۚ وَإِنَّهُمْ

لَفِى شَكٍّ مِّنْهُ مُرِيبٍ ﴿٤٥﴾ فصلت:45

‹‹ሙሳንም መጽሐፉን በእርግጥ ሰጠነው፤ በርሱም ተለያዩበት፤ ከጌታህም ያለፈች ቃል ባልነበረች ኖሮ በመካከላቸው በተፈረደ ነበር፤ እነርሱም ከርሱ አወላዋይ በሆነ ጥርጣሬ ውስጥ ናቸው። ›› (ቁርኣን 41፡45)

በተጨማሪም ቁረኣን ሌሎች ብዙ በሕርያት አለው፡፡ እነኚህንም በቁርኣን ሕያውነትና ስነ-ዘዴያዊ አንድነቱ ለማወቅ እንችላለን፡፡ ይህ በተለይ የአያቶቹ ቅድም ተከተል በወረደበት (በወሕይ ጊዜያት) ሳይሆን መፅሓፍ በደንብ ከተስተካከለ በኋላ የሆነ ነው፡፡ (በወሕይ ወቅት የቁርኣን አያቶች የተሰበጠሩና በወረዱበት ውስጥ ክስተቶች ዘወሰኑ ነበሩ፡፡)እነኚህ ባህርያት ቁርኣን በመለኮታዊነት የሚያቆይና የሚጠብቅ መሆኑን የሚያመለክቱና በውስጡ የያዛቸው ወድ ሃብቶች እንደየ ጊዜው አስፈላጊነት በመግለጥ ለሰው ልጆች ጉዳዮቹ ያለውን አስተዋፆኦ የሚያድስ ነው፡፡ ቁርኣን ስነ ፍጥረኦን በተመለከተ የተሟላ ግንዛቤ ስለሚያቀርብ ዕንቅስቃሴዎቹንና እርስ በእርሳቸው ባለቸው ግንኙነቶች ላይ ንቃት ስለሚፈጥር የጊዜ፣የቦታና የለውጥ ጌታ ነው፡፡ የሁሉም ህልውናና የኣላህን ቃላት ዕውቀት ንቃት የያዘም ነው ቁርኣንን በመሆኑም የአለፉት፣የአሁን ጊዜና የወደፊት ትውልዶችም በየትኛውም መንገድ ወሕይን (የኣለህን ራእይ) በተመለከተ የተሟላ ግንዛቤ ላይ ሊደርሱ አይችሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ ከኖርበት የእራሳቸው ጊዜ ስልጣኔያዊ፣ማሕበራዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች እንዲሁም አስተሳሰብ ስልቶች የሚፈልጉትን ከቁርኣን የሚወስዱ ይሆናል፡፡

የሼኽ አል ጋዛሊ መፅሓፍ አስፈላጊነት አዲስ ትርጓሜን ስለሚያቀርብ ሳይሆን የጊዜውን ኢስላማዊ ሃሳብ ወደ ዕውቀት ፈለጋ እና ትክክለኛ ስነ-ዘዴ ከመምራቱ በፊት ጉድለቶችንና እጥረቶችን ለማስወድ ጥረት ስለሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ተግባራዊ የሚሆነው በዓለም ውስጥ እየተከሄዱ ያሉ አዳዲስ ለውጦችና ዕድገቶችን መቀበል በጀመረው ኢስላማዊ ህብረተሰብ ውስጥ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ስነ-ዓላማዊነት

በሃሳብም ሆነ በዓለም ኢስላማዊ ባሕርይ ነው ፡፡ ነብዩ የነብያት መከተሚያ፣ቁርአን የመለኮታዊ መፅሐፍት መደምደሚያ መሆኑን በማወጅ የመጀመሪያውን ዓለም አቀፋዊ ሓይማኖታዊ እንቅስቃሴ የመሠረተው ኢስላም ነበር ፡፡ አልፎም ድንበሮቹን በምዕራብ ከአትላንቲካ ውቅያኖስ በምስራቅ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ በማስፋት በምስራቁ ዓለምና በምዕራቡ ዓለም   መካከል የነበሩ ልነቶችን በማሸነፍ የዘመኑ ማዕከላዊ የጥንታዊ ዓለም ስልጣኔዎችንና ዘሮችን በሙሉ ያወሃደው ኢስላማዊ ስልጣኔ ነበር።

ስነ ዓለማዊነት በኢስላመዊው መዋቅራችን ውስጥ በጥልቀት በመቅረፅ የዓለማችን ስልጣኔ ውድቀቶችና ኢስላማዊ መፍትሄዎቻቸውን ማጤን በእኛ ላይ ግዴታ ነው፡፡ ይህም የዘመኑ ሰዋዊ አስተሳሰቦችና ግኝቶች በአንድ ወጥ አገባብ በማደራጀትና ኢስላም በሰው ልጆች ታሪክ ላይ ያላውን የባለይነት በሚያሳይ ስነ ዘዴያዊ ንቃት ይሆናል ይህ የቁርአን ይዘት ሳይቀየርና ሳይዘምን በአለበት ሁኔታ የሚከናውን ነው፡፡

እዚህ ላይ ለወቅታዊው ስነ- ዘዴያዊ ንቃት ተፈላጊ ነገሮች መጥቀስ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ የተውሰነ ወቅት ወይንም ዘመን አካል ብቻ በመሆንና አካባቢያዊ ነገሮችን በመዘንጋት ወይንም ችላ በማለት በቀላሉ የሚከወን አይደለም ፡፡ ዕድገትና ልማት የዘመኑ ድሎችና ብዙ የቅርብ ጊዜ ግኝቶችን የማከመቸትና በቆየው ማህበራዊ ሥርዓት ውስጥ ቆርጦ በመቀጠል ብቻ አይደለም ፡፡ በህብረተሰቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃሳባዊ መዋቅር ውስጥ ጥራት ያለው ለውጥ መፍጠር ጭምር ነው ፡፡ ይህ ቁርአንን በአዲስ መልክ መቅረብና መገንዘብ ለአዲስ ዕውነትም ትኩስ ንቃትን መፈለግን ይጠይቃል፡፡ የዘመኑ ማሕበረሳብ ሃሳብና ግንዛቤ የቆየው ማሕበረሰብና ሃሳቦች በወደ ፊት ጊዜያት አገባብ መቀጠል ማለት አይደለም ፡፡ በተቃራኒው አንድ ማሕበረሰብ ወቅቱ ለሚፈልገው ሹመት ብቁ ለመሆን ሊያልፈወባቸው የሚገቡ ታሪካዊ ለውጦችን የሚያመለክት ነው ፡፡

እነኚህ ለውጦች አንድ ማህበረሰብ እንደጋና እራሱን እንዲያገኝ ለእኛ ደግም ቁርኣንን እየተለወጠች ባላችው ዓለም ውስጥ ባለ ወሰን ማግኛትና ማወቅ ማለት ነው፡፡

ከዚህ ማዕዘን የሚኖር ግንዘቤ ብዙዎቹ የዐረብና ኢስላማዊ ሕብረተሰቦችበአሁኑ ጊዜ ውስጥ እዚህ በመኖራቸው ብቻ እራሳቸውን እንደ ወቅታዊ ማሕበረሰቦች

የሚቆጠር ሆነው እነገኛቸዋለን ፡፡ ይሁንጂ በዕውነታው በወቅታዊው ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ አይደለም፡፡ የአሁኑን ዘመን ዓለም ኣቀፋዊ ባህላዊ ንቃት ከእነ፣ኣሳሳቢ ጥልቅ የአስተሳሰብ ባሕረይና ከፍተኛ ምኞቶች ስነ-ዘዴያዊ ዕውቀት ለመቅሰምና የዛሬ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ዕውቀት የላቸውም፡፡ የዐረብና ኢስላማዊ ማሕበረሰቦች ከዚህ ይልቅ በዘመናዊው ዓለም አቀፋዊ ወቅት ላይ እየኖሩ ወደ አለፈውና ባህላዊ አስተሳሰቦቻቸው የማሰብ አዝማሚያ ያላቸው ናቸው፡፡ ይህ መከፋፈል በወቅታዊነት ውስጥ የመኖርና ለወቅቱ ሁኔታ ምላሽ የመስጠት የሚያስችል ዓለም አቀፋዊ የንቃት ችሎታ ማነስ ቅልቅል ስሜት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በእነኚህ ሕብረተሰቦች ውስጥ የሚኖር የተወሰኑ የዕውቀት መሪዎች በባህላዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ ፅሑፎችን ማዘጋጀት መቀጠላቸውን የዓለም አቀፍ ታሪካዊና ማሕበራዊ ለውጥ ተፈጥሮ ሳይዳስሱ የኣለፈውን አኗኗር በአሁኑ ጊዜ ውስጥ ደግም ለመፍጠር ጥረት ላይ መሆናቸውን እናገኛለን፡፡

የቀጥተኛው ቅደመ አያቶቻችን የእጅቲሃድ ጉዳዮች በማበልፀግ በኃላ በእራሳቸው ዘመን ለእራሳቸው ጉዳዮች በመጠቀም የተብቃቁ ናቸው ፡፡ በተመሳሳይ ጊዜም እነኚሕ  ዕውቀታዊ መሪዎች በሁለቱ ዘመኖች መካከል ያሉ ታሪካዊ ልዩነቶችን የማያስተውሉና ለዘመናዊው ጊዜ የኢጅቲሃድ አስፈላጊነት ለመገንዘብ ያልቻሉ ናቸው ፡፡

---

1.ኢጅቲሃድ፡- ተቀባይነት ያገኙ የኢስላም የህግ ምንጭች ለሁሉም ጊዜያትና ቦታዎች ዋጋ እንዳላቸው በማሰብ ኢጅቲሃድ የሙስሊሙን ማሕበረሳብ ተለዋዋጭ ክስተቶች የሚፈጥሩ ተለዋዋጭ ነገሮችን በማገናዘብ ከእነዚያ ምንጮች ሕጋዊ ወሳኔዎችን ለማግኛት ፈጠራዊ ግን ስርዓት ያለው ዕውቀታዊ ጥረት ነው ፡፡

---

በዚህም ቀደምት ዑለማዎችና ምሁራን የኢጂቲሃድ አርዓያዎች መሆናቸው ቀርቶ የሚኮረጁ አርኣያዎች እየሆኑ ነው ፡፡ ይህን አካሄድ መቀየር አለብን ፡፡ ፖለቲካዊና ሕገ መንግስታዊ ህግጋትን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶችን በሚያቅፈው የፊቅህ ዕድገትና መሻሻል እንቅፋት የሆኑ ታሪካዊ ነገሮችን ለመለየት ጥረት መድርግ ይኖርብናል፡፡ እነኚህ ታሪካዊ ክስተቶች በአዕማህ ሀለፊነቶችና ለፊቅህ ቅርንጫፎች ባለቸው ቁርጠኛነታቸው ላይ ተፅዕኖ ያደረጉበትን መንገዶች ማብራራት አለብን ከዑማው (የሓያማኖት መመርያዎች) ለፊቅህ ያላቸው ከበሬታ

ሙሃዲሱን (የሃዲሱን ምሁራን ወይንም ዓሊሞች) ሰነድን ወይንም የሃዲስ አዘጋገብን በተመለከተ ከላቸው ተዓማንናትና ቁርጠንነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የዚህ ዓይናት ታሪካዊ መግለጫ ፍቅህን ታሪከ ወደ አገለገለው ተገቢ ደረጃው ሊመልሰው የሚረዳ ነው በባለስልጣነትና በዑለማእ በፊቅህና ሱፊነት፣ሱንና ሳይጠቅሱ ቁርኣንን በሚያጠኑትና ቁርኣንን ሳይጠቅሱ ሱንናን በሚያጠኑ ሰዎች መካከል ያለውን አለመግባባትም የሚያጋልጥ ነው አንድ ከፍተኛ ከቅራኔ ነፃ የሆነ በአላህ ፀጋ የተሰጠ የዑማው ኢስላማዊ ክንውኖች አዝማማሚያዎች የትኩረት ነጥብን አቅጣጫ-ቁርኣን ስለ አለ በኢስላማዊ ሥርዓት ውስጥ በእነኚህ ስሜቶች መፍጠር አልነበረባቸውም፡፡ ይህ ቁርኣን ፋይዳዎቹና ጠቀሜታዎች ለሙስሊሞችም ሆነ ለሌሎች ፍጡራን እኩል የሆነ ምሉዕና ሚዛነዊ ስልጣኔን ለመፍጠር ያለውን ሚና በተሟላ መንገድ ኢንዲውጣ የአላህን ፍቃድ ከሰው ጥረት ጋር የሚያገናኝ ነው::

وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَـٰبَ تِبْيَـٰنًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ ﴿٨٩﴾ النحل:89

‹‹መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፥ መሪም እዝነትም ለሙስሊሞችም አብሳሪ ሆኖ ባንተ ላይ አወረድነው፡፡ ›› (ቁርኣን 16፡89)

## ሱንናን በአግባቡ መረዳት ዶ/ር ጣሃ ጂ . አል ዐለዋኒ

ኢስላም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሱንና ለዑለማዎች፣ ለምሁራንና በለሙጅተሂድን (እጅቲሃድ ለሚያከናውኑ ዑለማዎች ) ዘንድ በሚታወቅ የመመሪያዎች መዋቅር ውስጥ ሲነሳና ሲተረጎም ኖሯል ፡፡ ስልጣንን ኃያሉ ከቁትኣን ቀጥሎ ሁለተኛ ነው፡፡ ሱንና ቁርኣንን የሚያብራራና የሚገልፅ ከምንም በላይ አስተምህሮዎችንና ስነ ዘዴውን የሚተገብር በመሆኑ በእርግጥ ሁለቱ አይለዩም፡፡

ስለዚህ ሱንናን ያለው ቦታ አስፈላጊ ኢስለማዊ አካል ነው ዕውነታውም በቀደምት ሙስሊሞች ዘንድ የክርክር ርዕስ ሆኖ አያውቅም ፡፡ በኋላ በመጡ ትውልዶች ዘንድ ግን በነብዩ ሱንናና ተኣማንነት በለውና ለሚኳቸው በሚገቡ ሀዲሶች እንዳቆየልን - በጥንት ዜና መወዕሎችና ትርክቶች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ያልቻሉ ዝቅተኛ ዕውቀትና ግንዛቤ ያላቸው ሕዝቦች ተነሱ፡፡ እነኚህ ታሪካዊ ወይንም ትርክታዊ ዘገባዎች ምን ያህል ተከተይነት እንዳላቸው፣የሰዎችን ዕውቀት ለመጨመር ውይንም በምክንያታዊ ወይንም በተጨባጭ ማስረጃ በሚቀረናቸው

ወቅት እንኳያለቸውን ተቀባይነት ዋጋ አላወቁም ነበር፡፡ የተሳሳተ መረጃ የደረሷቸው እነኚህ ሕዝቦች የዚህ ስነ-ዘዴያዊና ፍልስፍናዊ ጉዳይ ንግግር በራሱ በሱንና ላይ የሚካሄድ ንትርክ ያሰቡ ነበር፡፡ ሱንኖች (ልምዶችና ድርጊቶችን) የተያያዙ ዘገባዎችንም እንደ ተራ ሪፖርቶች ይቆጠር ስለነበር አብዛኞቹ ንትርኮች በእነኚህ ዘገባዎች ላይ የሚያውጠነጥኑ ነበር፡፡ ሱንና በነብዩ እንደ ምሳሌዎችና መመርያዎች የተቀመጠና የተላለፈበት መንገዶች መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ለመረዳት አልቻሉም በተጨማሪም በአንድ በኩል የነብዩ ድርጊቶች፣ክንውኖችና ንግግሮች የተዘገቡበትን ዘዴዎችና በሌላ በኩል ስለ ሌሎች ሰዎች የተዘገበው መካከል ያለውን ልዩነት ማየት አልቻሉም ነበር፡፡

የዚህ አሳዛኝ ውዥንብር ውጤት የሱንና የእራሱን ተቀባይነት ወደ ሚመለከት ተለወጠ ፡፡ ይህ ክርክር የዑሱልና ሀዲስ ጥናቶችን ላይ በተፃፈ ትናቶችን በያዙ መፅሓፍት ውስጥ ብዙ ቦታ የያዘ ነው፡፡ በዚህ የባከነ ኃይል ሱንና ለመገንዘብ፣ ለማብራራትና ተመኩሮዎችን ለመውሰድ በዋለ ኑሮ በሁሉም ቦታና ዘመን ያሉ ሙስሊሞች በአስተምሮዎቹ ላይ ተመስርተው አስተሳሰባቸውንና የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንዲያደራጁ ያስችላቸው ነበር፡፡

የሱንና ዘገባዎችን በአጠቃላይና አሃዶች (በአንድ ሰው ብቻ ያወራቸው ሀዲሶች) በተለይ የሚመለከቱ አስፈላጊና የታሰበበቸው ክርክሮች ሌሎች አሉታዊ፣ከባድና ጎጂ ውጤቶች አሏቸው፡፡ በሙስሊሞች መካከል ያሉ ልዩነቶችንና ክርክሮች በጥልቀት የሚፈጥር ናቸው፡፡ በዚህ መስክ የሚካሄዱ ምርምሮች ኢስላማዊ ጥናቶች ላይ ጥላ የሚያጠሉና ብዙ ስራዎችንም አውንታዊ እውቀታዊ ውይንም ተጨባጭ ተፅዕኖ መፍጠር ወደ ማይችሉ ተጨባጭነት የሌላቸው ወይይቶች ዝቅ የሚያደርጉ ናቸው ፡ ፡ ሰንናን ከቁርኣን አኳያ ያለው ደረጃ የሚመለከቱ ውዝግቦች የሱንና በቁርኣን መካከል ያለው መተካከት ሙስሊሞችን ለአስፈላጊ፣ረጅምና ተደጋገሚ ወቀሳ፡ ታሪካዊ ዘገባዎችን፣ ተራኪዎችንና የተናጋሮዎችን ማንናት ዕውነተኛነት በማጣራት ጊዜያቸውን እንዳያበክኑ ያደረጋቸው ነው፡፡ ለጥናት፣ ለማብራራትና መፅሓፍትን ለመገንዘብ፣ ሀዲሲችን ከጊዜና ቦታ አካባቢና ዕውነታ ጋር ለማቅረብ የተሰሩ ሥራዎችን የተመለከተና ለአስኒድ ጥናት የቃሉ ታላላቅ ጥረቶችንና ብዙ ቅች ጋር ያወዳደራቸው ተከትለው የመጡ ችግሮችንና ብጥብጦችን መነሻና ተፈጥሮ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መንገድ ሕግ በማውጣት መስክ ከፍተኛ መጠን ያለው ኃይልና ጉልበት ዋጋ ያላቸው ሥራዎች ለዑማ ፍላጎቶች የበለጠ መፍትሔዎችን ለማስገኘት ይችሉ ነበር። ይህ ግን ሥራዎች ሕግ-ነክ ገፅታዎችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የሱንና ገፅታች ያከተቱ ቢሆኑ ነበር፡፡

ሱንና እንደ አጠቀላይ የቁርኣን ቁርኣን ስነ ዘዴ ታሪካዊና ጂኦግራፊያዊ አገባብ በተውሰኑ በርዕይታዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ በመተግበር የሚካሄድ የአመራር ደረጃን ይወክላል ፡፡ ሱንናን የመገንዘቢያ ስነ-ዘዴዎች ጥናት ከዑሱል እና ሀዲስ ጥናቶች የበለጠ አስፈላጊ ገፅታዎች አንዱ እንደ ሆነ ይቆጠራል፡፡ ይህ ቁርኣን በጠቅላለው በተተባበረበት፣ቁርኣን ኢስላማዊ ሃሳቦችን ወደ እውነታ ለመተርጎም ቁርኣን የመሪነት ሚና በተጨወተበት መጪው ትውልድ ለመጥቀስና ለመድገም የሚጥረው የታሪክ ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ ሱንና የአላህን መልዕክት ለመተግበር ከሁሉም በላይ ከፍተኛውን ፣ይበልጥ ትክክለኛውን ምርጡና ሐቀኛወን መንገድ ይወክላል፡፡ እውነተኛው፣ስልጡን ሁሉን ዓቀፍ የቁርኣን ስነ-ዘዴ አምሳያ ነው፡፡ ይህ ምናልባትም ፈጣሪ ቁርኣንን በወረደበት ቅርፅ ለመቆየትና ለመጠበቅ ከተጠቀመው ዘዴ በስተጀርባ ያለውን የአላህ ጥበብ ነው ፡፡ ነብዩ በስተጀርባ ያለውን የአላህ ጥበብ ነው፡፡ ነብዩ እራሳቸው እያንዳንዷን ቁርኣን ፊደላት ፣ አናባቢዎችን መግቻዎችን ለማቆየት ጠንካራ አቋም አሳይተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ እያንዳንዷ የቁርኣን ፊደል በወረደችበት ቅርፅ እንድትቆይ ዘላቂ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ የትኛውም አያት ማሰጠር ተከልክሏል፡፡

ሱንናን በተመለከተ ይህ እውነታት የለውም ፡፡ ሱንና ተጠብቆ ለመቆት ቢቻልም ቀደም ተብለው የተጠቀሱ ክልከላዎች አልተሰጠም ፡፡ በተጨማሪም ነብዩ እንደ ቁርኣን ተፅፎ እንዲቆይ አላደረጉም፡፡ ቁርኣን ከጅብሪል ጋር እንደከለሱት አልከለሱትም ፡፡ ለዚህ የአቀራረብ ልዩነት ምክንያቱ በሰዎች ችሎታና ክህሎት ከፍተኛው ደረጃ ሱንና ተጨባጭ ልምድና ተግባር ሆኖ እንዲዘልቅ ለማስቻልና ነብዩ ለቁርኣን የነበራቻው የተሟለና ሁሉን አቀፍ ቀረቤታ እንዲኖር ነበር፡፡ በእርግጥ እሳቸው ቁርኣንን በሁሉም ዕለታዊ አኗኗራቸውና ዓለማዊ ክንውኖች ደዕዋ ሲያደርጉ፣ሲያስተምሩ፣በዙርያቸው ለውጥ ሲፈጥር ፣ ሲከለክሉ ፣ሲያዙ ሲመክሩ፣ ሲያመክሩ፣ሲማሩ ሲድኑ፣ፈትዋ ሲሰጡ፣መመርያ ሲያስተላልፍ ስነ-ስርዓት ሲያሲዞ ፣ሲዋጉ፣ሰላም ሲያስገኙ ስምምነት ለይ ሲደርሱ፣ሲነግዱ መልዕክቶችን

ሲለዋውጡ፣ ጋብቻ ሲፈፅሙ ፣ፍቺ ሲፈፅሙ ሲገነቡ ፣ሲያፈርሱ ፣ሲገዙ.. ቁርአንና ቁርአነዊ ስነ-ዘዴን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

የቁርአን ስነ-ዘዴ የነብዩን ድርጊቶች የሚከተልና የሚቆጣጠር ነበር፡፡ ከአያቶች ብዙዎቹ ይህ ስነ ዘዴ የሚተገበርበት ስርዓት የሚመዝኑ አስፈላጊም ሲሆን የሚወቅስ የሚገመግሙ፣የሚያስተካክሉና የሚመሩ ነበር ይህ የሆነው ቁርአንን መተግበር በሰዋዊ ውስንነቶች የተከበበ እንዲሁም በጊዜ ቦታ ተፅዕኖ ስር ስለአለ ነበር፡፡ አላህም ‹‹ በምትችሉት መጠን አላህን በማስታወስ ቆዩ›› ያለው ለዚህ ነው። ነብዩ ሌላ ሰው የቁርአንን ስነ ዘዴ ሲተገብሩ ትግበራዊ

ነብዩ ሥራ ላይ ከዋሉት አንፃር ለመገምገም ከፍተኛ ፍላጎት አለ፡፡ ምክንያቱም ከነብዩ ውጭ ሌሎች ሰዎች ለግላዊ ወገንተኛ ስሜትና ላልተሰው ተፅችኖዎች የበለጠ በቀላሉ ሊለወጡ ስለሚችሉ ነው፡፡ የእምነት የፀሎት ስነ ስርዓት (ዒባዳ) ለምሳሌ በተመለከተ ሰዎች ይከተሉ የነበረው የነብዩን ተምሳልት ብቻ ነበር ፡፤ የእሳቸውን ተምሳሌትነት ይከተሉ የነበረው መከተል የአዕምሮ ክህሎትን የሚጠይቅ ንቁ ድርጊትና በሚከተሉት ተምሳሌት ዙርያ ያሉ ሁሉንም አጠቃለይ ንቃቶች ስለሚጠይቁ ነው፡፡

አለም አቀፍ የኢስላማዊ አስተሳሰብ ተቋም ሁልጊዜም ሱንናን ለመገንዘብ የሚያስብ ነው፡፡ የሱንና አጠቃለይ ጥልቅ ዳሰሳ እንደ ኢስላማዊ ምንጭና ባሕል ዛሬ በሙስሊም ምሁራን ዘንድ ከላቁ ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ ይፈልጋል ፡፡ ይህ በተለይ እውነታነት ያለው የኢስላምን መነሻዎችና መሠረቶች መግለፅና ማብራራት እንዲሁም እነርሱን የመረዳት ስነ ዘዴዎች የዑማውን ዕውቀት ባህልና ስልጣኔ እንደገና ለመገንባት ከሚያስፈልጉ ቀዳሚ ምክንያቶች መካከል ስለሆኑ ነው፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት ተቋሙ የተለያዩ ድርጊቶችን ለማከናወን ወስኗል፡፡

በቅድምያ የዑሱልና የሃዲስ ጥናቶችን በደንብ ከተዳሳሱ ርዕሰ ጉዳዮች እስካሁን መፍትሔ ወደ ላገኙ ጉዳዮች ለማዘዋወር አልሟል ፡፡ ከዚህ አኳያ ተቋሙ የሱንናን አስፈላጊነት በአላህና በመልዕክተኛው ከሚያምኑ ሙስሊሞች የሚካድ ስለሌለ በበቂ ሁኔታ የተዳሰሰ ይህን ርዕስ ተመልክቷል፡፡ ተቋሙ ሑጂያት አልሱንና (የሱንና ሕጋዊ ስልጣኔ ) የሚል በወቅቱ አንጋፋ የዑሱል ሊቅ በሆኑት ሸይክ ዐብድል ጋኒ አብደል ካሊቅ የተፀፈ መፅሓፍ አሳትሟል፡፡ በዚህ ርዕስ ላይ ይህ ጠቃሚ ምሁራዊ

ምርምርና በመስኩ ከተከሄዱ በጣም አስፈላጊና የተሟሉ ስራዎች አንዱና ተቋሙ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደየመጨረሻ ቃል የሚመለከት ነው፡፡

በመካከል ተቋሙ በልዩ ልዩ ርዕሶች ለማስተማሩ ምሁራንና ተመራማሪዎች ሱንናን ሊደርስበት የሚችል ለማድረግ በዚህ መስክ ምርምር የሚያከሄዱ አጥኚዎች ትኩረት የኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጀ ወደሚጠቀሙበት ለማሰብ ጥረት አድርጓል፡፡ ተቋሙ ዓለማ ለሚሰሩ ብዙ ምሁራንም ድጋፍ ሰጥቷል፡፡
በተጨማሪም ተቋሙ ሱንና የፍቅህ ምንጭ ብቻ ሆኖ እንዳያቀየር ሱንና የማህበራዊ ሳይንሶች የዕውቀት ምንጭ እንዲሆን ለመድረግ የሚያስችሉ አግባብነት ያለቸው ማናቸውም ሳይንሳዊ ስነ-ዘዴዎች በመጠቀም ሱንና በርዕስ ለመመደብ ተንቀሳቅሷል፡፡
በመጨረሻም ተቋሙ በሱንና ልዩ ልዩ ገፅታዎችና ኢስላማዊ ስልጣኔ እንደገና ለመገንበት ባለው ሚና ላይ ፅሑፎችን እንዲያበረክቱ አንጋፋ ምሁራንን ለመጋበዝ ዕንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ ታዋቂው ምሁር ሼክ ሙሓመድ አል ጋዛሊ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘውን፡ አል ሱነን በይነ አሕል አል ፊቅህ ወ አህል አል ሀዲስ (ሱንና በፊቅህ በለሞያዎችና የሀዲስ እስፔሻሊስትቶች መካከል) የሚል መፅሓፍ አበርክተዋል፡፡ መፅሓፍ ሱንናን ለመገንዘብ የሚያስችሉ ዘዴዎችን የሚጠቁምና በአስኒድና ዘገባዎች አወቃቀር ሳይ በሚያተኩርና ፍላጎታቸው ሱንናን በወረደበትና ከሱንና ትምህርት በመቅሰም ላይ ትኩረት በሚያደርጉ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ነው፡፤ ይህ የተከበረ ምሁር በተቋሙ አመለካከት መፅሐፎቻቸውን እንዴት እንደሚፅፉ ከፍተኛ ልምድ እንዳለቸው እምነት አለ፡፡ ይሁን እንጂ በመፅሓፋቸው ውስጥ በጠቀሷቸው ምሳሌዎች በተወሰኑት ላይ ብዙ መልዕክት በእነኚህ ትናንሽ ዝርዝሮች ተሸፍኗል ለማለት ይቻላል፡፡

መፅሓፍ በቀዳሚነት ዓለማ ያደረገው ሽርዓና የምርምር ስነ-ዘዴን በተመለተ መሰረታዊ ዕውቀት በሌላቸውና ሀዲሶችን ለመገንዘብ በቂ የታሪክ፣ የሲራህ (የነብዩ የህይወት ታሪክ) ፣ የፊቅህና የዐረበኛ ቋንቋ ዕውቀት በሌላቸው ሰዎች ላይ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች የሀዲስ ስነ-ፅሑፎችን የሚያነቡት የሀዲሶችን ተጥሮና ከነቢዩ ቃላትና ዲረጊቶች በስተጀርባ ያሉ ምክኒያቶችን ሳይገነዘቡ ወይንም የሀዲሶችን አጠቃላይ አገባብ ሰይረዱ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ግንዛቤያቸው እጥረት ያለበትና ግረ የተጋባ ስለሚሆን ወደ ሕዝብ የሚያስራጫቸው የሀዲሶች ዕውቀት የተጠመመ ይሆናል፡፡

እነኚህ ሰዎች ሱንና ከቁርኣን እንደሚቀድም ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡ በክርክሮቻቸው እነርሱ የሚሰግፏቸውን ሀዲሶች የሚቃረኑ የበለጠ ታኣማኒና ዕውነተኛ ሀዲሶች ሲገጥሟቸው የቅራኔውን ተፍጥሮና ምክንያት፣ እነኚህ ሀዲሶችን የመገምገሚያ ዘዴዎችንም ሆነሀዲሶቹን የማገናዘቢያ ትክክለኛ ዘዴዊችን ደንቦችን አይረዱም።

መጽሐፍ በሱንና ጥናት ላይ ለተሰማሩ ምሁራንና ተመራማሪዎች የታሰበና ከትኩረታቸው የተወሰነውን ሱንናን ለመረዳት ለሚያስችሉ ዘዴዎች እንዲያውሉ የሚመክር ነው ፡፡ ይህ ያለ በቂ ግንዛቤ ሱንና ስለማሕኖር ያለ ሱንናም ምንም ፍቅህ፣ኢስላማዊ ስልጣኔ ወይንም እውነተኛ እውቀት ስለማይኖር ነው ፡፡

ተቋሙ በሸይክ አል ጋዛሊ መፅሓፍ ዙርያ ያለውን ግራ መጋባት ሲረዳ ዶ/ር ዩሱፍ አል ቀርዳዊ ሁለት በጥልቀት የተጻፈ መፅሓፍትን አንደኛው ሱንና ለመገንዘብ በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ ሌላኛውን ሱንና የዕውቀት መንጭ እንደሆነ የሚያስረዳ መፅሓፍትን እንዲያዘጋጁ ጠየቃቸው የመጀመሪያው መፅሓፍ ፡- ከያፈ ነታ`ዓመል ማዓ አል ሱንና አል ነበዊያህ(ሱንና የመገንዘቢያ ዘዴዎች) በሚል ርዕስ በተቋሙ ታትሟል፡፡ ሁለተኛው ወደፊት የሚታተም ይሆናል-ኢንሻ አላህ ፡፡

ሱንና የወቅቱን ኢስላማዊ ሕይወት ለመቅረፅ አውንታዊና አንቀሳቃሽ ሚና እንዲኖረው ለመዳሰስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በ ሃዲስ ጥናቶች መርሃ-ትምህርቶቻቸው ውስጥ ሱንና  በስነ-ዘዴያዊ መንገዶች የማጥኛ ዘዴዎች እንዲካታቱ ማድረጋቸው አስፈላጊ ነው፡፡

ሙስሊሞች ሱንና ለማወቅ በየጊዜው እየጨመረ የመሂዱ ፍላጎት እንዲኖራቸው ተስፋ ይደረጋል ፡፡ የዚህ አይነት የሱንና መገንዘቢያ መመሪያዎችና ሁኔታዎች የበለጠ በመድነቅና በሱንና ላይ የተዛባ ግንዛቤ የተፈጠረባቸው ምክንያቶችን ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል ፡፡ ተደራራቢ ጉዳዮች እንዴት ግንዛቤ ውድቀት እንደመሩን ይህ ውድቀት ዒልም አል ከላም (የትምህርት ስነ-መለኮት) በሱንና ተኣማኒነት ላይ በሚደረገው ክርክር እንዲታቀፍ የተደረገበትን ሁኔታ መመልከት ይኖርባቸዋል፡፡

ሱንና ለመገንዘብ በሚደረግ የተሟላ ስነ-ዘዴያዊ አቅጣጫ ውስጥ ሶስት ጥያቄዎች ጥልቅ ጥናትና ምርምር ይጠይቃሉ፡-

1.የመገንዘቢያ ሁኔታዎች

ከሱንና ጋር ተያያዥ ችግሮች በትክክል የመገንዘብ ጥያቄ ከሆነ በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች የተስተዋሉ አለመግባበቶችን ግራ መጋባት ምክንያቶች ምንድን ናቸው ? ለትክክለኛ የሱንና ጥናትና ግንዛቤ የሚያስፈልጉ ባህርያትን መመዘኛዎች ምንድን ናቸው ?ኢስላምን በጥብቅ መከተል ለግንዛቤ ቅደመ ሁኔታ ነውን የተሟላ ጥልቅ ግንዛቤ እጥረት ለማስወገድ የሚቻለው እንዴት ነው ? ለውድቀቱና በወሳኝና በተሟላ መንገድ ለማስተነገድ የሚቻለው እንዴት ነው ?

ግራ መጋባት ያስከተሉና ለብዙ ተመራማሪዎች አመለካከት በከፊል ሱንና ወይንም በመላው ሱንና ላይ የታኣማኒነት ክርክር የፈጠሩ ችግሮችን መፍታት የሚቻለው እንዴት ነው ? በቀደምት ሙስሊሞች ዘንድ ይህ ኣሳሰቢ ጉዳይ እንዳልሆና ኢስላማዊ ታሪክ ለመረዳት የሚቻል ቢሆንም ይህ ክርክር ለንትርኮችና ለፉከራ ምክንያት ነበር !

2.ልዩነቶችና ክፍፍሎች

ዑማው በልዩ ልዩ የእምነት አንጃዎችና ጀምዓዎች የተከፋፈለው እንዴትና ለምንድን ነው ? በትርጓሜ በመገንዘብና በሱንና ስርጭትና ተኣማኒነት የተከሰቱ ልዩነቶች ከእነኚህ ልዩ ልዩ ጀማዓዎች ብቅ ማለት ምክንያት የሆኑት እንዴት ነው?

ሱንና በልዩ ልዩ ኢስላማዊ የእምነት ቡድኖችና ጀምዓዎች መካከል እንደ መሳሪያ ያገለገለው እንዴት ነው ? የውሸት ሀዲሶች የመፍጠር ያልተሟላ ግንዛቤ እና ሱንና ለማውጣት ብቻ የዋለባት ክስተት እንዴት ነው ? በልዩ ልዩ ጀምዓዎች ብቅ ማለት ላይ የዚህ ክስተት ተፅዕኖ ምንድን ነበር በሀዲስ ጥናት ምርምርና በሃዲስ አስተላላፊዎች ሰንሰለት ትንተና ውስጥ ከታዩ የተራቀቁ ቴክኒካዊ ጥያቄዎች ጋር እነኚህ ልዩ ልዩ ጀምዓዎች ያለቸው ተያያዢነት ምንድን ነው ? እነኚህ ጉዳዮች ሁሉ ቀደም ተብለው በዑሱል ምሁራንና በከላም የስነ-መለኮት ምሁራን የተጠቀሱ የሱንና ክፍል አካል የሆኑት እንዴት ነው ? እነኚህ ጉዳዮች የሱንና ደረጃና ወሰን፣ ከቁርኣን አኳያ ያለው ደረጃ፣የተወሰኑ አያች መተካት፣ማብራሪያውና በቁርኣን ውስጥ ያለ ሃሳብ ድንበር መወሰንን፣የነብዩን ኢጂቲሃድ በዚህ ላይ ያለ ክርክር እንዲሁም ‹‹ የንግግረ ሱንና›› እና እነኚህ ጉዳዮችን ብዙዎችን የሚመለከቱ የተወሰኑ ምንባቦችን የሚያቅፉ ናቸው፡፡

ከእውቀታዊና ትምህርታዊ የዕይታ ማዕዘን ከእነኚህ ክስተቶች በሙስሊም አዕምሮ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ ምንድን ነው ? እነኚህን ጉዳዮችን የሚፈጥር ታሪካዊ አገባብ ምንድን ነው ? እውቀታዊ ፋይዳዎችና እስካሁን ያስከተሉት ጫና ምንድን ነው ? በዘመናዊ የሱንና ጥናቶችና ምርምሮች ውስጥ የሚስተናገድባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው ? ለእነኚጥናቶች መርሃ-ትምህርቶች የሚቀረፅባቸውስ መንገዶችስ ምንድን ናቸው? ሙስሊሞችን ለማወሃድና ዑማው ስልጣኔውን እንደገና እንዲገነባ የሚረዳ ምርጥ ራእይ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ ተመኩሮዎች መቅሰም የሚቻለው እንዴት ነው?

3. ሱንናን ለመገንዘብ የጊዜ- የቦታ ተፅዕኖ

ዑሱሊዩን እንደ ቀዳሚዎቹ የሙስሊሞች ትውልድ ሁሉ የነቢዩ ድርጊቶች እና ቃላት የተለያዩ ታሪካዊና ጂኦግራፊያዊ አገባብ ፣ የእሳቸውን ልምድ ሰብዓዊ ተፈጥሮ ለይተው ያውቁ ነበር ። ስለዚህ እነርሱ እነኚህ ምክንያቶች ከቁም ነገር ለመቁጠር የሚያስችሉ መመሪያዎችን ደንግገዋል ። ሌሎች ልዩ ለዩ ዓይነት ሀዲሶችን ሲያነሱ እንዲረዳቸው እስፔሻሊስቶች ከእነኚህ አመለካከቶች የተወሰኑትን ስራ ላይ ማዋል አለባቸዉ ወይ ?ይህ ከሆነ እነኝህ መመሪያዎችን ለማብራራት መከተል የሚያስፈልገው ቅደም ተከተልና ዘመናዊ የሀዲስ ጥናቶች ሚና ምንድን ነው?

ፊቅህ በሚዳስሳቸው ጥቃቅን ጉዳዮችና አሳቢ ፣ ፈላስፋና ሙተካሊም በሚዳስሳቸው እውቀታዊ ጉዳዮች መካከል ያሉት መሰረታዊ የዕውቀት ልዩነቶች በአንድ በኩል ማህበራዊ ሳይንቲስት የሚዳስሳቸው ማህበራዊ ጉዳዮች በተመለከተ ሱናን ለመረዳትና ለማስተናገድ ልዩ ልዩ መንገዶች የሚጠይቅና ብዙ ስነ-ዘዴዎች የሚያስፈልጉት ነው ። የፈቂህ መስክ አካል የሆነ ትንሽ ጉዳይን የሚመለከት ሀዲስ አጠቃላይ ማህበራዊ ጉዳይ ከሚመለከት ሀዲስ የተለየ ነው ። አጠቃላይ ማህበራዊ ጉዳይን የሚመለከተው ሀዲስ ትርጓሜው በማህበራዊ ሳይንቲስቶች በትንታኔያቸው የዚያን ክስተት ሁሉንም ገፅታዎች ከግምት የሚያስገቡበት ነው ። ተመሳሳይ ሀዲስን ተቃራኒ ሀሳቦች ለመደገፍና ---- ከራሳቸው እምነቶች ያላቸው አጥባቂ ደጋፊነት የሚታይበት በዑማው ውስጥ ከሚስተዋለው መከፋፈል እራሳችንን ነፃ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው ? በተለይ በአሁኑ ወቅት ሱንናን መሰብሰቡና ምሁራን አካዳሚያዊ ጥናትና ምርምር እንዲያካሂዱ ፣ውይይቶችንና ክርክሮችን እንዲያካሄዱ ለመጋበዝና ለዚህ አላማ ጥምር ተቋማትን ለማቋቋም በ፡ሚቻልበት ሁኔታ?

## የዑማ ችግሮችን ለመቅረፋ የሱንና ሚና

በአጠቃላይ ኢስላማዊው ዑላምና በተለይ የዐረቡ ዓለም ለወቅታዊው የኢስላማዊ አስተሳሰብ ውድቀት ምክንያት በሆኑ ብዙ ድክመቶዎች እየተሰቃዩ ነው ። ይህ ውድቀት በልዩ ልዩ ቅርፆች የሚታይ ነው ።የበለጠ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡት የሚከተሉት ናቸው ፦

1. በዑማው ልዩ ልዩ የእምነት ቡድኖች መካከል ያሉ ግንኙነቶች መፈረካከስ ፤ በእውቀታዊ ፣ በማህበራዊ የወገንተኝነት እንዲሁም በፖለቲካዊ ገፅታዎች የግጭት መንፈስ መደጋገም ፤ዑማዉን የሚከፋፍሉ ርዕዮቶች ማንሰራራት ወይንም ከሌሉ እነኚህን አይነት ርዕዮቶችን መፍጠር ።

2. የሌሎች ማሕበራዊና አካባቢያዊ አረጋጊ ነገሮች መደምሰስ ፤ የራስ ወዳድነት ፣ ወገንተኝነትና የአንጃ አስተሳሰቦች መብዛት ። እነኚህ አስተሳሰቦች የወደፊት ጊዜን በተመለከተ ስጋትና ጭንቀትን የአሁን ጊዜን በተመለከተ ተስፋቢስነትን ፣ ለየትኛውም አዎንታዊ ድርጊትና ክስተቶች በሚኖር ግብረ መልስ ላይ የተመሰረተ የአስተሳሰቦች ብልጫ ግዴለሽ መሆንና የከፍተኛ ፋላጎት ማጣትን ፤ ግጭትን በመደገፍ ውይይትን የሚያግድና ክርክር ሲኖርም ሌሎች ተነሳሽነቱን እንዲወስዱ መተው ።

3. የዑማውን ማህበራዊ ችግሮችን ከታሪክ ጋር ያላቸውን ትስስር እወነተኛ ተፈጥሮ በተመለከተ የገለልተኛ ንቃት እጦት ። በምሉዕና አጠቃላይ ትንተናዊ የአመለካከት ነጥቦች ለይ የጥራዝ ነጠቅ ፣ ጠባብ ፣ ስሜታዊ ፣ የሚያነሳሱ ስሜቶችና አመለካከቶች የበለይነት መያዝ ፤ በዚህ ታሪካዊ ወቅት የሙስሊም አዕምሮ ያለማጣራት ወይንም ለስህተተኛ መክንያቶች ማንኛውንም ነገር መቀበል ።ሌሎች ብዙ አሉታዊ ክስተቶችም አሉ ።

በዚህ ሁኔታ ሱንና ዳግም የዑማውን ጉዳዮች እንዲዳኝና ለዑማ ችግሮች አሳማኝ ምላሽ የሚያስገኙ አዕምሯዊ እርጋታና የራዕይ ጥራት ለማበረታታት የሚቻለው እንዴት ነው? ሙስሊሞች ለዑማው ሕይወትና ተስፋ የሚያመጡ ፣ በኢስላማዊ አላማዎች ዙሪያ ያሉ ማሕበራዊ ኃይሎቻቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ለማነቃቃትና ለማነሳሳት የሚቻለው እንዴት ነው? ይህ ዑማው ማንነቱን እንደገና

እንዲያንሰራራና ስነ-መሰረት ያለውና ልዕልና ያለው የስልጣኔና ታሪክ አካል የመሆኑን ስሜት ለማጠናከር የሚጠቅሙ አማራጭ የባህል ፣ተጨባጭ መህበራዊና እውቀታዊ ፕሮግራም እንዲፈልግ የሚያነሳሳው የተነሳሽነት ስሜት መፍጠር አስፈላጊ ነው ።

**ሱንናን ቃል በቃል የመተርጎም አደጋ**

በነብዩ ዘመን ሰዎች ሱንናን በዕለታዊ ህይወታቸው ውስጥ በሁሉም ገፅታዎች ይተገብሩ ነበር ። ይህን በማድረግም ቁርአንን በግለፅ በተሟላ መንገድ ይገነዘቡ ነበር ።የዚህ ቁርአናዊ ተአምር ተፅዕኖ በዑመተን ወሰጠን ( የማዕከላዊ መንገድ ማሕበረሰብ ) መፈጠር ውስጥ የተመሰከረ ነው ። ይህ ለሌሎች ምስክርነትና መመሪያ ፣እንከን የሌለው ጥሩነት የትኛውንም አይነት ተግዳሮት ለመጋፈጥና ለማሸነፍ ችሎታና ክህሎት የተሰጠው ነበር። በጊዜ ግስጋሴ ወስጥ ግን ሕዝቡ ለሱንና ያለው ግንዛቤ ሲያሽቆለቁል በሌሎች የትርጓሜ መሳሪያዎች ለይ መዝገበ-ቃላት ላይ የተመረኮዘ ባሕል ቅድምያ መያዝ ጀመረ፡፡ ይህ በከባድ ሁኔታ መዝገበ-ቃላትን አቅጣጫ የተከተለ ትርጓሜ ላይ የተመሰረተ የቃል በቃል አቀራረብ አቆጠቆጠ፡፡ ይህ መዝገበ-ቃላት ላይ የተመሰረተ አዝማሚያ የጊዜ-ቦታ ተፅእኖን ከግምት ያስገባ ስላልነበር ለግራ መጋባት ፣ ክርክርና ንትርክና ግጭት ግብዓት በመሆን ዑማውን ህዳሴ ለማደናቀፍ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን አጠናከረ ፡፡

ኢስላምን ወደ ዘመን ያለፈባቸው ምስሎች በማሳነስ በማይመስሉ መሰረቶች ለይ ብዙዎቹ መደምደሚያዎች እንዲቀረፁ በማድረግ ፣ ህዲስን ያስገኙ ተመሳሳይ ክስተቶች ብዙ ጊዜ ሊደጋገሙ እንደሚችሉ በማሰብ ( ይህ እውነተኛው ሕይወት ውስጥ የማይቻል ነው ) አገልግለዋል፡፡

ይህ ከሆነ ታድያ ዘመናዊ የሱንና እስፔሻሊስቶች እነኚህን ጉዳዮች የሚያስተናግዷቸውና የሙስሊሙን አዕምሮ ከአደጋዎቻቸው የሚጠብቁት እንዴት ነው? የሙስሊም አዕምሮ ኢስላማዊ መልዕክትን ከይዘቶቹ ባዶ ለማስቀረትና ከሁሉ-አቀፍ ባሕላዊና ስልጣኔየዊ ሚና ለማስወገድ ከተቃረቡ ተፅዕኖዎች ለመታደግ የሚቻለው እንዴት ነው?

እነኚህ ሕዝቦች ኢስለምን ወደ ግላዊና ባህሪያዊ ጉዳይ ያሳነሱ ፣ ራዕዩንና ማጣቀሻውን ወደ ጥቃቅን ፣ ሰው ሰራሽ ሃሳቦችና ወደ ፀሎታዊ የሐይማኖታዊ ፊደል ተከታይነት የገደቡ ናቸው፡፡ የዚህ አይነት አቅጣጫ ለእውነተኛ ኢስላማዊ ሕብረተሰብ መከሰት ፣ ለሕዝቡ አንድነትም ሆነ ለስልጣኔ ግንባታ ምቹ አይደለም፡፡

**ለዑማዉ ተሃድሶ የሱንና ሚና**

ያለ ምንም ጥርጥር ዑማችን ዛሬ ለሰው ዘር ግንባር ቀደም የማዕከላዊ መንገድ የቀድሞ ደረጃውን ለመመለስ የሚያስችለው የተሟላ የህዳሴ ዕቅድ በከፍተኛ ሁኔታ አስፈላጊ ነው፡፡ ሙሰሊም ማሕበረሰቦች አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎች የሚያሟሉ ከሆነ ደግሞ ይህ ሊሳካ አይችልም ፡፡ ከእነኚህ ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ የመጀመሪያው ለኢስላማዊ ህዳሴ የሚውል እውቀታዊና ባሕላዊ የላዕላይ እቅድ ማቋቋም ነው፡፡

ዑማው ዛሬ ከሁለት ባሕሎች የሚሳብ ነው ፡- የታሪካዊው ዘመን ባሕሪያት የያዘ የተወረሰ ባሕልና የተገኘበት አካባቢና ከውጭ የገባ ባዕድ ባሕል፡፡ የሙስሊም አዕምሮ እነኚህ ባሕሎችን በተመለከተ ንቁ አይደለም ፡፡ ምርቶቻቸውን በመሸመትና የራሱ የሆነ ምንም አዲስ ነገር ባለማበርከት የተብቃቃ ነው፡፡

የማሕበራዊ ለውጥ አላማዎችና ዘዴዎች ለዑማው ኢስላማዊ የሕይወት መንገድ በማገናኘት የሚፈለገውን ባሕላዊ እውቀታዊ ትራንስፎርሜሽን ( ለውጥ ) ለማስገኘትና ዑማው ይህን ከባድ ሐላፊነት እንዲሸከም የሙስሊም ዓለም ኃይሎችን ማንቀሳቀስ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቅም ነው፡፡ ከወቅታዊው የኢስላማዊ አስተሳሰብ ውድቀት ለማገገምና ፣ የአሁኑን ጊዜ ተግዳሮቶች ለማሸነፍ የሚያስችሉ ንቃትና ኃይል ለማግኘት የዑማዉን ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረ ባሕላዊና እውቀታዊ ከበሬታ እንደገና ለማቀዳጀት የማይቀየርሩ የኢስላም ምንጮችን ቁርኣንና ሱንናን ዳግም መመለስ ፣ በጥልቀትና በጥንቃቄ ማጥናትና መመርመር በወቅታዊ ኢስላማዊ አመለካከት በዝርዝር መመልከት ይኖርብናል፡፡ የዚህ አይነት አመለካከት ሁሉን ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ነገሮችንና መጠኖችን ከግምት ለማስገባት ግልፅ ዕይታ ያለውና የተሟላ መሆን አለበት ፡፡ ግቦቹን የሚገልፅ ፣ መሰረታዊ መመሪያዎችን ማብራራት የሚችል ፣ አስቸኳይ ችግሮችን ለመጋፈጥ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማዘጋጀትና ዑማው የሚመሰረትባቸውን እንደገና ለመገንባት ችሎታ ያለው መሆን አለበት፡፡

ቁርኣን ለቀደምት ኣያቶቻችን የአገራት መነሳት ፣ ለስልጣኔዎች መጀመርና መክበም ምክንያት የሆኑ ሕግጋትን ለመገንዘብ፣ ለመገንዘብ፣ ለመተርጎምና ለመተንተን የሚያስችሏቸው ምርጥ እውቀታዊ መዋቅር አሰታጥቋቸዋል፡፡ ይህ መዋቅር ሙሉ በሙሉ ገለልተኛ በሆነ መንገድ እውነታዎችን በጥልቀት እንዲመረምሩ አግዟቸዋል፡ ፡ በቋሚነትና ያለግጭት ነገሮችን ለመፈተሽ የዋለ አቅጣጫ ነበር፡፡ የታሪክ አንቀሳቃሾችን ታሳቢ ያደረገ፣ የሕብረተሰቦችን ውስጣዊ ውጥረቶች ይፋ ያደረገ፣ እንዴትና ለምን እንደተከሰቱ ፣ ክስተቶች እንዴት እንደሚተረጎሙ፣ ከእነርሱ መማር የሚቻሉ ተመክሮዎችና የወደፊት ማመልከቻዎች እንዴት ሊቀርቡ እንደሚችሉና ይሆናሉ ተብለው የሚታሰብ ክስተቶችን ከመከሰታቸው በፊት አገባብነት ያለው እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሁኔታን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

## መደምደሚያ

የነቢዩ ሱንና፣ የሕይወት መንገዳቸውን እንዲሁም የቅርብ በልደረቦቻቸው ሕይወት የሚወክለው ያንን ገለልተኛ፣ የዚያ እውቀታዊ መዋቅር ተጨባጭ አርአያነትን ነው፡፡ ለተላቁ እውቀታዊ ዉድቀት የቅርብ ገዜ መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው ወቅታዊ ኢስላማዊ አስተሳሰብ ቁርኣንን በትክክለኛ ፣ ከጊዜያችን መመዘኛዎች ጋር ተያያዥነት ባለው ምክንያታዊ የአዕምሮ ሁኔታ፣ የሕዝቦችን ሕይወት ከተቀረው ፍጥረት ጋር በስምምነት ማደራጀትና መምራት በሚችል የተሟላ ስነ-ዘዴ መገንዘብና መቅረብ ሲቻል ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ትክክለኛ የሱንና ንባብ፣ የነብዩ የቁርአን መልዕክት ትግበራ እንዲሁም በሕዝቦች ሕይወት ደማቅ እውነታ መድረጋቸው በዑማችን ውስጥ ለተከሰተው የመሃይምነት ጨለማ፣ ጥላቻ፣ ግጭትና የባከኑ ኃይሎችን የሚያስወግድ ነው፡፡ የአሁን ገዜ ሙስሊሞች እራሳቸው በእራሳቸው ላይ ያደረሱ የችሎታ እጦቶችን በማሸነፍና በዘመናዊ ሰዎች እውቀታዊና ባሕላዊ ውስብስብ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈው በትክክለኛ የተሟሉ ኢስላማዊ አስተምህሮዎች ላይ የተመሠረተ እውነተኛ አመራርና ደህንነትን ለአለም ሕዝብ መስጠት የሚችሉት ያኔ ነው፡፡ የዚህ አይነት ግንዛቤ የማይቀየሩ መመሪያዎችን ሊለመዱ ከሚችሉ መመሪያዎች መለየት የሚችሉና በምድር ላይ የሰውን የአላህን ወኪልነት አላማዎችና ዘዴ በትክክል ማሳየት የሚችሉ ሲሆኑ ነው፡፡

## ቁርአንና ዘመናዊ ሳይንስ፡ የስነ-ዘዴ ዕይታዎች

### ዶ/ር ዒማድ አል ዲን ኻሊል

ቁርአንን በጥንቃቄ የሚያነብና ለሳይንስ ያለውን ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ ለመድረስ ጥረት የሚያደረግ ማንኛውም ሰው የሳይንስ ብዙ ገፅታዎች የሚዳስሱ አያቶችን ያገኛል፡፡ የመጀመሪያው ምድብ ከሳይንሳዊ ሐቅ ጉዳዮች፣ ከወሰኑና ይላማዎቹን ከሚዳስስ ነው፡፡ ይህ ሳይንሳዊ ፍልስፍና ሚባለው ነው፡፡ ሁለተኛው ሳይንሳዊ ዕውነታዎችን የማግኛ ስነ-ዘዴን የሚመለከት ነው፡፡ ሶስተኛው በልዩ ልዩ የሳይንስ መስኮች ያሉ ሕግጋትን የሚተገብሩበትን በተለይም ተፈጥሮአዊ ሳይንሶችን የሚዳስ ነው፡፡ አራተኛው በምርምራዊ ስነ-ዘዴ የተገኙ እነዚያ ሕግጋት ሰዎች በምድር ለይ በአላህ ወኪልነታቸው ሕይወትን ለማሻሻልና ለማበልጸግ በላቸው ተልዕኮ በሰዎች እንዲተገበሩ የሚፈቅድ ነው፡፡ እነዚህ የትግበራ ሳይንሶች የሚባሉት ናቸው፡፡

በነኚህ ምድቦች በእያንዳንዳቸው መካከል በጣም የቅርብ ግንኙነት መኖሩ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የሳይንስ ፍልስፍና የሳይንስን አላማዎች ይተነትናል፡፡ ስነ-ዘዴው ዕውነታዎች ላይ ለመድረስ የሚቻልበት የአሰራር ሁኔታ የሚያቀርብ ነው፡፡ ይህም ትዕይንተ ዓለምን የሚያስተዳድሩ ሱናዎችና ሕግጋት፣ ዓለምና ሕይወትን በጊዜ ውስጥ የእነርሱን እንቅስቃሴ የሚያደራጅ ነው፡፡

እነዚህ ሕግጋትና ስርዓቶች በተራቸው ሰዎች የፍጥረትን ድንቅ መዋቅር እንዲያጠኑ ቀመሮችን የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ እነኚህ ለሰው ዘር ዕድገትና ደህንነት ሰዎች የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ይሆናሉ፡፡ ሰዎች ከዕለት ተዕለት ከባድ ምድራዊ የሕልውና ድካማቸው እራሳቸውን ነፃ የሚያወጡበትና ከሌሎች ፍጡራን የሚለያቸውን መንፈሳዊ ፋላጎቶቻቸውን የበለጠ የሚያረኩበት ዘዴ ይሆንላቸዋል፡፡ እንደ ወኪልነታቸውም ለዚህም የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነቶች የበለጠ እንዲወጡና ስልጣኔንና ደህንነት ወደ ዓለም ለማምጣት ሚናቸውን መወጣት ይችላሉ፡፡

ቁርአን እንደ ሳይንስ መፀሐፍ ወይንም እንደ ሌላ መማሪያ መፀሐፍ እንዳልወረደ የታወቀ ነው፡፡ የተወሰኑ ዘመናዊ አሳቢዎች በደራሲያቸው( አላህ) ያልታሰቡ ሳይንሳዊ ፍቺዎችና ትርጓሜዎችን ለአያቶቹ መስጠታቸውም የታወቀ ነው፡፡ ለዚህ በግብረመልስ ሌሎች አሳቢዎችን በሌላኛው ጫፍ ቁርአን ከየትኛውም ሳይንሳዊ

እውነታ ጋር ምንም ተያያዥነት እንደሌለው አጥብቀው ያሳስባሉ፡፡ በሌለ በኩል የማይካደው ቁርኣን ሳይንሳዊ መልዕክትን ሲዳስስ ለውይይት ምንም ዕድል በማይሰጥበት ሁኔታ የተጠቀሱ ዐራት ምድቦችን ሁሉንም ይተገብራል፡፡ ቁርኣናዊ ሳይንሳዊ መረጃ በአጠቃላይ ሁኔታና ከንፅፅሮችና ከተለዋዋጭ ድንበር ውጪ እንደማይገናኙና በመካከላቸው ምንም አይነት ቅራኔዎችና መከለያዎች እንደሌሉ ግልፅ ነው፡፡ ይህም ከአንድ ምንጭ ከስነ-አለምና ትዕይንተ አለማዊ ሕግጋትና ስርዓቶች አስገኚ ከኣላህ በመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም የሰው ዘር በምድር ላይ በኣላህ ወኪልነቱ ለኣላህ ሲል ስልጣኔን ለመገንባት እንደሚያደርግ እጅ በሕግ ማውጣትና የቁርአን መውረድ ሒደት ባለድርሻ ነው፡፡ ቁርኣን በቁርኣናዊ መልዕክትና በትእይንተ ዓለማዊ ህግጋት ላለዉ ወሳኝ ተያያዥነት ትኩረት ይሰጣል። የሰው ዘር ዓለምን በመገንዘብና ሕግጋቶቹንና ስርዓቶቹን ለማወቅ ጥረት በማድረግ ካልጀመረ በቁርአን አስተምሮዎች ወሰን ውስጥ በምድር ለይ የተሰጠውን ሚና እንዴት መወጣት ይችላል፡፡

እዚህ ላይ ዘመናዊ ሳይንስ በሐይማኖታዊ እውነታን እንደ አላፍ ክፍለዘመናት ውድቅ እንደማያደርግ ወይም እንደማይጠራጠር መጠቆም ያስፈልጋል፡፡ ከሚመስለው በላይ ከፍተኛ ደረጃ ባለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ቃልእንዳሌለዉ ዕውቅና ሰጥቷል፡፡ በዚህም የውስን ደረጃ  የሰው ሕይወት (ከቁሳዊ) ነገርና ንቅናቄ ድንበሮች የሚያልፈውን ዋና መጠን ከተቀማ ምክንያታዊነት አይኖረውም፡፡ ሳይንስ አሁን ከሐይማኖት ጋር በስምምነት ወደሚሰራበት ሁኔታው ተመልሷል፡፡ ይህ በቅርብ ጊዜያት ግኝቶች፣ በተለይ ተፈጥሯዊና ኒዩክለር ሳይንሶችና ለሰው ጭንቅላት አሰራር በተገኘ ግንዛቤ ምክንያት በሳይንስ ፍልስፍና ውስጥ የተካሄደ ትልቁ አብዮት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ምርምር የአቶምን አስኳል በማሰስ ሒደት << ቁሳዊ መከለያን>> ለመስበርና መዋቅር በቁሳዊው ዓለም የተገነባባቸውን መንፈሳዊ ገፅታዎችና ንጥረ ነገር ይፍ ለማድረግ ችሏል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሳይንስና ሐይማኖት በብዙ ሁኔታዎች እንደ አዲስ የምናገኝበት ነው፡፡

ስለዚህ በዐራቱ የሳይንስ ገፅታዎችና ቁርኣን ውስጥ ባለው መረጃ መካከል ወደ አለው ግንኙነት በቅፅበት ብንመለከት ምናገኘው ምንድን ነው?

## 1. የሳይንስ ፍልስፍና፣ ዓላማዎቹ እና የኢስላም መሠረታዊ መመሪያዎች

የሳይንስ ፍልስፍና ሳይንስ ለማሳካት የሚያስባቸውን አላማዎችና ግንኙነታቸውን በመመርመርና በመተንተን ላይ ትኩረት ያደርጋል ግንኙነቱ በመጀመሪያ ከሕዝብ ስልጣኔያዊ ጥረቶች በሁለተኛነትም ከትእይንተ ዓለም ጋር ያላቸው ራእይ፣ ከሕይወትና ከሚኖሩበት ዓለም ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ሳይንሳዊ ምርምርና የሚከተለው ምርምራዊ ስነ-ዘዴ ለኢስላማዊ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የሚጠቀም ነው፡፡ ይህም ከዑማው ክንውኖች ፣ በምድር ላይ ካለው ተልዕኳዊ ተፈጥሮና ፣ ለትእይንተ ዓለም ፣ለሕይወት ፣ለአለምና ለሰው ዘር ካለው አጠቃላይ እምነቶች ጋር ጠንካራ ትስስር ያላቸው ናቸው፡፡

እዚህ ላይ ሳይንሳዊ ስነ-ዘዴዎችን ግዴታ የሚያደርጉ ጥቂት መሰረታዊ የኢስላማዊ ሕይወትና ዓለማዊ አመለካከት መርሆዎችን መጥቀስ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም በተረጋገጡ ሳይንሳዊ እውነታዎች የተገኙ ሕግጋተትና ስርዓቶች ናቸው፡፡ የሚተገበሩባቸውን መንገዶች ማየት ያስፈልጋል፡፡ የዚህ አይነት አቅጣጫ እነኚህን መመሪያዎችንለማጠናከር ፣ሉላዊ ኢስላማዊ አመለካከትን ለማጥበቅ ፣የበለጠ ከዓለም እውነታ ጋር ለማገናኘትና ለስልጣኔ ንቁ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለዚህ በእኛ አስተያየት ለአንድ ሳይንሳዊ እንቅስቃሴ ዐራት መሰረታዊ መመሪያዎች ያስፈልጋሉ ፡-

ሀ. እስቲኸለፍ ወይንም ኺላፋህ

ኺላፋህ ፡- የሰው በኣለህ ወኪልነት መሰየምና የመንግሥት በነቢዩ ዓለማዊ መንግሥት ቀጣይነት መሰየም ነው፡፡ኸሊፋህ (ብዙ ቁጥር ኹላፋ) ፡- በቦታና በጊዜ ውስጥ የኣላህ ወኪል፡፡

የሰው ልጆች መለኮታዊ አደራ (አማናህ) መሸከም በምድር ላይ ለፈጣሪ ያለውን ኺላፋ ወይንም ወኪልነት ይወክላል፡፡ በቁርአንና በሱንና የተጠቀሰው የኺላፋህ መመሪያ ሳይንስ ከሚደግፋቸውና እውነታ እንዲሆኑ ከሚያስችሏቸው መመሪያዎች አንዱ ነው፡፡ ሙስሊሞች በምድር ላይ የአላህ ወኪሎች ወይንም ኩላፋህ የሆኑት እንዲያለሟት፣ ወደ እርሷ ስልጣኔ እንዲያመጡ ፣ችግሮቿ እንዲጋፈጡ፣ ከተመፃዋችነት ነፃ የሆኑ ሁኔታሆችን እንዲፈጥሩ፣ ለከፍተኛ ስኬቶች ምቹ የሆነ ምቹ ሕይወት እንዲያስገኙ ነዉ፡፡ ይህም በከፍተኛ ፍላጎት ወደ አላህ መመኘት ነው፡፡

ሰዎች ሱናን (ሕይወትን፣ ስነ-ዓለምን የሚያስተዳድሩ ትዕይንተ ዓለማዊ ህግጋት) ለማግኘት ሳይንሳዊ የምርምር ስነ-ዘዴዎችን ካልተጠቀሙ እንደ ወኪልነታቸው ስራቸውን ማከናወን አይችሉም፡፡ የማይቋረጥ ዕድገት ለማስገኘት ያላቸው አላማዎች ላይ ለመድረስ የሚያስችሉአቸው በቂ ዋስትናዎችና ድጋፍም ለማግኘት አይችሉም፡፡

የኃይል ክምችታቸው ጉልበት ለማግኘትና በእራሳቸውና በአካባቢያቸው መካከል የበለጠ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚችሉትም የዚያን ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የኺላፋህ መመሪያ በተጨባጭ ምክንያት ላይ ያልተመሰረተ ሃሳብ ወይም ምንም ነገር በሌለበት ባዶ ቦታ የሚከናወን የሐይማኖት ሕግጋት ከመሆን አያልፍም፡፡

ለ. ተዋዙን (ሚዛን)

ተዋዙን ወይንም በሰዎች መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶች መካከል ያለ ሚዛን ከኢስላማዊ ሕይወትና አስተሳሰብ መሰረታዊ መመሪያዎች አንዱ ነው፡፡ በቁርአንና በሱንና ውስጥም በጥልቀት ስር የሰደደ ጉዳይ ነው፡፡ በብዙ ገፅታዎች ቅርፆች የምናገኘው ነው፡፡

በዚህ አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ እራሱን ይፋ ያደረገ እውነታም እንመለከታለን፡፡ ይህም አላህ በውስጧ በሚኖራቸው ሚና መጠን ምድርን ለሰዎች ገር ማድረጉ ነው፡ ፡ አላህ ሰዎችን በተወሰነ ቅርፅ ፈጥሮ የተፈጥሯቸውን ፍላጎት እንዲያሟሉባት መግራቱ እውነት ሆኖ ሳለ ሌሎች መለኮታዊ ሐይማኖቶች መንፈሳዊና ቁሳዊውን መለያየታቸው ሙሉ በሙሉ በኢስላም ተቀባይነት የሌለው ድብቅነት የሌለው መቃረን ነው፡፡

ይህን በማድረጋቸውም ኃለኛውን (ቁሳዊ ነገሮችን ) በማፈንገጣቸው ውጤቱ በሰዎች ተፈጥሯዊ ፍላጎቶችና ለእነርሱ የተነገሩ የምድር ፍሬዎችና ጠቀሜታዎች መካከል መከለያዎች እንዲዘረጉ ሀኗል፡፡

እውነታው በሰው ሁለቱ ተፈጥሯዊ ጎኖች መካከል ትክክለኛ ሚዛን ከሌለ ትርጉም ያለው ኢስላማዊ ሕይወት ሊኖር አለመቻሉ ነው፡፡ ይሁንጂ የኢስላም አላማ በእውነታው ድንበር ውስጥ በመንቀሳቀስ ለድርጊት ፣ለለውጥ ፣ለዕንቅስቃሴ ብቁ የሆነ ፤ከወጥረት፣ ጥመት ወይንም ንፍገት ነፃ የሆነ ሚዛናዊ ሰው መፍጠር ነው፡፡

ይሁንጂ ይህ ሚዛናዊነት ያለው ( በዓለም ውስጥ ያለ የትኛውም ሐይማኖት ወይም አመለካከት በዚህ ጀረጃ በጠቅላላውና በቁርጠኝነት ያልተቀበለው) ይህ ሚዛናዊ ራዕይ ሳይንሳዊ ስነ-ዘዴዎች ፣እውነታዎችና መተግበሪያዎች በሌሉበት ሥራ ላይ መዋል አይችልም፡፡

ሐ. ተስኺር (ትህትና)

ይህ የኢስላማዊ የትእይንተ ዓለምና ሕይወትና ራዕይ ሌላኛው መሰረታዊ ባህሪይ ነው እዚህም ያለ ጥርጥር ይህ ራዕይ እውነታ ሆኖ ልዕልና ያለው እምቅ ኃይሉን ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ሳይንስ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ኢስላማዊ ዕይታ ተፈጥሮና ስነ-ግላዊ ሰዎችን እንዲያገለግሉ ተደርገዋል፡፡

አላህ ሕግጋትን ፣ስርዐቶችንና ችሎታዎች ሰዎች በወኪልነታቸው ለሚያከናውኗቸው መሰረታዊ ሥራዎች በሚመጥን ሁኔታ ከተፈጥሮ ጋርበአዎንታዊና ውጤታማአብረው እንዲሰሩ ዘርግቷቸዋል፡፡

ከዚህ አብሮነት ጋር የኢስላም ዓላማ<< የመካከለኛ መንገድ >> ስነ-ዘዴ ሃሳብ ነው፡፡ ተፈጥሮ ለሰው ፍላጎቶች የተገራች የመሆኗን መርህ ለሰዎች ይፋ ታደርጋለች፡ ፡ በተመሳሳይ ጊዜ ግን በእሴቶች፣ በመመሪያዎችና በስምምነቶች በሰው ሁለቱ ተፈጥሯዊ ጎኖችን የአብሮነት መመዘኛዎች ዘርግታለች፡፡ እነኚህ የተቀረፁት ሊቻል የሚቻለውን ከፍተኛውን የፈጠራ ደረጃ ለማስገኘትና በትዕይንተ ዓለም ውስጥ ከሰዎች ከፍ ያሉ ምኞቶች፣ ስነ-ምግባርና ክብር ጋር በከፍተኛ ደረጃ የሚመጥኑ ስልጣኔያዊ ጥራቶችን ለመቅረፅ ነው፡፡

ኢስላም የሳይንስ እምቅ ኃይል ስነ-ዘዴዎቹን፣ እውነታዎቹንና የሳይንስ መተግበሪያዎችን መጠቀም ካልቻለ የትኛውም ኢስላማዊ ሕብረተሰብ የተስኺር መርህን በመተግበር ወደ ታሪካዊ እውነታ መቀየር አይቻለውም፡፡

መ. በፍጥረትና በፈጣሪ መካከል ሊኖኖር የሚገባ አስፈላጊ ግንኙነት

በመጨረሻ ሳይንስ ከኢስላማዊ የዓለም አመለካከት በጣም ወሳኝ መመሪያዎች አንዱን በልዩነትና የሐይማኖቱን በአጠቃላይ ለመመስረት መዋል አለበት፡፡ ይህ በአስደናቂው የፍጥረት ስርዓትና በፈጣሪ መኖር መካከል አስፈላጊ ማያያዣ ነው፡፡ ሳይንስ ይህንን መያያዝ ይፋ የሚያወጣና ግልፅ የሚያደርግ ነው፡፡የፍጥረት ተአምርን በተመለከተ ብዙዎች ፅፈውበታል፡፡ ብዙ ሳይንቲስቶችና ምዑራን በሳይንስ ታሪክ ውስጥ ከማያከራክር ዋና አውነታዎች አንዱ በሆነው ፡-ፍጥረት

ፈጣሪ ያለው መሆኑ ላይ ለመድረስ ሕይወታቸውን አሳልፈዋል፡፡ ይህ ጉዳይ አሁን በወሳኝ ሁኔታ ምላሽ ያገኘና ጥያቄ ለመጠየቅ የሚያስችል አይደለም፡፡ትዕይንተ-ዓለም በዕንቅስቃሴው በተደራጀ፣ በትክክለኛነት፣ ሰምምነት ባለው ዕንቅስቃሴና በሚገነባ ውስጣዊ ተያያዥነት ስለሚሰራ መነሻው መነሻውና ምንጩ ልዕለ ተፈጥሯዊ፣ ምሉዕ-ኃይል ያለውና መሪ ፈቃድ መሆን አለበት፡፡

ስለዚህ ሳይንሳዊ ምርምር የትዕይተ-ዓለምን፣ የዓለምንና የሕይወትን ሚስጥራት የማሰስ ወሳኝ ተግባር በማከናወን እስከ ቀጠለ ድረስ ለኢስላማዊ ሕይወት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም በበለጠ በሚያሳምን ሁኔታ ወደ ስነ-ዓለም ሰሪ የሚያቀርቡ ነው፡፡ ወደ ፈጣሪ በዛረ መጠንም ከእራሱ የማምለክ ድርጊት ጋር የተመሳሰለ ይሆናል፡፡

## 2.ስነ-ዘዴው

በዚህ አግባብ ቁርኣን ለስነ-ዓለም ሕግጋት ግኝት የሚረዳ ስነ-ዘዴን አስቀምጧል፡፡ ይህ ስነ ዘዴ ተለዋዋጭና የተሟላ ፣በጊዜና በቦታ የሚለዋወጡ ነገሮች ተፅዕኖ ውስጥ የማይወድቅ ነው፡፡ ይህም ለምርምርና ጥናት ጥብቅ ዘዴና መሳሪያ ስለሆነ ነው፡፡ ተነፃፃሪ ለውጦችን አልፎ የሚሔድና በሁሉም ዘመንና አካባቢ በቋሚነት ዋጋ ያለው ነው፡፡ ቁርኣን ሰዎች የሕልውናቸውን እውነታና በትዕይንተ ዓለሞቻቸው ውስጥ ያላቸው ቦታ በተመለከተ ጥልቅ እይታ እንዲኖራቸው አጥብቆ ይመክራል፡፡ ስሜቶቻቸውን በመጠቀም ከቆሙበት ምድር አንስተው ዙሪያቸውን ከመቃኘት እስከ የአዕምሮና የትዕይንተዓለም አድማሶች እንዲመለከቱ ይጋብዛል፡፡ ለሰዎች ከፍተኛዎቹ የኢማን ክበቦች ላይ መድረስ ምነኛ መልካም አስተሳሰብ ነው፡፡

ኢማን፡- አላህ በእርግጥ ብቸኛ አምላክ መሆኑንና ነብዩ መሀመድ(ሰዐወ) የእርሱ የመጨረሻ ነቢይ መሆናቸውን የማመን ፅኑ እምነትና እርግጠኝነት ነው፡፡

ቁርኣን ሙስሊሞች በምርምር፣ በማሰላሰል፣ በእውቀትና በልምድ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእያንዳንዳቸው ለይ ለስሜቶች መሰረታዊ ሐላፊነት ሰጥቷል፡፡

ቁርኣን ተጨማሪ እርምጃ በመራመድ የሰው ልጆች ከልምድ የተገኙ እውቀታቸውን ስሜቶቻቸውን በሙሉ በመጠቀም ገደብ የለሽ መረጃ እንዲቀበሉ ነግሯቸዋል፡፡ በዚህም የማገናዘብ ኃይላቸው በትእይንተ ዓለም ሕግጋት በስተጀርባ ያለው እውነታ ላይ ለመድረስ የሚያስችሏቸውን መረጃ ለመመዝገብ ፣ለመለየት፣ለመቀበል ወይንም ውድቅ ለማድረግ ያስችሏቸዋል፡፡

አዕምሯዊ ችሎታ፣ ከህሎትና በልምድ የተገኘ ጥበብ፣ ዕውቀትና ስሜት በጥምረት ጥናትን፣ ምርምርን፣ በእውነት ላይ የተመሰረተ ምክንያታዊነትና ውሳኔ ሰጭነት የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ሰዎች የሚፈተኑትም በዚህ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በመሰረታዊነት ሰዎች ከሌሎች ሕያዋን ፍጡራን የተለዩ በመሆናቸው ነው፡፡ የመስማት ፣የዕይታና በልብ ውስጥ ያለ ስሜት(አል ፉአድ) በጥምረት ለሰው ሕይወት ጥምረት የሰጡ፣ ሰው ልዩ ፍጡር እንዲሆን ያደረጉ መሆናቸው ደጋግመው የሚገልፁ ብዙ የቁርአን አይነቶች አሉ፡፡ ሰዎች እነኝህን ኃይሎች በስፍት ቢያንቀሳቅሱና በተሟላ ሁኔታ ሥራ ላይ ቢያውሉ በሳይንሳዊና በሐይማኖታዊ የበላይነት ጫፍ ላይ መድረስ ይችላሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ከፍታ የስነ-ዓለም ጌታዎች በሚያደርጓቸውና በምድላይ የአላህ ወኪል የመሆናቸው ክብር የተገባቸው ያደርጋል።

በሌላ በኩል እነኚህ ኃይሎች የሚያቀዘቅዙ ከሆነ ለእራሳቸው ያነሰ ክብር የመረጡ ይሆናል፡፡ ይህም አላህ የመስሚያ፣የእይታና፣ ልቦናዊ ስሜት ሰጥቷቸው እያለ እጣ ፈንታቸው ያላደረገላቸውን ደረጃ የመረጡ ይሆናሉ፡፡

ሰዎች አዕምሯዊ የማሰብ ችሎታቸውን እንዲያነቃቁ የሚመክሩ ሌሎች ሃምሳ የሚሆኑ አያቶች አሉ፡፡ አዕምሯዊ የማሰብ ችሎታ በእሱ ውስጥ ያለ የእምነት ወሰንን እንዲገነዘቡባቸው በአላህ የተሰጣቸው ቁልፍ ነው በተጨማሪ አያት ሰዎች በሚኖሩበት ዓለም ውስጥ በዙሪያቸው ያሉ ክስተቶችን በተመለከተ ለረጅም ጊዜ በጥልቀት ፣በማገናዘብና በኃላፊነት እንዲያስቡ ይጋብዛሉ፡፡

ስለ ማሰላሰል የተነገረ ነገር ሁሉ እውቀት ለማግኘትም የሚውሉ ናቸው፡፡ ዕውቀት ከማሰላሰል የሚያልፍ እውቀታዊ እርምጃና ውጤቱ ነው፡፡ ዕውቀት መጎናፀፍ ለሰዎች በዙሪያቸው ያሉ ነገሮችን በተመለከተ የተሻለ ንቃት ይሰጣቸዋል፡፡ የማንነታቸው ገፅታዎችና ከትዕይተ-ዓለም ጋር ያላቸው ግንኙነት በተመለከተም ጥልቅ ግንዛቤ ይሰጣቸዋል፡፡ ሁልጊዜ ግንዛቤያቸውን ይሰልላቸዋል፡፡ ማናቸውንም የሚገጥሟቸውን ጉዳዮች፣ክስተቶች ወይንም ችግር በሐላፊነት ለመቅረፍ ያላቸውን ዝግጁነት ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ቁርኣን አንድ ሰው በእውነተኛ ምክንያታዊነት ፣ንፅፅር፣ መዘናና ጥናት ላይ በመመርኮዝና፣ ስምምነት ላይ በተደረሰባቸው ውጫዊ መረጃዎች በመታገዝ እንዲሁም በዚህ መስክ የበለጠ ተፎካካሪነት ባላቸዉ ሰዎች እውቀታዊና አሳማኝ ኃይሎችን በመጠቀም ተቀባይነት ባላቸው ወጤቶች ለይ

ለመድረስ የሚያስችሉ ሊከተሏቸው የሚገቡ ዘዴዎችን ከእነ ማረጋገጫቸው፣ ሙግት እውቀታዊ ክርክሩ ትኩረት ሰጥቶታል፡፡

ቁርኣን ዒራም (እውቀት/ሳይንስ) የሚለው ቃል የሚከተሉትን ሃሳቦችን ለመግለፅ መጠቀሙን ማስተዋል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ (ሀ) አላህ ለነቢያቱ ያስተማረዉ ዲን ዲን፡- አላህ ለሰዎች ያዘዘው እንከን የሌለው የተሟላ እምነትን፣ ስነ-ምግባርን፣ ሕግን፣ መስዋዕትነትን፣ ተቋማትና ፍርድን ያቀፈ ሐይማኖት ነው፡፡

(ለ) አላህ ስነ-አለም በቅንጅት እንድትንቀሳቀስባቸው ያስቻላት ሱነኖች (ሕይወትን፣ ስነ-ዓለምን የሚያስተዳድሩ ትእይተ ዓለማዊ ሕግጋት)፤እና

(ሐ) በአያቶቹ የታቀፉ ትላልቅ እውነታዎች ናቸው፡፡

ዒራም የተገለፁ ሐይማኖታዊ አሴቶች አመልካች እንደሆነም ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም ዒራምና ዲን በቁርኣናዊ ቋንቋ ተመሳሳይና ተጨማሪ ልዩ ትርጓሜዎች አሏቸው፡፡ የአላህ ቃላት ይህን እውነታ የሚያስተምሩና በሚታዩና በሚጨበጡ እውነታዎች ብቻ በሚያምኑ ፈላስፋዎችና ሰዎች ከተገኙ በቂ እውቀትና መረጃ የሌላቸው  አስተያየቶችና ምክንያት የሌላቸው  ጥላቻዎች ፍቺዎች የበለጠ አላህ ዒራምና ዲን እንዲያስተላልፉ የሚያስፈልጓቸው ሰፊ ፣የተያያዘ-ስሜቶችን እንድንገነዘብ የሚያስችል ኢራም ከሚለው ቃል የወጡ ብዙ ሃሳቦችን ከ750 በሚበልጡ አያቶች ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ቁርኣን ቁሳዊና ሕይወታዊ፣ እውነታዊና እውቀታዊ ክስተቶችን ለማጥናት ሙሉ በሙሉ ሳይንሳዊ አቅጣጫ መከተል አስፈላጊ መሆኑን ትኩረት ሰጥቶታል፡፡ በዚህ አቅጣጫ ለይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚኖራቸው እንደ ጥላቻዎች፣ በቂ እውቀትና መረጃ ላይ የተመሰረቱ አስተያየቶችን ፣ ጥንቆላንና ባዕድ አምልኮን በግልፅ ውድቅ አድርጓል፡፡ እነኚህ ኢ-ሳይንሳዊ ክንዋኔዎች ሰዎች ሊከተሏቸው ዲኑ ከሚፈልገው ፣ አላማዎቹ ላይ ለመድረስ መከተለ ካለባቸው ቀጥተኛ መንገድ ያፈነገጡ ናቸው፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው ቀጥተኛው መንገድ በሁለት ነጥቦች መካከል በጣም አጭሩ ርቀት ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ መንገድ ማፈንገጥ ርቀትና ችግርን ይጨምራል፡፡ ተጓዦች አላማዎቻቸውንና ግቦቻቸው ላይ እንዳይደርሱ አቅጣጫ ሊያስለውጣቸውም ይችላል፡፡ ቁርኣን ደጋግሞ ይህንን ግልፅ እውነታ አጥብቆ ሲናገር ከጥላቻ ሊገኝ የሚችል ነገር ዋጋቢስነትና አይነስውርነት መሆኑና ለእውነታ ብቸኛው አማራጭ ስህተት እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

## 3. **እውነታዎች**

በቁርአን የቀረበው ሶስተኛው ገፅታ በልዩ ልዩ የሳይንስ መስኮች እንደ የስነ ፈለክ ጥናት፣ ጂኦግራፊ፣ የዕፅዋት ሳይንስ ፣ ባዮሎጂ ፣ሰብአዊ ፊዚዮሎጂ ያሉ በዙ እውነታዎችና ስርዓቶችን ነው፡፡

በዚህ ረገድ ብዙዎች ዘመናዊ አሳቢዎች እና/ወይንም አብራሪዎች ከሁለቱ ተቃራኒ ተቋሞች አንዱን የያዙ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አቋም የቁርአንን አያቶች ለማብራራት በዘመናዊ ሳይንሳዊ መረጃዎች እምነት መጣል አስፈላጊ መሆኑን የሚናገር ነው፡፡ ይህ በዚህ ሒደት የሚገኙ ስነ-ዘዴያዊ ስህተቶችን የሚያካትት፤ አጠቃላይ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ከፊል መረጃ ስራ ላይ የሚዉልበት ፣ተለዋዋጭ መረጃዎች ቋሚ ሕግ ለማውጣትና ንፅፅራዊ መረጃዎች እንከን የሌለው ሕግ ለመቅረፅ የሚውሉበት አቅጣጫ ነው፡፡የዚህ አቅጣጫ ድክመት እነኚህ ያልተሟሉና ተነፃፃሪ መረጃዎች ሲቀየሩ የዚህ አቋም ደጋፊዎችን የሚያስከፉ መሆናቸው ነው፡ እራሳቸው ሳይንቲስቶች ማረጋገጥ እንደሚችሉት መረጃዎች የዚህ አይነት ዝንባሌ አሏቸው፡፡ ከዚህ ዕጣ ፈንታ ወጪ ያለው ሁለተኛው አቋም ሳይንሳዊ መረጃዎችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረግ ወደ ተሳሳተ የአስተሳሰብ ወጥመድ የሚመደብ ነው፡፡

በሕይወታችን እያንዳንዷ ስፍራ ውስጥ መውሰድ ያለብን ቁርአን የሚያስተምረን ለትክክለኛ ስነ-ዘዴ በጣም የቀረበ ስነ-ዘዴ መካከለኛ አቋም ነው፡፡ ተለዋዋጭ መረጃዎች ለሚኖረው ሳይንስ እራሳችንን ሙሉ ለሙሉ መስጠት የለብንም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ሳይንስ ሚና የሚኖርበት እያንዳንዷን ትርጓሜ በአጠቃላይ ውድቅ ማድረግ የለብንም፡፡

ችሎታና ክህሎት ያላቸው ቁርአንን የሚተረጉሙና የሚያብራሩ ምሁራን በሁለቱ የማስተካከያ ጎኖች፡- በቁርአናዊ ኢያህ እና በሳይንሳዊ ጥናት መካከል ያለው ተያያዥነት ተፈጥሮ ለመረዳት በሰነጠሉባቸው የራሳቸው መስክ አዕምሯዊ እውቀት፣ ችሎታ፣ ክህሎትና ልምድ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በቅርብ የተጀመሩ ዘመናዊ ቁርአናዊ ትርጓሜ ዝንባሌዎችንም መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነኚህ አዝማሚያዎች የቁርአንን ፍቺዎችና ይዘት ለመገንዘብ ሙያዊ ቃለትና አዕምሯዊ ምስሎችን የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ አቅጣጫ አል ተፋሲር አል በያኒ ሊ አል ቁርአን ይባላል፡፡ ይህ ዘዴ በቁርአንን የሚተረጉሙና

የሚያብራሩ ዑላማዊ ምሁራን በቁርአን ለማስተላለፍ የታሰበው የቃላትና የሐረጎች ፍቺዎችን ለማወቅ ለማወቅ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ተርጓሚዎች ከግነት ወይንም ከስህተት የሚጠብቃቸውና ገለልተኛ ዋስትናዎችን የሚሰጣቸው ዘዴ ነው፡፡

የማይለወጡ ህግጋት ወይንም የማያከራክሩ በእራሳቸው ግለፅ የሆኑ የተወሰኑ ሳይንሳዊ እውነታዎችም አሉ ለምሳሌ ዝናብ በማስገኘት የንፋሶች ሚና፣ በፀሃይ ስነ-ፈለካዊ ስርዓት እንቅስቃሴዎች የስበት ሚና፣ የሽል(የሽል) አካላዊ መዋቅር ደረጃዎች ወይንም ከጋዝ የተሰሩ ነገሮች ከምድረ-ገፅ ያላቸው  በጨመረ ወይም በቀነሰ መጠን የሚያሳዩት የመጠን ለውጥ ወዘተ፡፡

ከእነኚህም ውጪ ቁርኣን በሚወርድበት ወቅት ዐረቦች ሳይንሳዊ ተፈጥሯቸውን ያላወቀቋቸው  ብዙ ሌሎች ሳይንሳዊ እውነታዎችም አሉ፡፡ እነኚህን እውነታዎች የሚመለከቱና የሚያረጋግጡ የቁርኣናዊ አያቶች ትርጓሜ ቢያንስ በቅርብ ክፍለ ዘመናት በራሳቸው ይፋ በሚሆኑ ሳይንሳዊ እውነታዎች ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ከቁርኣን ብዙ ተአምራዊ ገፅታዎች አንዱን ግልፅ ያረጉ ናቸው፡፡

ከእውነታ ወይንም ሐቅ ከአንድ በላይ የሆኑ ገፅታዎችን የሚያሳዩ ሳይንሳዊ ተጨባጭ እዉነታዎች ወይንም ነገሮች አሉ፡፡ ይሁንጂ እነኚህ ገፅታዎች ሁሉም በአንድ ነጠላ፣ ተለዋዋጭ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው ፋይዳቸውን ለመረዳት በመስቀለኛ ማጣቀሻነት ከሌሎች ቁርኣናዊ አያቶች አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የሰማያት ተዐምራዊ መዋቅር አንድ ለይ የተያያዘውና ከመበታተን የሚጠበቀው በአንዳች ስርዓት መሆኑን የሚያረጋግጡ አያቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይሁንጂ እንደ <<ተረጋገጡ>> ሕግጋት ወይንም በተጨባጭ የሚታዩ እውነታዎች በውይይት ወይንም በግምገማ ደረጃ ያሉ ቲዮሪዎችን ያልተረጋገጡ በመሆናቸው በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያዙና በየትኛውም የተወሰነ --- ለማብራራት በተርጓሚውና በአብራረው ስራ ላይ የማይውሉ ናቸው፡፡ በቋሚነት የሚለዋወጡ ሳይንሳዊ መረጃዎችን በተመለከተ በጥንቃቄ መጀመርና የሚከተሉትን ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ማስቀረት አስፈላጊ ነው፡፡ (ሀ) ሙሉ በሙሉ ከማፅደቅና (ለ) ሳይንሳዊ ትርጓሜ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረግ፡፡ለሳይንሳዊ ትንታኔ ሙሉ በሙሉ ትኩረት መስጠት በሁሉም ደረጃ ሊኖሩ የሚገባቸውን ትክክለኛ ግንዛቤ፣ ንቃትና ቀጣይ

ጥናቶችንና ምርመራን የሚያዛባ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ፍፁም ውድቅ ማድረግ ለማገናዘብ የሚኖር ችሎታን ያደክማል፡፡ በዘመናዊ ሰዎችና በቁርአን ውስጥ ባለው የመረጃ አንድ ገፅታ ላይ መከለያዎችን ሊፈጥር ይችላል፡፡

ሰዎች በአላህ እንዲያምኑ እንደ ማረጋገጫዎች የታቀዱ ሳይንስ-ነክ መረጃዎች በቁርአን  ውስጥ በብዛት የሚገኙ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ በአንድ ሳይንሳዊ አርእስት ላይ የቀረበ ጉዳይ ለመጪዎቹ ትውልዶችም የታሰብ አለመሆናቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡ በወሕይ ወቅት አይታወቁም ማለትም አይደለም፡፡ ሁለት አይነት አያቶች አሉ፡- አንደኛው አይነት መረጃን የሚያስተላልፍና ወደ አላህ ፍጥረት ልዕልናዎች፡-ትዕይንተ ዓለም፣ ዓለምንና ሕይወት ትኩረትን የሚመራ ነው፡፡የዚህ አይነት በህይወት ወቅትም ሆነ በሌላ በየትኛውም ዘመን በደንብ የሚታወቁ ተጨባጭ እውነታዎችና ክስተቶችን የሚያቀርብ ነው፡፡ በየትኛውም አይነት በወሕይ ወቅት ይታወቁ ያልነበሩ ነገር ግን በዘመናት ውስጥ ሳይንስ ይፋ ያደረጋቸው በተጨባጭ ሳይንሳዊ እውነታዎችን፣ ስርአቶችንና ሱነኖችን የሚመሩ አመለካከቶችን ያቀፈ ነው፡፡ ይህ የአያቶቹ ምድብ ብዙውን ገዜ ሳይንሳዊ ተኣምርና አስደናቂ የቁርአን ተፈጥሮ በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡

ቁርኣን የሳይንስ የመማሪያ መጽሐፍ ስላልሆነ ሁሉንም ሳይንሳዊ ተጨባጭ እውነታዎች ይፋ ያደረገ ወደ ሌሎችም ብዙ እውነታዎች መጠቆሚያዎችን ያቀረበ ነው፡፡ ሰዎች  በእራሳቸው የበለጡ እውነታዎች ላይ እንዲደርሱ ነፃነት የሚሰጣቸው ለተመራማሪዎች ስነ-አዕምሯዊ ምሕዳር ይፈጥራል፡፡ ነገር ግን እነኚህን ግኝቶች መከተል የሚያስፈልገው በሐይማኖታዊ ፅናትና ቁርጠኝነት ሊሆን እንደሚገባ ቁርኣን ያሰምርበታል፡፡

## 4. **ትግበራ**

በቁርኣንና በሳይንስ መካከል ያለውን ዐራተኛ ገፅታ ስናስተውል ሕይወትን ለማሻሻልና በሁሉም ደረጃ የሰብዓዊ ስልጣኔ ጥራት ከፍ ለማድረግ ሳይንሳዊ ተጨባጭ እውነታዎችንና ግኝቶችን መጠቀም አስፈላጊ  መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ ሰዎች በጊዜና ቦታ በሁሉም ስፍራ ከሚገኙ ሳይንሳዊ መረጃዎችን መጠቀም እንደሚገባቸውና በሚኖሩባቸው ዘመን ላለ ስልጣኔ ማዋል የሚጠራ ሰፊ፣

ተለዋዋጭና ቋሚ አቋም ነው፡፡ ይህ ከሆነና በሚታወቁት ሳይንሳዊ ተጨባጭ እውነታዎች የስልጣኔ ሁኔታ ዕድገቶች ካሉ ቁርኣን በሁሉም ትውልድ የሚታሰበውን ውጤት ሊያመጣ በሚችል ሁኔታ ተፈላጊ እንደሚሆንና በአዳዲስ እውነታዎችና በአዳዲስ ሁኔታዎች በመመስረት በየዘመኑ የሚኖሩ ትውልዶች የተሻለ ለውጦች እንዲያስገኙ ሊያነሳሳቸው ይችላል፡፡

በመሆኑም በቁርኣንና በሳይንስ መካከል ወደ አለው ይህ ዐራተኛ የግንኙነት ገፅታ በመመልከት ቁርኣን የምዕመናንን ማህበረሰብ በተሻለና በበለጠ ሁኔታ ሳይንሳዊ ተጨባጭ እውነታዎችን፣ ግኝቶችና ቀመሮችን መጠቀም እንዳለባቸው ቁርኣን በቋሚነት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ጥሪ የሚያደርግ መሆኑን እንረዳለን:፡

وَحَآجَّهُۥ قَوۡمُهُۥۚ قَالَ أَتُحَٰٓجُّوٓنِّي فِي ٱللَّهِ وَقَدۡ هَدَىٰنِۚ وَلَآ أَخَافُ مَا تُشۡرِكُونَ بِهِۦٓ إِلَّآ أَن يَشَآءَ رَبِّي شَيۡـٔٗاۚ

وَسِعَ رَبِّي كُلَّ شَيۡءٍ عِلۡمًاۚ أَفَلَا تَتَذَكَّرُونَ ٨٠ الانعام: 80

ወገኖቹም ተከራከሩት፡፡ «በአላህ (አንድነት) በእርግጥ የመራኝ ሲኾን ትከራከሩኛላችሁን በእርሱም የምታጋሩትን ነገር አልፈራም፡፡ ግን ጌታዬ ነገርን ቢሻ (ያገኘኛል)፡፡ ጌታዬም ነገሩን ሁሉ ዕውቀቱ ሰፋ፡፡ አትገነዘቡምን» አላቸው:፡(ቁርኣን 6:80)? ???

ቁርኣን ሙስሊሞች እራሳቸውን ከጠላቶቻቸው የሚከላከሉበትና በምድር ላይ ያሏቸውን ሚናቸውን የሚያስከብሩበት ጥንካሬ እንዲኖራቸው የሚጠይቃቸው ነው፡፡

ይህ ጥሪ በሁሉም ጊዜና ቦታ አስቸኳይነትን ከጠቅላላው ጊዚያዊውን ከዘላለማዊ ጋር በማዋሃድ እንዲተገበር ሰፊና ተለዋዋጭ አስተሳሰብ አይደለምን?

لَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا رُسُلَنَا بِٱلۡبَيِّنَٰتِ وَأَنزَلۡنَا مَعَهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡمِيزَانَ لِيَقُومَ ٱلنَّاسُ بِٱلۡقِسۡطِۖ وَأَنزَلۡنَا

ٱلۡحَدِيدَ فِيهِ بَأۡسٞ شَدِيدٞ وَمَنَٰفِعُ لِلنَّاسِ وَلِيَعۡلَمَ ٱللَّهُ مَن يَنصُرُهُۥ وَرُسُلَهُۥ بِٱلۡغَيۡبِۚ إِنَّ ٱللَّهَ قَوِيٌّ عَزِيزٞ ٢٥

መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን፤ ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደነርሱ አወረድን፤ ብረትንም በውስጡ ብርቱ ኀይልና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያሉበት ሲሆን አወረድን፤ (እንዲጠቀሙበት)

አላህም ሃይማኖቱንና መልክተኞቹን በሩቁ ሆኖ የሚረዳውን ሰው ሊያውቅ (ሊገልጽ አወረደው)፤ አላህ ብርቱ አሸናፊ ነውና፡፡(ቁርኣን 57:25) ??

<<የብረት>> ምዕራፍ በሰላምም ሆነ በጦርነት ሜዳዎች እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ይህ ማዕድንን መጠቀም በጣም አስፈላጊ መሆኑን፣ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማመልከት ይመክራል

ሙስሊሞች ከምድር ጋር ያላቸው ቀረቤታ ሙሉ ሱራን በጣም ተፈላጊ በሆነ ማዕድን ከመሰየም የሚበልጥ ማስረጃ አለ? ሳይንስና ቴክኖሎጂን መጠቀም ከሚያሳስበውና ኢስላም የሚያዛቸውን የፈጠራና የስልጣኔ አዝማሚያዎች ማዳበር ከእምነት የሚመነጭ አስፈላጊ የባህሪይና ስነ-ምግባር አካልና ማንኛውም ሳይንቲስት በልቡ ሊይዝ የሚገባው መሆኑን ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው አያህ የበለጠ ምን አሳማኝ ማረጋገጫ አለ? በተጨማሪም ይህ አያህ ብረት አላህ በባሪያዎቹ ላይ ያበረከተው ትልቅ ስጦታ መሆኑን ያመለክታል፡፡በተመሳሳይ ጊዜም ብረት ለሁለት አገልግሎቶች ሊጠቅም እንደሚችል፡- <<ለብርቱ ሃይል>> (ብረት የጦር መሳሪያዎችን ለመፈብረክና ለወታደራዊ ዝግጅቶች ሲጠቅም) እና << ለመጠቀሚያዎች>> ( ሰዎች በሰላማዊ፣ አዎንታዊ ገንቢ እንቅስቃሴዎቻቸው ከዚህ ማዕድን ሊያገኙ የሚችሉት) ጥቅምን ያመላክታል፡፡ በሰላምም ሆነ በጦርነት ጉዳዮች በየዘመናቱ እያደገ ከመጣው የብረት አስፈላጊነት በላይ ትኩረት መስጠቱን የሚያመለክት ነገር አለን? በእራሳችን ዘመን ሰዎች ለጦርነት ወይንም ለአውዳዊ አላማዎች ሊጠቀሙበት ከሚችሏቸው በጣም አስፈላጊ መሳሪያዎች ለመሆን ችሏል።

ብረትን በተመለከተና በእርሱ የተሰየመ ሙሉ ሱራህ ላይ ስንደርስ በሱራት ሰባ የተጠቀሰውና አላህ ነቢዩ ዳውድ ብረት ማለስለስን (ማቅለጥን) ያስተማረበትን ፀጋ እናስታውሳለን፡፡ ይህ የተጠቀሰው በስልጣኔያዊ ጥረት አገባብ ነው፡፡ ዙልቀርነይን ሌላኛው ምሳሌ ነው፡፡ ለተጨቆኑት ሲናገርና ወደፊት ሊደርስባቸው ከሚችል ወረራ ሊከላከልላቸው ያለውን ፍላጎት ሲያሳውቃቸው እንዲህ ብሏቸዋል፡-

قَالَ مَا مَكَّنِّي فِيهِ رَبِّي خَيْرٌ فَأَعِينُونِي بِقُوَّةٍ أَجْعَلْ بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُمْ رَدْمًا ﴿٩٥﴾ ءَاتُونِي زُبَرَ ٱلْحَدِيدِ حَتَّىٰٓ إِذَا سَاوَىٰ بَيْنَ
ٱلصَّدَفَيْنِ قَالَ ٱنفُخُوا۟ حَتَّىٰٓ إِذَا جَعَلَهُۥ نَارًا قَالَ ءَاتُونِىٓ أُفْرِغْ عَلَيْهِ قِطْرًا ﴿٩٦﴾ فَمَا ٱسْطَٰعُوٓا۟ أَن يَظْهَرُوهُ وَمَا
ٱسْتَطَٰعُوا۟ لَهُۥ نَقْبًا ﴿٩٧﴾ الكهف: 95-97

‹‹ አለ ፦ ጌታዬ በርሱ ያስመቼኝ ሀብት (ከናንተ ግብር) በላጭ ነው፤ ስለዚህ በጉልበት እገዙኝ፤ በናንተና በነሱ መካከል ብርቱን ግድብ አደርጋለሁና። የብረትን ታላላቅ ቁራጮች ስጡኝ፥ (አላቸው)፤ በሁለቱ ኮረብታዎች (ጫፍ) መካከልም ባስተካከለ ጊዜ፣ አናፉ አላቸው፤ (ብረቱን) እሳትም ባደረገው ጊዜ የተቀለጠውን ነሐስ ስጡኝ፤ በርሱ ላይ አፈስበታለሁና፤ አላቸው። (የእጁጅና መእጁጅ) ሊወጡትም አልቻሉም፤ ለርሱ መሸንቆርንም አልቻሉም። ›› (ቁረአን 18፡95-97)

ቁርአን በሰው፣ በተፈጥሮና በልዕለ ተፈጥሮ መካከል ያለውን ልዩ የሰምምነት ምስል ያሳያል፡፡ ቁሳዊ ኃይሎችን ለሰው መጠቀሚያነት ለማዋልና በመቀየርና አላህን በማምለክ መካከል ያለውን ሚዛናዊነት ይገልፃል፡፡ በስነ-ውበታዊና በተጨባጭ የተፈጥሮ ገፅታዎች መካከል ያለውን ድንቅ ንፅፅር ያሳያል፡፡ በአንድ በኩል በሰዎች ጥንካሬና ተጨባጭ እምቅ ኃይል፣ እና በሌላ በኩል ከተቀረው ፍጥረት አኳያ ያላቸው ድክመትና በዘላቂነት አላህን ፈላጊ የመሆናቸው እውነታ በግልፅ ያመለክታል፡፡ የሕዝቦች ችሎታ ቁሳዊና ተፈጥሯዊ ፍላጎቶቻቸው ከሚሚላት ሊከለክላቸው ከሚችል አዝማሚያ መጠበቅ የሚያመለክት ቋሚ ቁርአናዊ ማስታወሻ አለ፦

۞ وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا دَاوُۥدَ مِنَّا فَضْلًا ۖ يَٰجِبَالُ أَوِّبِى مَعَهُۥ وَٱلطَّيْرَ ۖ وَأَلَنَّا لَهُ ٱلْحَدِيدَ ﴿١٠﴾ أَنِ ٱعْمَلْ سَٰبِغَٰتٍ
وَقَدِّرْ فِى ٱلسَّرْدِ ۖ وَٱعْمَلُوا۟ صَٰلِحًا ۖ إِنِّى بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿١١﴾ وَلِسُلَيْمَٰنَ ٱلرِّيحَ غُدُوُّهَا شَهْرٌ وَرَوَاحُهَا
شَهْرٌ ۖ وَأَسَلْنَا لَهُۥ عَيْنَ ٱلْقِطْرِ ۖ وَمِنَ ٱلْجِنِّ مَن يَعْمَلُ بَيْنَ يَدَيْهِ بِإِذْنِ رَبِّهِۦ ۖ وَمَن يَزِغْ مِنْهُمْ عَنْ أَمْرِنَا نُذِقْهُ مِنْ
عَذَابِ ٱلسَّعِيرِ ﴿١٢﴾ يَعْمَلُونَ لَهُۥ مَا يَشَآءُ مِن مَّحَٰرِيبَ وَتَمَٰثِيلَ وَجِفَانٍ كَٱلْجَوَابِ وَقُدُورٍ رَّاسِيَٰتٍ ۚ
ٱعْمَلُوٓا۟ ءَالَ دَاوُۥدَ شُكْرًا ۚ وَقَلِيلٌ مِّنْ عِبَادِىَ ٱلشَّكُورُ ﴿١٣﴾ فَلَمَّا قَضَيْنَا عَلَيْهِ ٱلْمَوْتَ مَا دَلَّهُمْ عَلَىٰ مَوْتِهِۦٓ إِلَّا

دَآبَّةُ ٱلْأَرْضِ تَأْكُلُ مِنسَأَتَهُۥ ۖ فَلَمَّا خَرَّ تَبَيَّنَتِ ٱلْجِنُّ أَن لَّوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ٱلْغَيْبَ مَا لَبِثُوا۟ فِى ٱلْعَذَابِ

ٱلْمُهِينِ ﴿١٤﴾ سبأ: 12- 14

‹‹ ለዳውድም ከኛ የሆነን ችሮታ በእርግጥ ሰጠነው፤(አልንም)፡- ተራራዎች ሆይ! ከርሱ ጋር ውዳሴን መላልሱ፤ በራሪዎችንም፣ (ገራንለት)፤ ብረትንም ለርሱ አለዘብንለት።ሰፋፊዎችን ጥሩሮች ሥራ፤ በአሠራርዋም መጥን፤ መልካምንም ሥራ ሥሩ፤ እኔ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና (አልነው)።ለሱለይማንም ነፋስን የቀትር በፊት ጉዞዋ የወር መንገድ ፣ የቀትር በኋላ ጉዞዋም የወር መንገድ ሲሆን ገራንለት፤ የነሐስንም ምንጭ ለርሱ አፈሰስንለት፤ ከጋኔኖችም በጌታው ፈቃድ በፊቱ የሚሰሩን፣ (አደረግንለት)፤ ከነሱም ውስጥ ከትእዛዛችን ዝንፍ የሚል ከነዲድ እሳት ቅጣት እናቀምሰዋለን። ከምኩራቦች፣ ከምስሎችም እንደ ገንዳ ከሆኑ ገበታዎችም፣ ከተደላደሉ ታላላቅ ድስቶችም፣ የሚሻውን ሁሉ ይሠሩለታል፤ (አልናቸውም)፡- የዳውድ ቤተሰቦች ሆይ! አመስጋኞች ሆናችሁ (ለጌታችሁ) ሥሩ፤ ከባሮቼ በጣም አመስጋኞቹም ጥቂቶች ናቸው። በርሱም ላይ ሞትን በፈጸምንበት ጊዜ መሞቱን በትሩን የምትበላ ተንቀሳቃሽ ምስጥ እንጂ ሌላ አላመለከታቸውም፤ በወደቀ ጊዜም ጋኔኖች ሩቅን ሚስጢር የሚያውቁ በሆኑ ኖሮ፣ በአዋራጅ ስቃይ ውስጥ የማይቆዩ እንደነበሩ ተረዱ። ›› (ቁርኣን 34፡10-14)

በሌላ ሱራ ይህ ይነበባል፡-

ٱلَّذِىٓ أَحَلَّنَا دَارَ ٱلْمُقَامَةِ مِن فَضْلِهِۦ لَا يَمَسُّنَا فِيهَا نَصَبٌ وَلَا يَمَسُّنَا فِيهَا لُغُوبٌ ﴿٣٥﴾ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَهُمْ

نَارُ جَهَنَّمَ لَا يُقْضَىٰ عَلَيْهِمْ فَيَمُوتُوا۟ وَلَا يُخَفَّفُ عَنْهُم مِّنْ عَذَابِهَا ۚ كَذَٰلِكَ نَجْزِى كُلَّ كَفُورٍ ﴿٣٦﴾

وَهُمْ يَصْطَرِخُونَ فِيهَا رَبَّنَآ أَخْرِجْنَا نَعْمَلْ صَٰلِحًا غَيْرَ ٱلَّذِى كُنَّا نَعْمَلُ ۚ أَوَلَمْ نُعَمِّرْكُم مَّا يَتَذَكَّرُ

فِيهِ مَن تَذَكَّرَ وَجَآءَكُمُ ٱلنَّذِيرُ ۖ فَذُوقُوا۟ فَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِن نَّصِيرٍ ﴿٣٧﴾ إِنَّ ٱللَّهَ عَٰلِمُ غَيْبِ

ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ إِنَّهُۥ عَلِيمٌۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿٣٨﴾ هُوَ ٱلَّذِى جَعَلَكُمْ خَلَٰٓئِفَ فِى ٱلْأَرْضِ ۚ فَمَن كَفَرَ فَعَلَيْهِ

كُفۡرُهُۥۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلۡكَٰفِرِينَ كُفۡرُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ إِلَّا مَقۡتٗاۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلۡكَٰفِرِينَ كُفۡرُهُمۡ إِلَّا خَسَارٗا ﴿٣٩﴾ فاطر: 39-35

‹‹ ጌታዬ ሆይ! ለእኔ ማር፡፡ ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባንም ንግሥና ስጠኝ፡፡ አንተ ለጋሱ አንተ ብቻ ነህና»አለ፡፡ነፋስንም በትእዛዙ ወደፈለገበት ስፍራ ልዝብ ኾና የምትፈስ ስትኾን ገራንለት፡፡ ሰይጣናትንም ገንቢዎችንና ሰጣሚዎችን ሁሉ (ገራንለት)፡፡ሌሎችንም በፍንጆች ተቆራኞችን (ገራንለት)፡፡«ይህ ስጦታችን ነው፡፡ ያለግምት ለግስ፤ ወይም ጨብጥ» (አልነው)፡፡ ›› (ቁርአን 38፡35-39)

ቁርአን ገለፃውን ይቀጥላል፡-

فَفَهَّمۡنَٰهَا سُلَيۡمَٰنَۚ وَكُلًّا ءَاتَيۡنَا حُكۡمٗا وَعِلۡمٗاۚ وَسَخَّرۡنَا مَعَ دَاوُۥدَ ٱلۡجِبَالَ يُسَبِّحۡنَ وَٱلطَّيۡرَۚ وَكُنَّا فَٰعِلِينَ ﴿٧٩﴾ وَعَلَّمۡنَٰهُ صَنۡعَةَ لَبُوسٖ لَّكُمۡ لِتُحۡصِنَكُم مِّنۢ بَأۡسِكُمۡۖ فَهَلۡ أَنتُمۡ شَٰكِرُونَ ﴿٨٠﴾ وَلِسُلَيۡمَٰنَ ٱلرِّيحَ عَاصِفَةٗ تَجۡرِي بِأَمۡرِهِۦٓ إِلَى ٱلۡأَرۡضِ ٱلَّتِي بَٰرَكۡنَا فِيهَاۚ وَكُنَّا بِكُلِّ شَيۡءٍ عَٰلِمِينَ ﴿٨١﴾ وَمِنَ ٱلشَّيَٰطِينِ مَن يَغُوصُونَ لَهُۥ وَيَعۡمَلُونَ عَمَلٗا دُونَ ذَٰلِكَۖ وَكُنَّا لَهُمۡ حَٰفِظِينَ ﴿٨٢﴾ الأنبياء: 82-81

‹‹ ለሱለይማንም (ትክክለኛይቱን ፍርድ) አሳውቅናት፤ ለሁሉም ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠን፤ ተራራዎችንም ከዳውድ ጋር የሚያወድሱ ሲኾኑ ገራን፤ አእዋፍንም፣ (እንደዚሁ ገራን) ሠሪዎችም ነበርን። የብረት ልብስንም ሥራ፣ ለናንተ ከጦራችሁ ትጠበቃችሁ ዘንድ፣ አስተማርነው፤ እናንተ አመስጋኞች ናችሁን? ለሱለይማም ነፋስን በኀይል የምትነፍስ በትእዛዙ ወደዚያች በርሷ ውስጥ በረከትን ወደ አደረግንበት ምድር (ወደ ሻም) የምትፈስ ስትሆን (ገራንለት)፤ በነገር ሁሉም ዐዋቂዎች ነበርን። ከሠይጣናትም ለርሱ (ሉልን ለማውጣት) የሚጠልሙንና ከዚያም ሌላ ያለን ሥራ የሚሠሩን (ገራንለት)፤ ለነሱም ተጠባባቂዎች ንበርን። ›› (ቁርአን 21፡79-82)

እነኚህ አያቶች በሰዎች፣ በተፈጥሮና በስውር ኃይሎች ለአላህ ፈቃድና ፍላጎት በፈጠራዊ ሁኔታ ባላቸው አብሮነት የሚኖራቸውን ከፍተኛ ሰልጣኔያዊ መቀላቀልና ውህደት ከሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎች ጥቂቶች ናቸው፡፡ እነዚ ትእይንተ ዓለማዊ

ኃይሎች በማምለክ፣በማወደስና በማመስገን ለእነኚህ ቸርነቶች ሁሉ በድርጊቶቻቸው ወደ አላህ ለተመለሱ ሰዎች አገልግሎት በታዘዙላት ውህዶች የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ በዚህም ሕይወት በምድር ላይ ወደ ሕልውና የመጣችበትን ክብር ለመቀዳጀት ወደ አላህ የዞሩ ናቸው፡፡

وَذَكِّرْ فَإِنَّ ٱلذِّكْرَىٰ تَنفَعُ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٥٥﴾ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾ مَآ أُرِيدُ مِنْهُم مِّن

رِّزْقٍ وَمَآ أُرِيدُ أَن يُطْعِمُونِ ﴿٥٧﴾ الذاريات:55-57

‹‹ ጋኔንንና ሰውን ሊገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም። ከነሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፤ ሊመግቡኝም አልሻም። ›› (ቁርኣን 51፡56-57)

እዚህ የተመረጡ የአላህ አገልጋዮችን፡- ነብዩ ዳውድንና ሱለይማንን እናገኛለን፡፡ የትኛውም የጊዜ ገደብ ወይንም አካላዊ መከለያ እንደማይወስናቸው ስውር ኃይሎች ሁሉ ግዙፍ የተፈጥሮ ኃይሎች ለእነርሱ ታዛዥችና አገልጋዮች ናቸው፡፡ በመጨረሻም ሳይንስም ኃይል የተነሳው ይሆናል፡፡ እነኚህም ኃይሎች ሁሉ፡- ብረት፣ ነፋስ፣ ነሐስ፣ጅን፡- በታዛዥነት የተፈጠሩት ሐላፊነት የተሰጣቸው፣ አምላክን አስታዋሽ፣ ንቁ በሆኑ ሕዝቦች ትዕዛዝ ላይ ለመዋልና ኢንዱስትሪና ኪነ ጥበብ በልማት ስልጣኔያዊ ዓላማዎቻቸውን ከግብ ለማድረስ በሚያደርገዋቸው ጉዞ እነርሱን ለማገዝ ነው፡፡ እነኚህ ቁርኣናዊ ታሪኮች ዛሬም ሰለ ብረትና ነሐስ የተጠቀሱ ግልፅ ማጣቀሻዎች ለእኛም ተግባራዊ መሆን የሚችሉ፣ ለዘመናዊ ስልጣኔ በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ ነገሮች ወይንም ለመገንባት፣ ኢንዱስትሪ ለማስፋፋትና በሁሉም ነገር ተመራጭ ለሚፈለግ የትኛውም ስልጣኔ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ አለህ ለነቢዩ ዳውድ ብረት ብቻ እንዳልሰጣቸው ማየት እንችላለን እንዴት ማለስለስ፣ ማቅለጥና ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ጭምር አስተምሯቸዋል፡፡ በተጨማሪም በምድር ላይ ህይወትን ለማለምለም ሆነ ለማውደም በጣም አስፈላጊ ኃይል የሆነው ንፋስ በማጣቀሻነት የተጠቀሰውንም መርሳት የለብንም፡፡

እነኚህ አያቶች የመለኮታዊ ሐይማኖቶች ብቸኛ አላማ ተከታዮቻቸው ወደ ብቸኝነትና ንቁ ያልሆነ ሁኔታ ለመምራትና ዓለም የምትለማ ሳትሆንየምትታለፍባት ቅስት መሆኑዋን ለማሳመን ወሳኝ ምላሽ የሚሰጠን ነው፡፡ለእነኚህ ህዝቦች ሐይማኖት <<የስልጣኔ ተቃራኒ>> ሲሆን እምነት <<ለፈጠራ ለአዲስ ግኝት እንቅፋት>> ነው፡፡ በሰዎችና በፈጣሪ መካከል የሚኖር ግንኙነት ለማንቀሳቀስና

ለመለወጥ ፍላጎት ወደ መታጣት እንደሚወስድ ይሚገታሉ፡፡ በተጨባጭ ነገሮች ላይ ብቻ የተመሰረቱ አስተምሮዎች ብቻ ሕይወትን በማለምለምና በማሻሻል ንቁ ሚና እንዳላቸው ይከራከራሉ፡፡ይህ አስተሳሰብ በአጠቃላይ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ቁርኣን ተሸናፊነትና ንቃት አልባነት ሙሉ ለሙሉ የማይቀበል መሆኑን የሚያስረዱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምሳሌዎች የቀረቡት ጥቂት ብቻ ናቸው፡ ፡ይህ ባህሪይ ሐይማኖትና እድገትን ሃሳባቸውን የማይለውጡ ጠላቶች የሚያደርጋቸው ነው፡፡ በእርግጥ ፈሪሀ አላህ መሆን ማለት የተለመዱ የሕይወት ሒደቶችን መተው ማለት አይደለም፡፡ የመገልገያነት እሴት የሌላቸው ድርጊቶችን መፈፀም ማለትም አይደለም፡፡ ከኢስላማዊ እይታ አንፃር አጠቃላዩ የሐይማኖት ጉዳይ የአኗኗር ልምምዶችና ክንውኖችን ጥራት ለማጠንከር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢስላም በእራሳቸው የሕይወትና የታሪክ ሒደቶች ዉስጥ የሚካተት ነው።